DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

Office of Integrity

ዲሴምበር (December) 2021

# የSY22-23 የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ምዝገባ እና ሎተሪ መመሪያ መጽሐፍ

ገቢ የተደረገው: በምክትል ቻንስለር ቢሮ፣ ስልታዊ የትምህርት ቤት ዕቅድ አውጪ እና ምዝገባ

**የDCPS አድልዎ አልባ ማስታወቂያ (Notice of Non-Discrimination)**

የTitle VI of the Civil Rights Act of 1964፣ የTitle IX of the Education Amendments of 1972፣ የSection 504 of the Rehabilitation Act of 1973፣ የ'the Age Discrimination Act of 1975'፣ የTitle II of the Americans with Disabilities Act of 1990፣ የ'the Genetic Information Nondiscrimination Act of 2008'፣ እና የ'D.C. Human Rights Act of 1977'ን፤ ተከትሎ፤ እንዲሁም ሁሉንም በእነዚህ ድህጋጌዎች ላይ - ተከትለው የተደረጉ ማስተካከያዎች አካትቶ፤ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) - በትምህርታዊ ፕሮግራሞቹ ወይም እንቅስቃሴዎች (በዚያ በሚደረግ የቅጥር ሁኔታ ወይም ከዚያም ከመግባት በኋላ ባለው) ላይ - በእውን ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ወይም በሚታሰብ፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በአካላዊ ገጽታ፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በትምህርት ደረጃ፣ በፖለቲካዊ ዝንባሌ፣ በዘር አመጣጥ (genetic) መረጃ፣ በጉዳተኝነት፣ በገቢ ምንጭ፣ የክሬዲት መረጃ፣ በቤት ውስጥ ጥቃት እንደ ተጎጂነት በመሆን ወይም የቤተሰብ አባል ተጎጂ በመሆኑ ምክንያት፣ በወሲባዊ ጥቃት ወይም አድብቶ-በማሳደድ፤ ምንም ዓይነት አድልዎ አያደርግም። የወሲባዊ ጥቃት ትንኮሳ፤ እንደ ፆታዊ-አድልዎ ሆኖ የሚታይ ሲሆን፣ በ'Title IX of the Education Amendments of 1972'ን ተከትሎ የሚከለከል ነው። በተጨማሪም፤ ከዚህ በላይ በተገለጹት ምድቦች ውስጥ ጥበቃ-የተሰጠው ላይ መሠረት ያደረገ ማንኛውም ትንኮሳ፤ የተከለከለ ነው።

በዚህ የመመሪያ መጽሐፍ (handbook) ውስጥ የተካተቱት ፖሊሲዎች እና የውይይት ሂደቶች፤ DCPS በማንኛውም ከላይ-በተጠቀሱት የጥበቃ-ምድቦች ላይ መሠረት ባደረገ-ሁኔታ፣ በተማሪዎች መግቢያ ጊዜ- ወይም በምዝገባ-ጊዜ - አድልዎን እንደማያደርግ ለማረጋገጥ የተቀረጸ ነው። የ'አድልዎ አልባ ማስታወቂያችንን (Notice of Non-Discrimination)' ለመመልከት፣ አስፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ እና በDCPS ውስጥ ስለ ፀረ-አድልዎ የበለጠ ለማወቅ: Dcps.dc.gov/anti-discrimination **ጎብኙ።** ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት ወይም አቤቱታን ፋይል-ለማድረግ፤ የ'Comprehensive Alternative Resolution & Equity (CARE) ቢድንን፣ በ1200 First St NE, 9th Floor, Washington, DC 20002 የሚገኘውን፤ በስልክ (202) 442-5405 ወይም በኢሜል በdcps.care@k12.dc.gov አነጋግሩ። the (CARE) Team - የአድልዎ ጥያቄዎችን ከመቀበል በተጨማሪ - የ'CARE Team' - ስለ ማንጓጠጥ አቤቱታ፣ መብቶችን መነፈግ፣ ወይም ተገቢ-ባልሆነ የተማሪዎች፣ የወላጅ፣ ወይም የጎብኚ እንግዳ እንክብካቤ- በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከገጠማቸው፤ የእነዚህን ሁሉ አቤቱታዎች የመቀበል ኃላፊነት አለበት።፣ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት: https://dcps.dc.gov/page/studentparentvisitor-grievance-process ጎብኙ።

## ማውጫዎች


| | |
|---|---|
| **ስለ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ምዝገባ እና ሎተሪ መመሪያ መጽሐፍ** | 4 |
| **ቁልፍ የሆኑ አባባሎች** | 4 |
| **በDCPS ምዝገባ የመግቢያ ዘዴዎች** | 8 |
| **በተሰጠ መብት መግቢያዎች (Admissions by Right)** | 9 |
| • ከK-12 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብቶ የመማር መብት | 9 |
| • ከምዝገባ በኋላ ከልሉን ለቅቆ መውጣት | 9 |
| **የSY22-23 አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፉ (Feeder Patterns)** | 10 |
| **የSY22-23 የትምህርት ቤት ክልል ካርታዎች** | 11 |
| • የSY22-23 የመጀመሪያና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክልል ካርታ (Map) | 11 |
| • የSY22-23 የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክልል ካርታ (Map) | 12 |
| • የSY22-23 የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካርታ (Map) | 13 |
| **የተማሪዎች ምደባ እና የትምህርት ቤት የክልል ወሰን ለውጦች** | 14 |
| **በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት የተገኘ መግቢያዎች** | 14 |
| • ስለ'My School DC' ሎተሪ | 14 |
| • ቅድመትምህርት ቤት (PK3) እና ቅድመ መዋዕለሕፃናት (PK4) | 15 |
| ○ ቅድመ እርምጃ PK | 15 |
| • ከክልል-ወሰን ውጪ አጎራባች ትምህርት ቤቶች | 16 |
| • ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች | 16 |
| • ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች | 16 |
| **የሎተሪ ምርጫዎች** | 16 |
| • የክልል-ወሰን ውስጥ (In-Boundary) ምርጫ (PK3/PK4 አመልካቾች እና የሁለት-ቋንቋ/dual language የሚጠቀሙ አመልካቾች ብቻ) | 17 |
| • ወንድምና እህት ምርጫዎች | 17 |
| ○ የወንድምና እህት-በትምህርት ገቢታ መገኘት ምርጫ | 18 |
| ○ ለወንድምና እህት-የቀረበ ምርጫ | 19 |
| ○ በወንድምና እህት ምርጫ ላይ ልዩ የሆነ ማመልከቻ | 19 |
| i. የ'Capitol Hill Cluster' ትምህርት ቤቶች | 19 |
| ii. ሁለት ቋንቋ (Dual Language) የሚጠቀሙ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች | 19 |
| iii. የትምህርት ቤት በርካታ መንገዶች | 19 |
| iv. ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች | 19 |
| ○ የወንድምና እህት ምርጫዎች ማረጋገጫ | 20 |
| • የቅርብነት (Proximity) ምርጫ | 20 |
| • ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- የተመደበላቸውን ቦታዎች ማግኘት | 20 |
| • ምርጫን መለወጥ (Preference Change) | 21 |
| **የሎተሪ ውጤቶች** | 21 |
| • የመጀመሪያ ደረጃ በተሰጠው ትምህርት ቤት የተዛመዱ ተማሪዎች | 22 |
| ○ ከሎተሪ-በኋላ (Post-Lottery) ማመልከቻዎች | 22 |
| • የመጀመሪያ ደረጃ ባልተሰጠው ትምህርት ቤት ውስጥ የተዛመዱ ተማሪዎች | 22 |
| • ያልተዛመዱ ተማሪዎች | 22 |
| • በተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች የሎተሪ ውጤቶች | 23 |

| | |
|---|---|
| **ተጠባባቂ (Waitlist)** | 23 |
| • የተጠባባቂ ቅደም ተከተል በተመረጠ ትምህርት ቤቶች የተሰጠ ምርጫ/ፕሮግራሞች | 24 |
| **መደበኛ በሆነ ምደባ መግባት** | 24 |
| • ስለመደበኛ ምደባዎች | 24 |
| • የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ምደባዎች ክፍል | 24 |
| • በአዲስ መልክ የተገኘ የልዩ ትምህርት-ብቁነት ለPK3 እና PK4 ተማሪዎች (የቅድሚያ ደረጃዎች ምደባዎች) | 25 |
| • እንግሊዘኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ አገልግሎቶች (በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ክፍል ምደባዎችን) ውስጥ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎች | 25 |
| • የተማሪ ምደባ ቢሮ ዝውውሮች | 26 |
| ○ በራስ ውሣኔ የሚደረግ፣ ከክልል ወሰን ውጪ ዝውውሮች | 26 |
| ○ የማደጎ እንክብካቤ ውስጥ/Foster Care ያሉ ልጆች (የዲሲ የልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎቶች አስተዳደር/DC Child & Family Services Administration) | 26 |
| ○ የወታደር ቤተሰቦች (Military Families) | 27 |
| ○ ቤት አልባነት (Homelessness) | 27 |
| **ምዝገባ (Enrollment)** | 29 |
| • የሎተሪ ምዝገባ | 29 |
| • የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎች | 29 |
| • ምርመራ እና የዲሲ ነዋሪ ያለመሆን አጠራጣሪነት | 30 |
| • የትምህርት ቤት ጤና መስፈርቶች | 30 |
| ○ ክትባቶች (Immunizations) | 31 |
| • በትምህርት ቀኑ ውስጥ፣ መድኃኒት መውሰድ/የሕክምና እንክብካቤ ማስፈለግ | 31 |
| • የአትሌቲክ ተማሪዎች ምዝገባ | 31 |
| • መውጣት/መልቀቅ | 31 |
| **ልዩ የምዝገባ ሁኔታ ያላቸው ተማሪዎች** | 32 |
| • የተመረጠ 504 ፕሮግራም | 32 |
| • ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies) | 32 |
| • የኤምባሲ ቤተሰቦች | 33 |
| • ቪዛ የሚጠይቁ የውጪ ሃገር የስኮላርሽፕ (Scholarship) የልውውጥ ተማሪዎች | 33 |
| • የኢሚግሬሽን ሁኔታ (Immigration Status) | 33 |
| • በዓመቱ አማካኝ ላይ (Mid-Year) የማመልከቻ ሂደት | 33 |
| • የዲሲ ነዋሪዎች ያልሆኑ (Non-DC Residents) | 34 |
| **የDCPS ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ፕሮግራም መግቢያ መስፈርቶች እና ሂደቶች** | 35 |
| **ከተማአቀፍ፣ ሁለት ቋንቋ፣ እና ሞንተሶሪ (Montessori) ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች** | 35 |
| • ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች | 35 |
| • ሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች | 35 |
| ○ ሙሉ (Whole) ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች | 35 |
| ○ የመጀመሪያ ደረጃ የሆኑ መሠረታዊ ፕሮግራሞች (Elementary Strand Programs) | 36 |
| • የሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች – ከ6-12ኛ ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች - የባለሁለት ቋንቋ (Dual Language) ፕሮግራሞች | 36 |
| • የሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራሞች | 36 |

| | |
|---|---|
| ○ ሙሉ (Whole) ትምህርት ቤት ፕሮግራም | 36 |
| ○ መሠረታዊ ፕሮግራሞች | 36 |
| • ሁለት ቋንቋ ፕሮግራም የምዝገባ ፖሊሲዎች | 36 |
| ○ የቋንቋ የበላይነት: ከPK3-1 ክፍሎች የምዝገባ ፖሊሲ | 36 |
| ○ የስፓኒሽ ቋንቋ ችሎታ ብቃትን መፈተኛ: ከ2-12 ክፍሎች የምዝገባ ፖሊሲ | 36 |
| ○ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) ለሚጠቀሙ (ከPK3-5) ምዝገባ | 37 |
| ○ ሁለት ቋንቋ ያልሆነ (Non-Dual Language) አማራጭ ትምህርት ቤት ምደባ (እህት ትምህርት ቤት) (ከK-8 ክፍሎች) | 37 |
| ○ ሁለት ቋንቋ ያልሆነ አማራጮች ለPK3 እና PK4 | 38 |
| • ሞንተሶሪ (Montessori) ትምህርት ቤት ምዝገባ ፖሊሲዎች | 38 |


# ስለ ኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ምዝገባ እና ሎተሪ መመሪያ መጽሐፍ

**አጠቃላይ የምዝገባ ጥያቄዎች**
*የምዝገባ ቡድኑን በ*
enroll@k12.dc.gov ወይም (202)

የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) የምዝገባ እና ሎተሪ

*መመሪያ መጽሐፍ፣ ለቤተሰቦች እና ትምህርት ቤቶች፤ በሕግጋቶች፣*

*መመሪያዎች፣ ሂደቶች፣ እና በ2022-23 የትምህርት ዓመት በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ፤ በመግቢያ (admission) እና በምዝገባ ላይ ያሉ ልምዶችን ላይ ዝርዝሮችን እና መመሪያዎችን ይሰጣል። በሙብት፣ በሎተሪ፣ እና ይፋዊ በሆነ ምደባ የሚደረጉ የትምህርት ቤት መግቢያዎችን፤ እንዲሁም ሌሎች የምዝገባ ሁኔታዎችን እና መረጃዎችን የመመሪያ መጽሐፉ ይገልፃል።*

## ቁልፍ የሆኑ አባባሎች

**አዋቂ (Adult) ተማሪ፡** በምዝገባው ጊዜ፣ ተማሪው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ዕድሜ ካለው፣ ምዝገባውን ራሳቸው እንዲያጠናቅቁ ብቁ ይሆናሉ። አዋቂ የሆነው ተማሪ ከወላጅ ጋር የሚኖር ከሆነ፣ የወላጅን አድራሻ በመጠቀም እና የዲስትሪክቱ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ ቃለ መሃላ የተገባበትን መረጃ እና ጊዜው ያላለቀ (valid) የነዋሪነት ማረጋገጫ ደጋፊ የሆኑ ሰነዶችን፣ አዋቂ ተማሪው ማቅረብ ሊኖርበት ይችላል። በምዝገባው-ጊዜ - ከ18 ዓመት በታች ተማሪው ከነበረ፤ ነገር-ግን በትምህርት ዓመቱ ወቅት 18 ዓመት ከሞላው፣ የዲስትሪክት ነዋሪነታቸው የሚቀጥል እና እስከ-አሁኑ የትምህርት ዓመት ማብቂያ ድረስ፣ የምዝገባ ወረቀቶችን በድጋሚ ማስገባት አያስፈልጋቸውም።

- የ'OSSE' ቢሮን የምዝገባ እና የነዋሪነት የመመሪያ መጽሐፍን ለተጨማሪ ዝርዝሮች ተመልከቱ።

ከተማአቀፍ ትምህርት ቤት፡ የተከለለ ወሰን የሌለው ትምህርት ቤት ሆኖ በክልል ወሰን ውስጥ ያለ ትምህርት ቤት ሊባል የማይችል። ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት በሎተሪ ብቻ እና ለማንኛውም ተማሪ/ቤተሰብ የምዝገባ ዋስትና መስጠት አይችልም። በኮሎምብያ ዲስትሪክት ዙሪያ የሚገኙ ተማሪዎች በከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመግባት በ'My School DC' ሎተሪ በኩል ማመልከቻቸውን ማስገባት አለባቸው። በከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቅርብነት የተመረጠ (proximity preference) ለማግኘት ተማሪዎች ብቁ አይሆኑም።

- የSY22-23 የከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶችን፣ በገጽ 35 ይመልከቱ።

**አስገዳጅ የሆኑ ክፍል ደረጃ(ዎች)፡** ተማሪዎች በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ እያሉ በሚዛመዱበት የክፍል ደረጃ(ዎች) ውስጥ ተማሪዎች ትምህርት ቤት እንዲገቡ ሕጉ ይጠይቃል። በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ፣ ከመዋዕለ-ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ጋር በተዛመደ ሁኔታ፣

ዕድሜያቸው በ5 እና 18 መካከል ያሉ ተማሪዎች ትምህርት ቤት እንዲገቡ ሕጉ ያስገድዳል። ተማሪው አስገዳጅ በሆነው (compulsory) የትምህርት ዕድሜ ውስጥ ሆኖ ለመወሰድ የሚያስችለው፣ እና በመዋዕለ-ሕፃናት ውስጥ መማር ያለበት ዕድሜ፤ በሴፕቴምበር (September) 30 ቀን ላይ፣ የ5 ዓመት ዕድሜ - ሊኖረው ይገባል።

**ሞግዚትነት:** ብቁና ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት በአካል ሞግዚት እንዲሆን መብት የተሰጠው ግለሰብ። (5-A DCMR § 5099**)**

**ባለ ሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች:** የተወሰኑ ወይም ሁሉንም የትምህርት አሰጣጥ ስርዓትን - ከእንግሊዘኛ ሌላ፣ በሌላ ቋንቋ የሚሰጥ ፕሮግራም። አንዳንድ ባለሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች በመላው ትምህርት ቤት የሚሰጥ ፕሮግራሞች ሲሆኑ፣ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የባለ ሁለት ቋንቋ ፕሮግራም መንገድ ሰጪ እና ባለ ሁለት ቋንቋ ያልሆነ ፕሮግራም የምርጫ መንገድን ይሰጣሉ። ባለ ሁለት ቋንቋ (Dual language) ፕሮግራሞች፤ ለመካፈል የሎተሪ ማመልከቻን ማስገባት ያስፈልጋል።

- የSY22-23 ባለ ሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞችን፣ በገጽ 35 ይመልከቱ።

**የቅድመ እርምጃ ቅድመ-መዋዕለሕፃናት ትምህርት ቤቶች:** የቅድመ እርምጃ ቅድመ-መዋዕለሕፃናት (PK)፣ ለሁሉም በክልል ወሰን ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦች በቅድመ-ትምህርት ቤት (PK3) እና ቅድመ-መዋዕለሕፃናት (PK4) እንዲገቡ ዋስትና ይሰጣቸዋል። የቅድመ እርምጃ PKን ቦታ ለማረጋገጥ፣ በክልል ወሰን ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻቸውን በPK3-8 የመጨረሻ ቀን በኦንላይን በክልል ወሰናቸው ውስጥ ወደሚገኘው ትምህርት ቤት ማስገባት አለባቸው።

ከመጨረሻ ቀኑ በፊት የ'My School DC' ሎተሪን ያስገቡ በክልል-ወሰን ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች፣ ከሌላ ከፍተኛ ደረጃ ከተሰጠው ትምህርት ቤት ጋር እስካልተዛመዱ ድረስ፣ ለቅድመ እርምጃ PK ተዛማጅነት ዋስትና ይኖራቸዋል።

- የSY22-23 ቅድመ እርምጃ PK ትምህርት ቤቶች፣ በገጽ 15 ይመልከቱ።

**አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (Feeder Pattern) ትምህርት ቤት:** አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ ትምህርት ቤት ተማሪው አሁን ካለበት ትምህርት ቤት አጠናቆ ከወጣበት ክፍል ተዘዋውሮ የመግባት መብት ያለው ትምህርት ቤት ነው። ይህ የምደባ አሰራር የሚከሰተው፣ ተማሪው ከመጀመሪያና አንደኛ ደረጃ ወደ መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ሲዛወር ወይም ከመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም ከትምህርት ቤት ካምፓስ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲዛወር ብቻ ነው። ሁለት ዓይነት የአዘዋዋሪ ንድፎች ዓይነቶች:

- **የአካባቢ አዘዋዋሪ ንድፍ (Geographic Feeder Pattern):** የአካባቢ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (Geographic Feeder Pattern) ትምህርት ቤቶች፣ በትምህርት ቤት ክልል እና ቅርብነት የተገነዱ ናቸው። የአካባቢ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (Geographic feeder pattern) መብቶች፣ ተማሪው በዚህ አዘዋዋሪ ሆኖ በሚያስተላልፍ ትምህርት ቤት ውስጥ እንደ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary)፣ በ'My School DC' ሎተሪ የተመዘገቡ ተማሪዎችን በሙሉ ያካተተ ነው። የአካባቢ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (Geographic feeder pattern) መብቶች፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የነበሩ ተማሪዎችንና በኋላ ግን ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) የሄዱ ተማሪዎችን፣ ወይም ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) የሆኑና ያቋረጡ ተማሪዎችን ያካተተ አይደለም። ከምዝገባ በኋላ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) መውጣትን በተመለከተ የበለጠ መረጃን ለማግኘት፣ በገጽ 9 ላይ ይመልከቱ።

- **ፕሮግራምን የተከተለ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (Programmatic Feeder Pattern):** ፕሮግራምን የተከተለ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (Programmatic feeder pattern) ማለት፣ በልዩ የፕሮግራም ጥናት (እንደ ሁለት ቋንቋ መናገር)፣ የተዘጋጁ የትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች ማለት ናቸው። ፕሮግራምን የተከተለ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (programmatic feeder pattern)፣ በልዩ ፕሮግራሞች ትምህርት ቤት/ፕሮግራም የተመዘገቡ ተማሪዎችን፣ በዚያው በልዩ ትምህርቶች ጥናት ውስጥ ሆነው ወደ ሁለተኛና መካከለኛ ደረጃ ወይም

ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዝውውር በሚያደርጉበት ጊዜ፣ በሚቀጥለው የትምህርት ቤት ደረጃ እንዲመዘገቡ መብት የሚሰጥ ነው።

- ○ የSY22-23 አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፉትን (feeder patterns)፤ በገጽ 10 ይመልከቱ።

**የአካባቢ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (Geographic Feeder Pattern):** *ከላይ የሚገኘውን፣ አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ ትምህርት ቤት (Feeder Pattern School) ይመልከቱ።*

**አሳዳጊ (Guardian):** በብቃት ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ሕጋዊ አሳዳጊ እንዲሆን የተመረጠ ግለሰብ። (5-A DCMR § 5099)

**በክልል ወሰን ውስጥ (In-Boundary) ምርጫ:** ለDCPS ቅድመ-ትምህርት ቤት (PK3) እና ለቅድመ-መዋለሕፃናት (PK4) በክልል-ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤቶች፣ ወይም በK-5 ውስጥ ላሉ ተማሪዎች በሁለት-ቋንቋ መስጫ በሆነው በክልል ወሰን (in-boundary) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤታቸው ውስጥ ለሚያመለክቱ፤ ብቻ በስራ-ላይ የሚውለው የሎተሪ ምርጫ ነው። የPK3 እና PK4 አመልካቾች፣ የሎተሪ ምርጫውን፤ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በሚገኝ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ያገኛሉ። ከK-5 በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በሚገኝ ትምህርት ቤት በሚሰጠው፣ የሁለት ቋንቋ (dual language) መስጫ-ውስጥ፤ ለሁለት ቋንቋ (dual language) መስጫ ካመለከቱ፤ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ምርጫን ለማግኘትም ይችላሉ። በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሁለት ቋንቋ (dual language) መስጫ ውስጥ ስለ ማመልከት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ በገጽ 37 ላይ ተመልከቱ።

**በክልል ወሰን ውስጥ (In-Boundary) ትምህርት ቤት (አጎራባች ወይም ዞን ውስጥ የገቡ ትምህርት ቤቶችንም የሚጨምር):** በተማሪው የመኖሪያ አድራሻ አማካኝነት፣ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ለመግባት ተማሪው መብት የሚያገኝበት ትምህርት ቤት።

- የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ለማወቅ፣ ወደ enrolldcps.dc.gov/node/41 ሂዱ።
- የSY22-23 የትምህርት ቤት ወሰኖችን በትምህርት ቤት ደረጃ የሚያሳዩትን ካርታዎች (maps) ለማግኘት ገጽ 11 ይመልከቱ።

**የሎተሪ ምርጫ:** በተወሰኑ መመዘኛ መሠረት፣ ለሎተሪ አመልካቶች የተሰጠ ልዩ ስልጣን። DCPS የሎተሪ ምርጫዎችን የሚመድብ እና እንደተመደቡበት ምርጫዎቻቸው፣ በተገኙ ክፍት የሆኑ ቦታዎች ውስጥ፣ ለተማሪዎች ይሰጣል።

- የDCPS የምርጫ ዓይነቶችን በገጽ 16 ይመልከቱ።

**ሞንተሶሪ (Montessori):** የሞንተሶሪ (Montessori) ትምህርት አሰጣጥ የልጁን የመማር ተፈጥሮአዊ ዝንባሌን ባተኮረ ሁኔታ ይካሄዳል። የሞንተሶሪ (Montessori) አስተማሪዎች ትዕዛዝ ከመስጠት ይልቅ የማመላከት አሰራርን መጠቀም፣ እያንዳንዱን ተማሪ ካለው/ላት ፍላጎት፣ ከሚሹት ነገር ጋር እና ከእድገት ደረጃቸው ጋር የሚሄዱ እንቅስቃሴዎች ጋር ያገናኟቸዋል። በክፍሉ ውስጥ መነቃነቅን እና በጋራ መስራትን እንዲያስች ሆኖ የተቀረፀ ሲሆን፣ ትኩረት እንዲጨምር እና ስርዓት ማክበርንም ባገናዘበ ሁኔታ መስራትን የሚያበረታታ ነው። የDCPS ሞንተሶሪ (Montessori) ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞችን በገጽ 36 ይመልከቱ።

**'My School DC' ማመልከቻ:** ለሁሉም የDCPS ቅድመ-ትምህርት ቤት (PK3) እና ቅድመ መዋዕለሕፃናት (PK4) ፕሮግራሞች፣ በDCPS የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት፣ የDCPS ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ትምህርት ቤቶች ከሆኑት (PK3-12)፣ በማንኛውም የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ (PK3-5) በDCPS

የሁለት ቋንቋ (dual language) መስጫ ፕሮግራሞች፣ የDCPS ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች (PK3-12)፣ እና የDCPS የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (selective high schools) እና ፕሮግራሞች (9-12)ን ጨምሮ፤ ቤተሰቦች የኦንላይን ማመልከቻዎችን በሞሙላት መጠቀም አለባቸው። ተካፋይ የሆኑ የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችም፣ የ'My School DC' ማመልከቻን መጠቀም አለባቸው። የ'My School DC' ማመልከቻ፣ በMySchoolDC.org ላይ ይገኛል። ቤተሰቦች፤ እርዳታ-ለማግኘት፣ የ'My School DC' አጣዳፊ-መስመር (hotline)ን መደወል ይችላሉ: (202) 888-6336

የ'My School DC' ሎተሪ: በ'My School DC' ሎተሪ የሚካፈሉ ትምህርት ቤቶች በሙሉ ውስጥ፤ የአዲስ ተማሪዎችን ምደባ የሚወስን ነጠላ የሆነ፣ በዘፈቀደ (random) ሎተሪ ነው።

- የሎተሪ ማመልከቻው መቼ ማስገባት እንደሚያስፈልግ ለማወቅ፣ በገጽ 14 ይመልከቱ።
- ከ'My School DC' ሎተሪ ጋር የተያያዙ ወሳኝ ቀኖችን ለማወቅ፣ በገጽ 15 ይመልከቱ።

**የ'My School DC' የዓመቱ-አጋማሽ ማመልከቻ:** በተወሰነ የትምህርት ዓመት ውስጥ፣ ወደ ዲስትሪክቱ የመጡ ወይም አሁን ከሚገኙበት ትምህርት ቤት ወደ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት (DCPS ወይም ቻርተር) ለመዛወር የሚጠይቁ፣ ከPK3-12ተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የሚሆን ማመልከቻ ነው። ስለ ዓመቱ-አጋማሽ (mid-year) ማመልከቻ፤ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ በገጽ 33 ላይ ተመልከቱ።

**የ'My School DC' ከሎተሪ-በኋላ ማመልከቻ:** ይህ ማመልከቻ ተካፋይ ለሆኑ ትምህርት ቤቶች፣ በተወሰነ የትምህርት ዓመት ውስጥ የሎተሪ ማመልከቻ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ ላለፈባቸው፣ ወይም ሌሎች ተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ማመልከትን የሚጠይቁ ቤተሰቦች ካሉ፣ ማመልከት እንዲችሉ የሚረዳ ነው። ከሎተሪ-በኋላ ማመልከቻ የጊዜ ገደብ፤ ከማመልከቻ የጊዜ-ገደቡ ካለቀበት ቀን በኋላ ጀምሮ - እስከ ኦክቶበር (October) 5 ቀን 2022፣ ለሁሉም ክፍሎች የተራዘመ ይሆናል። የ'My School DC' ከሎተሪ-በኋላ ( Post-Lottery) ማመልከቻ፣ በmyschooldc.org ላይ ይገኛል።

**አጎራባች ትምህርት ቤት:** ***በክልል ወሰን ውስጥ (In-Boundary) ትምህርት ቤትን*** *ከዚህ በላይ ይመልከቱ።*

**ሌሎች ዋና እንክብካቤ ሰጪዎች (Other Primary Caregiver):** የተማሪው ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም አሳዳጊ፤ እንክብካቤና እርዳታ ማድረግ ሳይችል ቀርቶም ሆነም - ሳይሆን፤ የተማሪ ዋና እንክብካቤ ሰጪ ወይም ተቆጣጣሪ በመሆን ከእርሱ ወይም እርሷ ጋር አብሮ እየኖረ ተማሪውን የሚረዳ፤ ከወላጅ፣ ሕጋዊ-ሞግዚት፣ ወይም በፍርድ ቤት ከተወከለ አሳዳጊ ውጪ የሆነ ሌላ ግለሰብ። እነዚህ 'ሌላ ዋና እንክብካቤ ሰጪዎች'፣ የተማሪው ዋና እንክብካቤ ሰጪ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና የዲሲ ነዋሪነትን፣ ሌላ ዋና እንክብካቤ ሰጪ የመሆናቸውን ሁኔታ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ፣ በተጨማሪነት የሚጠየቁትን የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ 'DC Residency Verification (DCRV)' ቅጽ በመስፈርትነት ያሟሉ መሆን አለባቸው። *እባክዎን ያስታውሱ: እንደ 'ሌላ ዋና እንክብካቤ ሰጪ' ሆኖ ተማሪን ለማስመዝገብ የሚጠይቅ ግለሰብ፣ የተማሪው ሕጋዊ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት አለመሆኑን እና ተማሪው 'ሌላ ዋና እንክብካቤ ሰጪ' የሚል ትርጓሜን የሚያሟላ ግለሰብ ስላስመዘገበው ብቻ፤ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና ሞግዚቶች ያሏቸው ትምህርታዊ-መብቶችን የሚወስን አይሆንም።*

- የOSSE የምዝገባ እና ነዋሪነትን (Enrollment & Residency) በosse.dc.gov/publication/other-primary-caregiver-forms በመጎብኘት፣ እባክዎን የ'ሌላ ዋና እንክብካቤ ሰጪ'፣ 'Other Primary Caregiver (OPC)'ን ቅጽ ይመልከቱ።

**ከክልል ወሰን ውጪ (Out-of-Boundary) ትምህርት ቤት:** ከተማሪው የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary)  ሌላ የሆነ ትምህርት ቤት።

**ወላጅ፡** የተፈጥሮ ወላጅ፣ የእንጀራ አባት/እናት፣ ወይም በጉዲፈቻ ወላጅነት ምክንያት የተማሪው ሞግዚት ወይም ተቆጣጣሪነትን፣ የጋራ ጥበቃ (joint custody) የሆኑ። (5-A DCMR § 5099)

**ተካፋይ የሆነ (Participating) የሎተሪ ትምህርት ቤት፡** የ'My School DC' ሎተሪ አንዱ አካል ለመሆን የተስማማ ማንኛውም የ(DCPS ወይም ቻርተር) ትምህርት ቤት። አብዛኛዎቹ የDCPS እና የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት ሎተሪ ተካፋይ ናቸው።

**PK3 (ቅድመትምህርት ቤት፣ የሚባለውም)፡** በተመዘገቡበት የትምህርት ዓመት፣ September 30 ሲሆን ዕድሜአቸው ቢያንስ ሶስት ዓመት የሚሆናቸውን ተማሪዎች የሚያገለግል የቅድመ ልጅነት ፕሮግራም።

**PK4 (ቅድመ መዋዕለ-ሕፃናት፣ የሚባለውም)፡** በተመዘገቡበት የትምህርት ዓመት፣ September 30 ሲሆን ዕድሜአቸው ቢያንስ አራት ዓመት የሚሆናቸውን ተማሪዎች የሚያገለግል የቅድመ ልጅነት ፕሮግራም።

**ፕሮግራምን የተከተለ አዘዋዋሪ ንድፍ (Programmatic Feeder Pattern)፡** *ከላይ የተመለከተውን **አዘዋዋሪ የሆነ ማስተላለፊያ ያላቸው (Feeder Pattern)** ይመልከቱ።*

**የቅርብነት ምርጫ (Proximity Preference)፡** በዞናቸው ውስጥ ካለው የDCPS የመጀመሪያና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በእግር መንገድ ከግማሽ ማይል በላይ ርቀት ለሚኖሩ እና ከቤታቸው በእግር መንገድ ግማሽ ማይል ወይም ከዚያ ያነሰ በሚገኝ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary ) ትምህርት ቤት ለመግባት ላመለከቱ ተማሪዎች የሚሰጥ የሎተሪ ምርጫ ነው። ይህ ምርጫ ከPK3 - 5ተኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ብቻ የሚሰጥ ይሆናል። የቅርብነት ምርጫ (Proximity preference) ለከተማአቀፍ ወይም የተመረጡ ትምህርት ቤቶች አይሰጥም።

**የነዋሪነት ማረጋገጫ (Residency Verification)፡** የዓመታዊ የምዝገባ ሂደት አካል የሆነው አንዱ መስፈርት፣ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ሞግዚቶች፣ አዋቂ-የሆኑ (adult) ተማሪዎች፣ ወይም ሌላ ዋና እንክብካቤ ሰጪ የሆኑ ሁሉ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪ መሆናቸውን ማረጋገጫ ሆኖ፣ በየዓመቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

- ነዋሪነት እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል በገጽ 29 ይረዱ።

**ትምህርት ቤት የመግባት መብት (Right-to-Attend School)፡** የDCPS ትምህርት ቤት፣ ከK - 12ተኛ ክፍሎች ውስጥ ተማሪዎች እንዲገቡ እና በሎተሪ ሂደት ውስጥ ማለፍ አይጠበቅባቸውም። ተማሪዎች በDCPS ከK-12፣ ሁለት ዓይነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመግባት መብቶች አሏቸው፡ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤቶች እና አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላፍ (feeder pattern) ትምህርት ቤቶች። ለመጪው የትምህርት ዓመት፣ ተማሪዎች በአሁኑ ወቅት በሚማሩበት ትምህርት ቤት በድጋሚ የመመዝገብም መብት አላቸው።

**ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች**: ተማሪዎች ለመግባት ልዩ የብቁነት መስፈርት እና ወደትምህርት ቤቱ መግባት ማመልከቻ ማስገባት የሚያስፈልጋቸው የDCPS ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች ናቸው። ከ9ኛ -12ተኛ ክፍሎች ለመግባት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በሙሉ ማመልከት ይችላሉ፣ ነገር ግን የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች የሚጠይቋቸውን መስፈርቶች ያሟሉ ብቻ ለመግባት ብቁ ይሆናሉ። የDCPS የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ምንም የክልል ወሰን የሌላቸው እና ተማሪዎችን የተለየ መስፈርትን ላይ ባተኮረ ሁኔታ ተማሪዎችን ይቀበላል። ወደእነዚህ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ማንኛውም ተማሪ ማመልከት ይችላል፣ ነገር ግን እንደየትምህርት ቤቱ የመቀበያ ደንብ መሠረት፣ የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ የመግባት ብቁነት ይኖራቸዋል። አንድ ወይም ከዚይ በላይ በሆኑ የDCPS የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች ለሚያመለክቱ ተማሪዎች፣ የ'My School DC' ማመልከቻ ተጨማሪ ክፍሎችን መሙላት ያስፈልጋቸዋል።

- የDCPS የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች እና የመግቢያ መስፈርቶችን በገጽ 35 ይመልከቱ።

**ወንድምና እህት:** ለሚለው ትርጓሜ ሲሰጥ፤ ልጁ ቢያንስ አንዱ ወላጅ ወይም ሕጋዊ አሳዳጊው ባለበት በመደበኛነት በአሁኑ ጊዜ የDCPS ተማሪ እና ነዋሪ ሆነው፤ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖር ተማሪ ነው። (5-E DCMR § 2199.2)

**በአንድላይ የሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ:** ከዚህ በላይ የተተረጎመውን መሰረት፣ በአሁኑ ወቅት በትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገቡ እና የሚማሩ ወንድምና እህት ላላቸው ተማሪዎች፣ የ'My School DC' ሎተሪ ምርጫ ይሰጣቸዋል።

- በወንድምና እህት ምርጫ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 18ን ይመልከቱ።

**ለወንድምና እህት የቀረበ ምርጫ:** በሎተሪ አማካኝነት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቦታ የተሰጣቸው፣ ወንድምና እህት ያለው ተማሪ፣ የ'My School DC' ሎተሪ ምርጫ ይሰጣቸዋል።

**ልዩ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም:** በDCPS ወይም ፕሮግራሙን በአዘጋጀው ትምህርት ቤት፣ ከሌላ ትምህርት ቤት በበለጠ ሁኔታ፣ መሠረታዊ ለውጥ ያለው የትምህርት ልምድ የሚያካፍል ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም። አንዳንድ ልዩ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች የብቁነት መስፈርቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ። በDCPS የሚገኙ ልዩ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች፣ ስነጥበት፣ ሁለት ቋንቋ፣ ቅድመ ኮሌጅ፣ ግሎባል ጥናቶችና አለም አቀፍ ባካሎሪየት (Global Studies International Baccalaureate)፣ ሞንተሶሪ (Montessori)፣ ስቴም (STEM)፣ እና ሌሎችንም ጨምሮ ሊያካትቱ ይችላሉ።

**ስቴም - STEM (ሳይንስ (Science)፣ ቴክኖሎጂ (Technology)፣ ኢንጂነሪንግ (Engineering)፣ እና ሒሳብ (Math):** ስቴም (STEM) ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ እና ሒሳብን አዋህዶ፣ እያንዳንዱ የዚህ ይዘት ክፍሎች በሌሎቹ የይዘት ክፍል ውስጥ በኩል ደረጃ ተጣምረው፣ ከስነጽሁፍ እና ድርሰት ጎን ለጎን ለማስተማር ለማስቻል ነው። ተማሪው ስቴም (STEM)ን በዋናነት ወይም በስራ መስክ በሚወስድበት፣ እንዲሁም ሁሉም ተማሪዎች በስቴም (STEM) በቂ እውቀት ያላቸው ዜጎች ለማድረግ ዝግጁነታቸውን ለማሻሻል፣ የDCPS ስቴም (STEM) ጥምረት አላማው ነው።

**የመጨረሻ የክፍል ደረጃ (Terminal Grade):** ትምህርት ቤቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ደረጃ፤ ለምሳሌ፤ ለመጀመሪያና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: - ደረጃ 5፤ ከK- 8 የትምህርት ካምፓሶች እና መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች : - ደግሞ ደረጃ 8፤ እና ከ6-12 ትምህርት ካምፓሶች እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች: - ክፍል ደረጃ 12።

**ተጠባባቂ (Waitlist):** ተጠባባቂ (Waitlists) በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለመግባት ፍላጎት ያላቸውን፣ ነገር ግን በሎተሪ ሂደቱ

አማካኝነት ያልተዛመዱ ተማሪዎች ዝርዝር የያዘ ነው። 'My School DC' በሎተሪ ተካፋይ ከሆኑትን የሁሉንም ትምህርት ቤቶች የተጠባባቂዎች ዝርዝርን ይቆጣጠራል። ሆኖም ግን፣ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ቦታ ይኑራቸው አይኑራቸው የሚወስኑት፣ ከተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ተማሪውን ምን ጊዜ መጥራት እንደሚችሉ፣ እና ለመቀበል ወይም ላለመቀበል የመጨረሻ ቀኑን መወሰን የሚችሉት ራሳቸው ትምህርት ቤቶቹ ናቸው። የተሰጠውን ቦታ በሎተሪው በተወሰነው ተራ ቁጥራቸው መሰረት ትምህርት ቤቶቹ ለተማሪዎች ይሰጣሉ። ለምሳሌ፣ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ያሉ ተጠባባቂ ተማሪዎች፣ ቦታቸውን ከተራ ቁጥር 8 በፊት መስጠት አለባቸው።

**በዞን ውስጥ ያለ ትምህርት ቤት (Zoned School):** ***በክልል ወሰን ውስጥ (In-Boundary) ትምህርት ቤት****ን ከዚህ በላይ ይመልከቱ።*

## በDCPS ምዝገባ የመግቢያ ዘዴዎች

በDCPS ምዝገባ ተቀባይነት ያላቸው፣ እነዚህ ከዚህ በታች የሚገኙት ሶስቱ የመግቢያ ዘዴዎች እና ተግባራዊ ገጠመኞች (applicable scenarios) ዘዴዎች ብቻ ናቸው።

| የመግቢያ ዘዴ | ተግባራዊ ገጠመኞች (Applicable Scenarios) |
|---|---|
| **1. በመብት (By Right)** | **1.** የተማሪው የመኖሪያ አድራሻ፣ ለትምህርት ቤት ምዝገባ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ እና ተማሪው ከK-12 ክፍሎች የሚመዘገብ ነው። **ሁሉም የPK3 ወይም የPK4 ተማሪዎች የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻን ማስገባት አለባቸው።** |
| | **2.** ተማሪው የመጨረሻ ደረጃ (terminal grade)ን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ስላጠናቀቀ እና በተመደበለት የአካባቢ (geographic) ወይም ፕሮግራምን የተከተለ (programmatic) አዘዋዋሪ ትምህርት ቤት የመግቢያ ደረጃ ላይ ይመዘገባል። **የአካባቢ አዘዋዋሪ ንድፍ መብቶች፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ከተመዘገቡ በኋላ ወደ ከክልል ወሰን ውጪ (out of the boundary) የሄዱ ተማሪዎችን ወይም ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አዘዋዋሪ ንድፍ በማንኛውም ጊዜ ያቋረጡ ተማሪዎችን አያካትትም።** |
| | **3.** ተማሪዎች አሁን ባሉበት ትምህርት ቤት ውስጥ ወደሚቀጥለው ክፍል እንደገና ተመዝግበዋል። |
| | |
| **2. በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት** | **1.** የቅድመ-ትምህርት ቤት (PK3) እና ቅድመ መዋዕለ-ሕፃናት (PK4) አዲስ ተማሪዎች በሙሉ። |
| | **2.** በK-12 የDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከተማሪው ክልል ወይም አዘዋዋሪ ንድፍ ውጪ የሚመዘገቡ አዲስ ተማሪዎች በሙሉ። |
| | **3.** ወደ ሁለት ቋንቋ (dual language) መስጫ በሆነው በክልል-ወሰን ውስጥ ( in-boundary) ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገቡ - ሁሉም አዲስ ተማሪዎች (የሙሉ/whole ትምህርት ቤት ፕሮግራሞችን አይጨምርም)። (PK3-5) |
| | **4.** በDCPS ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች ውስጥ (PK3-12) የሚገቡ አዲስ ተማሪዎች በሙሉ። |
| | **5.** በDCPS የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች (9-12) ውስጥ የሚገቡ አዲስ ተማሪዎች በሙሉ። |
| | |
| **3. በመደበኛ ምደባ** (በሚከተሉት ዓይነት የተማሪዎች የምደባ ሁኔታዎች ብቻ፤ ለመደበኛው በክልል ውስጥ (in-boundary) እና በሎተሪ ምዝገባ ሂደቶች በተለየ ሁኔታ | **1. ልዩ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ ክፍል (Division of Specialized Instruction):** ተማሪው ለልዩ ትምህርት ለብቻ የተዘጋጀ (self-contained) ፕሮግራም ውስጥ ሲገባ፤ ለምሳሌ፤ BES, CES, ILS, SLS.[1] |
| | **2. ቅድመ ደረጃዎች (Early Stages):** ለPK3 ወይም PK4፤ ተጠብቆ-የተቀመጠ የ'Early Stages' ቅድሚያ-የሚሰጣቸው ቦታዎች ውስጥ የሚመደቡ፣ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (Students with disabilities)። |
| | **3. የቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division):** የእንግሊዝኛ-ቋንቋ ተማሪዎች በተገቢው ፕሮግራሞች ውስጥ ባላቸው የክፍል ምደባ መሰረት |

[1] This non-comprehensive list of self-contained program acronyms stand for the following: Behavior and Education Support (BES); Communication and Education Support (CES); Independence and Learning Support (ILS); and Specific Learning Support (SLS).

| | |
|---|---|
| ታይተው ተቀባይነት ይኖራቸዋል።) | የተፈቀደላቸው እንዲሁም ከአሜሪካ-ውጪ የሚመጡ ተማሪውች እና የውጪ ሃገር የትምህርት መረጃ ምርመራ መሰረት ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች። |
| | **4. የተማሪ ምደባ ቢሮ (Student Placement Office):**<br>a. በወጣቶች መልሶ-ማቋቋም አገልግሎት መምሪያ (Department of Youth Rehabilitation Services (DYRS)/በቤተሰብ ፍርድ ቤት ማህበራዊ አገልግሎት ክፍል (Family Court Social Services Division (FCSSD) ቁጥጥር በሚደረግበት ውስጥ ትጋት የሚያሳዩ ወጣቶች<br>b. በልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎት አስተዳደር (Child & Family Services Administration (CFSA)፣ ጥበቃ ስር ያሉ ልጆች<br>c. ከክልል ወሰን ውጪ (Out-of-Boundary) የመዛወር የግል ምርጫበራስ ውሣኔ የሚደረግ፣ ከክልል ወሰን ውጪ ዝውውሮች<br>d. በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የተፈናቀሉ ቤተሰቦች<br>e. የወታደራዊ ቤተሰብ ልጆች<br>f. ሰለባዎች፣ ያለፈቃድ፣ እና አስቸካይ መዛወር (ለደህንነት ጥበቃ)<br>g. የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎች (የዲሲ ሴፍ የተጎጂ ምርመራ ፕሮጀክት - DC SAFE Lethality Assessment Project)<br>h. ወጣት እና ዕድል አካዳሚ መምሪያ ሂደት ዘርግቷል።<br>i. ሁለት ቋንቋ ያልሆነ (Non-Dual Language) አማራጭ ትምህርት ቤት ምደባ (እህት ትምህርት ቤት/Sister School)<br>j. ቤት አልባ የሆኑ ልጆች እና ወጣቶች ድጋፎች መስጫ ፕሮግራም |

# *በተሰጡ-መብት መግቢያዎች (Admissions by Right)*

## ከK-12 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብቶ የመማር መብት

**የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ለማግኘት፣** http://enrolldcps.dc.gov/node/41ን: ይጎብኙ የምዝገባ ቡድኑንበ enroll@k12.dc.gov ወይም (202) 478-5738 ያነጋግሩ

DCPS በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኝ፣ የአካባቢው የሕዝብ ትምህርት ቤት ዘዴ ነው። ተማሪዎች በ5ተኛ እና በ18ተኛ የልደት በዓላቸው[2] መካከል፣ በተለመደው ሁኔታ ከመዋዕለ-ሕፃናት እስከ 12ተኛ ክፍል ጋር በተመሳሳይነት የዕድሜ ደረጃ ላይ እያሉ ትምህርት ቤት እንዲገቡ የዲሲ ሕግ ያስገድዳል። በSeptember 30፣ የ5 ዓመት ዕድሜ የሚሆናቸው ተማሪዎች፣ በእድሜያቸው በሚያስገድዳቸው መሠረት በትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው እንዲማሩ ተደርገው ይወሰዳሉ። ሁሉ የDCPS ትምህርት ቤቶች ለዲሲ ነዋሪዎች ነፃ ነው። በዋሽንግተን ዲሲ የሚኖር ማንኛውም ዕድሜው የሚያስገድደው ተማሪ፣ ቢያንስ በአንድ የክፍል መደብ — እነርሱን በማንኛውም ጊዜ መግባት የሚያስችላቸው፣ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ቢያንስ አንድ የመግቢያ መብት አላቸው። ለመግባት መብት ያለው ትምህርት ቤት፣ ለተማሪው እንደ በክልል ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ወይም አዘዋዋሪ (feeder pattern) ትምህርት ቤት ሆኖ መለየት ይችላል። ተማሪዎች ከK - 12 ክፍሎች ገብቶ የመማር መብት ባላቸው ትምህርት ቤት(ቶች) ውስጥ፣ የ'My School DC' ሎተሪን ሳያመለክቱ መግባት ይችላሉ።

[2] D.C. Official Code § 38-202(a).

በክልል ወሰን እና አዘዋዋሪ ንድፎች ስር በአሁኑ ወቅት ስላለው የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (attendance)፣ በDCPS ድህረ-ገጽ ላይ ሊገኝ ይችላል።[3] አዘዋዋሪ ንድፎች በየዓመቱ የመቀያየር ዕድል ሊኖራቸው ይችላል።

## ከምዝገባ በኋላ ክልሉን ለቅቆ መውጣት/መዛወር

ከPK-12 ሲማሩበት ከነበረው ከክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት፣ በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ መኖራቸውን ቀጥለው - ከክልል ወሰን ውጪ ሆነው የለቀቁ፣ በአዲሱ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ፣ ተማሪው የመማር መብት አለው። ተማሪው አሁን በወቅቱ ባለበት ትምህርት ቤት ውስጥም፣ እስከ ትምህርት ቤት የመጨረሻ የክፍል ደረጃ ድረስ መማሩንም መቀጠል ይችላል። ማንኛውም የመኖሪያ ስፍራ ለውጥ ሲኖር፣ ሁሉም ቤተሰቦች ያለውን ለውጥ በሶስት (3) ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

ከመጨረሻው የክፍል ደረጃ በኋላ፣ የመኖሪያ አድራሻቸውን መሰረት በማድረግ በክልል ወሰን (in-boundary) ውስጥ በተመደቡበት ቀጣይ ክፍል የመግባት ወይም ከክልል ወሰን ውጪ (outside of the boundary) ለሆነ ትምህርት ቤት በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት፣ ተማሪዎች የማመልከት መብት አላቸው። የቀድሞ የክልል ወሰን (in--boundary) አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (feeder school) ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው የመማር መብታቸውን የሚያጡ፣ እና የ'My School DC' ሎተሪን በመጠቀም እንደ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ተማሪ ማመልከት አለባቸው። ተማሪው የኮሎምብያ ዲስትሪክትን ለቆ በሚሄድበት ጊዜ ስለሚኖሩት አማራጮች መረጃ ለማግኘት በገጽ 34 ይመልከቱ።

# የSY22-23 አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፉ (Feeder Patterns)

ይህን ማገናኛ (link) SY22-23 DCPS School Feeder Patterns እባክዎን ይመልከቱ። የተመለከተው አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላፉ (feeder patterns)፣ በSY21-22 እና በSY22-23 መካከል - ከክፍል ወደክፍል ለሚዘዋወሩ ተማሪዎች የሚሰራ ነው። አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላፍ (Feeder pattern) መብቶች፣ ተማሪው የመጨረሻ ደረጃ (terminal grade)ን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ስላጠናቀቀ እና በተመደበለት የአካባቢ (geographic) ወይም ፕሮግራምን የተከተለ (programmatic) አዘዋዋሪ ትምህርት ቤት የመግቢያ ደረጃ የመመዝገብ መብት እንዲኖራቸው ይፈቅድላቸዋል። የአካባቢ አዘዋዋሪ ንድፍ መብቶች፣

በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ከተመዘገቡ በኋላ ወደ ከክልል ወሰን ውጪ (out of the boundary) የሄዱ ተማሪዎችን ወይም ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አዘዋዋሪ ንድፍ በማንኛውም ጊዜ ያቋረጡ ተማሪዎችን አያካትትም።

ማስታወሻ: በተማሪው የመማሪያ ጊዜ ቀስ በቀስ የማለቅን (assignment phase-in) ፖሊሲ እና ከቀድሞ ሕግ ለየት ባለ ሁኔታ (grandfathering) አንቀጽ መሠረት፣ አዘዋዋሪ መብቶች የመቀያየር ሁኔታዎች ሊታይባቸው ይችላል። በተማሪ ምደባ እና በትምህርት ቤት የክልል ወሰን ለውጦች ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ እባካችሁን በገጽ 14 ላይ ተመልከቱ።


- ለማጣቀሻነት፣ በዚህ ማገናኛ (link) SY21-22 DCPS School Feeder Patterns ላይ ምልከታ አድርጉ።

[3] https://dcps.dc.gov/boundaries

# የSY22-23 የትምህርት ቤት ክልል ካርታዎች


## የSY22-23 የመጀመሪያና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክልል ካርታ (Map)

የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ለማወቅ፣ enrolldcps.dc.gov/node/41ይጎብኙ።




## የSY22-23 የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክልል ካርታ (Map)

የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ለማወቅ፣ enrolldcps.dc.gov/node/41. ይጎብኙ።



# የSY22-23 የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካርታ (Map)

የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ለማወቅ፣ enrolldcps.dc.gov/node/41ይጎብኙ።



# የተማሪዎች ምደባ እና የትምህርት ቤት የክልል ወሰን ለውጦች

DCPS የትምህርት ቤት የክልል ወሰን፣ አዘዋዋሪ ንድፎችን፣ እና ሌሎች የተማሪ ምደባ ፖሊሲዎችን እንደየአስፈላጊነቱ አልፎ አልፎ አዲስ ለውጥና ማሻሻያዎችን ያደርጋል። ለSY22-23 ምንም የተደረጉ የክልል ለውጦች የሉም፤ ሆኖም-ግን ከዚህ ቀደም-ተላልፈው የመጡ ፖሊሲዎችን እና በወንድምና እህት (sibling) አማካኝነት የነበሩ የክልል ለውጦች እንደነበሩ ይቀጥላሉ። በተማሪ ምደባ ፖሊሲዎች፣ የክልል ወሰኖች፣ እና አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፉ (feeder patterns) ላይ፣ የበለጠ ለመረዳት፣ እባክዎን እዚህ [dcps.dc.gov/boundaries](dcps.dc.gov/boundaries) ይጎብኙ።

# በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት የተገኙ መግቢያዎች

## ስለ'My School DC' ሎተሪ

> **ስለ 'My School DC' ሎተሪ የበለጠ ለመረዳት:**
>
> *በ* [Www.myschooldc.org](Www.myschooldc.org) ይጎብኙ፤
> የምዝገባ ቡድኑን*በ* [enroll@k12.dc.gov](mailto:enroll@k12.dc.gov)
> ወይም (202) 478-5738 ያነጋግሩ

የግዛቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (The Office of the State Superintendent of Education (OSSE)፣ የ'My School DC' ሎተሪን፣ ከምክትል ከንቲባ የትምህርት ቢሮ (Office of the Deputy Mayor for Education (DME)፣ DCPS፣ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ (DC Public Charter School Board (DCPCSB)፣ እና ተካፋይ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል። 'My School DC'፣ በሁለቱም፤ በDCPS እና ተካፋይ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ተጠሪነትን እያገኘ፣ ኮመን ሎተሪ ቦርድ (Common Lottery Board) ተብሎ በሚጠራ ቦርድ ይተዳደራል። በእያንዳንዱ መደበኛ የተማሪ ማመልከቻ፣ ቤተሰቦች እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ማመልከት እና ደረጃ (rank) መስጠት ይችላሉ።

የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻ የሚያስፈልገው:

- በማንኛውም የDCPS ትምህርት ቤት እንደ አዲስ የPK3 ወይም PK4 ተማሪ ሆኖ ለመግባት፤ <u>በእናንተ የDCPS የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤትን ጨምሮ፣</u> ማመልከት።
- በDCPS ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ትምህርት ቤት፣ ከK-12ኛ ክፍሎች እንደ አዲስ ተማሪ ሆኖ ለመግባት ማመልከት።
- በDCPS ከተማአቀፍ ትምህርት ቤት (PK3-12)፣ እንደ አዲስ ተማሪ ሆኖ ለመግባት ማመልከት።
- በDCPS የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (selective high school) ወይም ፕሮግራም ውስጥ (9-12)፤ እንደ አዲስ ተማሪ ሆኖ ለመግባት ማመልከት።
- *አዲስ፤ ለSY22-23*: ሁለት-ቋንቋ (dual-language) መስጫ ውስጥ ገብቶ ለመማር፣ ከሚከተሉት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (PK3-5) ውስጥ በአንደኛው ማመልከት: በCleveland ES፣ Marie Reed ES፣ እና Tyler ES። *ይህ፣ ክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ያሉትን ተማሪዎች ጨምሮ፤ ለሁሉም ተማሪዎች በስራ-ላይ የሚውል ይሆናል።*[4]

የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻ አስፈላጊ <u>አይደለም</u>:

- በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ወይም የአካባቢው (geographic) ወይም ፕሮግራምን የተከተለ አዘዋዋሪ (programmatic feeder) የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ከK-12 ክፍሎች መመዝገብ።
- አሁን-በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ በድጋሚ-መመዝገብ፣ ወይም በአሁኑ-ትምህርት ቤታቸው ውስጥ መቆየት።
- በመደበኛ ምደባ አማካኝነት መመዝገብ።

---

[4] Beginning SY22-23 all families, even in-boundary families, will need to apply to attend the dual language track at the three DCPS elementary schools that offer both a traditional and a dual language strand: Cleveland ES, Marie Reed ES, and ES. In-boundary students will receive a preference but will not be guaranteed a seat. Students currently enrolled in the dual language strand will not need to apply to re-enroll. In-boundary students will not need to apply to attend the traditional strand. For more information see page 38.

የ'My School DC' ሎተሪ ሂደት፣ ሁሉም የዲሲ ነዋሪዎች ማግኘት ይችላሉ። ማንም ተማሪ፣ ባለው ጉዳተኝነት ወይም ሊኖረው ይችላል ተብሎ በሚጠረጠር ጉዳተኝነት ምክንያት ወደ DCPS ከመግባት ሊከለከል አይችልም። ማንም ተማሪ፣ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የብቃት-ችሎታው ምክንያት፣ ወደ DCPS ከመግባት ሊከለከል አይችልም። የተማሪው የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ሁኔታ፣ በሎተሪ ማመልከቻው ጊዜ ተገኝቶ የሚታይበት ሁኔታ አይኖርም። የሎተሪ ማመልከቻው፣ ስለልጁ የጉዳተኝነት ሁኔታ፤ ልጁ IEP መኖሩን-አለመኖሩን ጨምሮ፣ የ'My School DC' ሎተሪን ወደሚያመልክቱበት ትምህርት ቤት መረጃ እንዲያቀርቡ አይጠየቁም።

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ውሱንነት ያላቸው ተማሪዎች፣ በማንኛውም የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ማመልከት ይችላሉ። DCPS፤ በተማሪው የቋንቋ ፍላጎቶች ላይ እና በመኖሪያ-ቤት በሚነገር ቋንቋ ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፤ አድልዎ አያደርግም። የ' My School DC' ማመልከቻ፤ በአሳዳጊው የሚመረጠውን ቋንቋ በመጠየቅ፤ ከአሳዳጊው ጋር በተሻለ-ሁኔታ ለመግባባት 'My School DC' ማመቻቻ ያደርጋል። በተማሪው ምደባ-ላይ ጥቅም-ላይ የማይውል እና በሎተሪ ውጤቶቹ ላይ በማንኛውም መንገድ ተጽዕኖ አያደርግም።

የሎተሪ ማመልከቻዎች በኦንላይን በwww.myschooldc.org አማካኝነት ሊያስገቡ ይቻላል። 'EdFEST' በሚከናወንበት ወቅት፣ ወይም በማንኛውም የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ፤ የ'My School DC'ን አጣዳፊ የስልክ መስመርን (hotline) በ(202) 888-6336 በመደውም፣ የሎተሪ ማመልከቻውን በስልክ ማጠናቀቅ ይቻላል።

| በትምህርት ዓመት 22-23 የ'My School DC' ሎተሪ የጊዜ-ሰሌዳ | |
|---|---|
| ቅዳሜ፣ ዲሴምበር (December) 11 ቀን 2021 | EdFEST |
| ሰኞ፣ ዲሴምበር (December) 13 ቀን 2021 | የ'My School DC' ማመልከቻ ይጀምራል |
| ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (February) 1 ቀን 2022፤ በ11:59 p.m. EST | የማመልከቻው የመጨረሻ ማብቂያ ቀን (ከ9-12 ክፍሎች) |
| ማክሰኞ፣ ማርች (March) 1 ቀን 2022፤ በ11:59 p.m. EST | የማመልከቻው የመጨረሻ ማብቂያ ቀን (ከPK3-8 ክፍሎች) |
| አርብ፣ ኤፕሪል (April) 1 ቀን 2022 | የሎተሪ ውጤቶች ይገለጻሉ፤ ለትምህርት ዓመት 22-23 የምዝገባ ወቅት ይጀምራል |
| ሰኞ፣ ሜይ (May) 2 ቀን 2022 | በሎተሪ-መዘመድ ምዝገባ የመጨረሻ ማብቂያ ቀን |

## ቅድመትምህርት ቤት (PK3) እና ቅድመ መዋዕለ-ሕፃናት (PK4)

አዲስ የ3- እና 4-ዓመት ዕድሜ ያላቸውን በትምህርት ቤት ለማስገባት፣ በ'My School DC ሎተሪ በኩል- ሁሉም ቤተሰቦች ማመልከት አለባቸው። በሴፕቴምበር (September) 30[5] ቢያንስ የ3 ዓመት ዕድሜ ከሆናቸው - በቅድመ ትምህርት ቤት (PK3) እና ቢያንስ የ4 ዓመት ዕድሜ ከሆናቸው - በቅድመ መዋዕለሕፃናት (PK4)፤ ወላጆች ልጆቻቸውን ሊያመዘግቡ ይችላሉ።

DCPS በቅድመ ልጅነት ትምህርት አሰጣጥ ላይ ጠንካራ ዕሴትን ስለሚሰጥ፣ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ በተቻለ መጠን ብዙ ልጆች አድልዎ በሌለውና ፍትሃዊ መንገድ፣ ቦታዎችን ለመስጠት ጥረት ያደርጋል። ሆኖም ግን፣ በሕጉ መሠረት ተማሪዎች እስከ 5 ዓመት[6] ትምህርት ቤት የመግባት ግዴታ ስለሌለባቸው፣ በመሠረቱ ተማሪዎች በPK3 ወይም PK4 ውስጥ ቦታ ለማግኘት ዋስትና የላቸውም።

### *ቅድመ እርምጃ (Early Action) PK*

[5] 5-E DCMR § 2004.
[6] D.C. Official Code § 38-202(a).

ቅድመ እርምጃ (Early Action) በከተማው ውስጥ ዋስትና ያለው PK ብቻ ነው። ቅድመ እርምጃ (Early Action) PK፣ በተወሰነው ቅድመ እርምጃ (Early Action) PK ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ለሁሉም በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች፣ ወደ PK3 እና PK4 ፕሮግራሞች እንዲገቡ ዋስትና ይሰጣል። ቅድመ እርምጃ (Early Action) PK ቦታዎችን በእርግጠኝነት ለመያዝ፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሚገኙ ቤተሰቦች የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻን እስከ ማክሰኞ፣ ማርች (March) 1 ቀን 2022 11:59 p.m. EST የመጨረሻ-ማብቂያ ጊዜ ድረስ፣ ማስገባት አለባቸው። የቅድመ እርምጃ (Early Action) PK ትምህርት ቤቱ - እንደምርጫ ሆኖ በማመልከቻው ላይ መካተት ያለበት እና በማመልከቻው ላይ በሚገኘው እውነተኛ ቅደም-ተከተል ምርጫችሁ ላይ ባለው-መሠረት፣ ደረጃ-ሊሰጠው (ranked) ይገባል። ቤተሰቦች በ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻቸው ላይ፣ ከሌላ ደረጃው ከፍተኛ ከሆነ ትምህርት ቤት ጋር ካልተጣመሩ፤ በክልል ወሰናቸው ውስጥ (in-boundary) ከሚገኝ የቅድመ እርምጃ (Early Action) PK ትምህርት ቤት ጋር መጣመራቸውን የሚያሳይ የቅድመ እርምጃ (Early Action) PK ያገኛሉ።

ልጁ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ከሚገኝ ትምህርት ቤት ጋር ከተጣመረ፣ ቤተሰቦች፣ እንደሁሉም የሎተሪ ጥምረቶች ሁሉ፣ በሎተሪ መመዝገቢያ የመጨረሻ ቀን፣ (ሰኞ፣ ሜይ/May 2 ቀን 2022) ተማሪውን ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል። ተማሪው ከክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ከሚገኝ ከፍተኛ ደረጃ ካለው ትምህርት ቤት ጋር ከተጣመረና በPK3 ወይም PK4 ቦታ ካገኘ፣ ተማሪው በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በሚገኝ በቅድመ እርምጃ (Early Action) PK ውስጥ በሚገኝ የክልል ወሰን ትምህርት ቤት (in-boundary school) ብቁ ሆኖ መቀጠል የማይችል ሲሆን፤ ነገር ግን፣ እንደገና-ማመልከት ከፈለጉ፤ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያላቸውን የክልል ወሰን (in-boundary) ምርጫ ጠብቆ-ማቆየት ይችላሉ።

በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ለሚገኙ ቤተሰቦች፣ የPK3 እና PK4፣ የSY22-23 ቅድመ እርምጃ (Early Action) PK በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይገኛሉ:

1. Aiton Elementary School (ዋርድ/Ward 7)
2. Browne Education Campus (ዋርድ/Ward 5)
3. Bunker Hill Elementary School (ዋርድ/Ward 5)
4. Burroughs Elementary School (ዋርድ/Ward 5)
5. Drew Elementary School (ዋርድ/Ward 7)
6. King Elementary School (ዋርድ/Ward 8)
7. Langley Elementary School (ዋርድ/Ward 5)
8. Miner Elementary School (ዋርድ/Ward 6)
9. Moten Elementary School (ዋርድ/Ward 8)
10. Noyes Elementary School (ዋርድ/Ward 5)
11. Stanton Elementary School (ዋርድ/Ward 8)
12. Takoma Elementary School (ዋርድ/Ward 4)
13. Thomson Elementary School (ዋርድ/Ward 2)
14. Truesdell Elementary School (ዋርድ/Ward 4)
15. Turner Elementary School (ዋርድ/Ward 8)
16. Wheatley Education Campus (ዋርድ/Ward 5)

**ስለቅድመ እርምጃ (Early Action) PK የበለጠ ለመረዳት**

በ https://dcps.dc.gov/page/pre-kindergarten-pk3-and-pk4 ላይ ጎብኙ:

የምዝገባ ቡድኑን በ enroll@k12.dc.gov ወይም (202) 478-5738 ያነጋግሩ

## *ከክልል ወሰን ውጪ (Out-of-Boundary) አጎራባች የሆኑ ትምህርት ቤቶች*

ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አጎራባች ትምህርት ቤት ውስጥ ለመግባት ፍላጎት ያላቸው፣ ከK-12 ክፍሎች ለመመዝገብ ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦች በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት ማመልከት አለባቸው።

**ስለDCPS ትምህርት ቤት አማራጮችን ለማወቅ**

በ [Http://profiles.dcps.dc.gov/](Http://profiles.dcps.dc.gov/) ይጎብኙ፤

የምዝገባ ቡድኑን በ [enroll@k12.dc.gov](mailto:enroll@k12.dc.gov) ወይም (202) 478-5738 ያነጋግሩ

## ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች

ከተማአቀፍ ትምህርት ቤት ማለት የክልል ወሰን የሌለው እና በዚህም ምክንያት በማንኛውም ተማሪዎች፣ እንደ-ክልል ወሰን ውስጥ (in- boundary) ትምህርት ቤት ተብሎ ሊሰየም የማይችል ትምህርት ቤት ነው። በማንኛውም የክፍል ደረጃ በከተማአቀፍ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመግባት፣ ተማሪዎች፣ የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻን ማስገባት አለባቸው፤ ነገር ግን በሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ውስጥ ማመልከቻውን እንደገና ሳያስገቡ፤ ዳግመኛ-መመዝገብ ይችላሉ። በከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቅርብነት የተመረጠ (proximity preference) ለማግኘት ተማሪዎች ብቁ አይሆኑም።

- የSY22-23 የከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶችን በገጽ 35 ይመልከቱ።

## ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች

DCPS በተወሰነ አይነት የመመዝገቢያ ሂደቶች እና የመመረጥ መስፈርት መሠረት፣ ተማሪዎችን የሚቀበል፤ ስምንት (8) የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች አሉት። በነእነዚህ የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራም ውስጥ ዕድል ለማግኘት፣ ሁሉም ተማሪዎች የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻን ማስገባት አለባቸው። ከ9- 12 ክፍሎች ውስጥ ለመመዝገብ ብቁ የሆነ ማንኛውም ተማሪ፣ ወደእነዚህ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራም ማመልከት ይችላል፣ ነገር ግን የተመረጡ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም የፕሮግራሞች የተወሰኑ ተጨማሪ መስፈርቶች የሚያሟሉት ብቻ የሎተሪ ማዛመጃን ለማግኘት ወይም የተጠባባቂነት ቦታን ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ።

- የምዝገባ መስፈርቶችን እና ብቁነት ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በገጽ 35 ላይ እባክዎን ይመልከቱ።

## የሎተሪ ምርጫዎች

ተማሪዎች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ፤ የሎተሪ ምርጫ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላል። በትምህርት ቤቱ ምርጫ ያደረጉ ተማሪዎች፤ ምርጫ ካላደረጉ ተማሪዎች በፊት ወይም በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ከሆኑ፤ ምርጫ ካላደረጉት ተማሪዎች የበለጠ ከተጠባባቂ ዝርዝር ተመርጦ ምደባ እንዲያገኙ እና ቦታቸውን እንዲወስዱ ይጠየቃሉ።

DCPS የሎተሪ ምርጫ ያላቸውን ተማሪዎች በአጎራባች ሰፍራዎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እና ወንድምና እህትን በአንድ ትምህርት ቤት ለማስገባት እንደሚያምኝ ሆኖ ይዛመዳሉ። የሚከተሉት ምርጫዎች (preferences)፣ ለSY22-23 የDCPS የሎተሪ አመልካቾች ሆነው የሚከተሉትን መስፈርቶድ ለሚያሟሉ የተሰጠ ነው:

**ስለ ሎተሪ ስልተ-ቀመር (Algorithm) ይወቁ**

[ይህ ቪዲዮ](#) ስልተ ቀመሩ (algorithm) እንዴት እንደሚሰራ ያሳያል። *የ'My School DC'ን በ*[info.myschooldc@dc.gov](mailto:info.myschooldc@dc.gov) ወይም በ(202) 888-6336 ያነጋግሩ።

*የDCPS የምዝገባ ቡድን፣ በ*[enroll@k12.dc.gov](mailto:enroll@k12.dc.gov) ወይም በ(202) 478-5738 ያነጋግሩ።

1. የክልል ወሰን ውስጥ (In-boundary) ምርጫ (PK3/PK4 እና የሁለት ቋንቋ (Dual Language) የሚጠቀሙ አመልካቾች ብቻ)
2. ወንድምና እህት ያሉበት ምርጫ

3. የቅርብነት (Proximity) ምርጫ

*ማስታወሻ፡ ምርጫዎቹ በተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራም የመግቢያ ምዝገባ ሂደት ውስጥ አያገለግሉት፤ እና ለከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች የወንድምና እህት ምርጫ ብቻ አገልግሎት ላይ ይውላል።*

በተጨማሪም፤ በፍትሃዊ-እኩልነትን በማግኘት ከተመደቡ ቦታዎች (Equitable Access Designated Seats) ጋር፣ በአንዳንድ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የሎተሪ ቦታዎች፤ ብቁነት ላላቸው አመልካቾች ተይዘው የተቀመጡ ናቸው። ስለ ፍትሃዊ-እኩልነትን በማግኘት የተመደቡ ቦታዎች (Equitable Access Designated Seats) ተጨማሪ መረጃዎች፣ በገጽ 20 ላይ ይገኛል።

## 1. የክልል-ወሰን ውስጥ (In-Boundary) ምርጫ (PK3/PK4 አመልካቾች እና የሁለት-ቋንቋ/dual language የሚጠቀሙ አመልካቾች ብቻ)

**የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ለማግኘት፣**
http://enrolldcps.dc.gov/node/41ን: ይጎብኙ

የDCPS የምዝገባ ቡድኑን፣ በenroll@k12.dc.gov ወይም በ(202) 478-5738 ያነጋግሩ።

በPK3 እና PK4 በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ቦታ ማግኘታቸውን፣ ቤተሰቦች በተሻለ ሁኔታ ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤታቸው ውስጥ ወደ PK3 ወይም PK4 ቦታ ለማግኘት ያመለከቱ ወላጆች፣ በክልል ወሰን ውስጥ ምርጫቸው (in-boundary) መሰረት ይሰጣቸዋል።

- *ሁለት ቋንቋ(Dual Language) መስጫዎች ላይ የተሰጠ ማስታወሻ:* ሁለቱንም የተለመደ (traditional) እና ባለሁለት ቋንቋ (dual language) ማግኛን የሚያቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ (Cleveland ES, Marie Reed ES, እና Tyler ES)፤ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሚገኙ ተማሪዎች - ምርጫቸውን ማግኘት የሚችሉ ሲሆን፤ ነገር ግን፣ በሁለት ቋንቋ (Dual Language) ትምህርት ሰጪዎች ውስጥ ቦታ ማግኘታቸውን ዋስትና አይሰጥም። [በክልል-ወሰን ውስጥ (In-boundary) ያሉ ተማሪዎች፤ በተለመደ/traditional - (ባለሁለት ቋንቋ ያልሆኑ ) ውስጥ፣ ከK-5 በሆኑት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው የመማር መብት አላቸው።] በባለ-ሁለት ቋንቋ (dual language) በሚጠቀሙ ውስጥ በአሁኑ-ጊዜ የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ በሚቀጥለው የትምህርት ዓመት እንደገና-መመማር ማመልከት አያስፈልጋቸውም። ለተጨማሪ መረጃ፣ በገጽ 37ን ይመልከቱ።

- *በቅድመ እርምጃ(Early Action) PK - ውስጥ የተሰጠ ማስታወሻ:* ቅድመ እርምጃ (Early Action) PK የሚሰጡ፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገቡ ቤተሰቦች፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ቦታ ማግኘታቸው ዋስትና የሚያገኘው፣ በቅድመ እርምጃ (Early Action) PK፣ በገጽ 15 ላይ በሚገኘው ክፍል ላይ የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ከተከተሉ ብቻ ነው።

**እንዴት መጠየቅ ይቻላል (How to Claim):** ምንም እርምጃ መውሰድ አያስፈልግም። ይህ ምርጫ እራሱ በራሲ በአውቶማቲክ በ'My School DC' መመልከቻ ላይ የመኖሪያ አድራሻን መሰረት በማድረግ ይገባል። በምዝገባ ወቅት፣ በሚደረገው የDC የነዋሪነት ማረጋገጫ ሂደት ወቅት፣ የቤተሰቡ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የመኖሪያ አድራሻ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ ይረጋገጣል። **የዲሲ ነዋሪነታቸው ማረጋገጥ ያልቻሉ እና ምዝገባው በተካሄደ ጊዜ፣ በትምህርት ቤት የዞን ክልል ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች፣ ምርጫቸውን ሊያጡ እና የተሰጣቸውንም ዕድል (እና ተከታይ ምዝገባቸው) ሊሰረዝ ይችላል።** በዘፈቀደ በሚሰጠው የሎተሪ ቁጥራቸው መሰረት፣ ከዚህ በፊት ብቁ ለሆኑበት እና ለሌሎችም ማንኛውም ምርጫዎች፣ እንደገና ወደ ትምህርት ቤቱ የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ፤ ሆኖም ግን የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ምርጫቸው አይኖርም።

## 2. ወንድምና እህት ምርጫዎች

ወንድምና እህትን በአንድነት በትምህርት ቤት ማስገባት፤ ለተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ትምህርት ቤቶች የሚጠቅም ነው። በዚህም ሁኔታ፣ DCPS በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት የወንድምና እህት ምርጫን ይሰጣል። በአሁኑ ወቅት በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ወንድምና እህት ያላቸው፣ በመጪው ዓመት የሚማሩ፣ ወይም ለመጪው ዓመት በአንድ ዓይነት ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ምርጫው ለአዲሱ ተማሪ የተጠየቀለት፤ ወይም-ደግሞ ለመጪው-ዓመት - የማዛመቻ ወይም የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ቦታ የተሰጣቸው ተማሪዎች ብቻ፤ የወንድምና እህት ምርጫን ያገኛሉ። ወንድምና እህት (A sibling) የሚለው ትርጓሜ፤ ልጁ ቢያንስ አንዱ ወላጅ ወይም ሕጋዊ አሳዳጊው ባለበት በጋራነት በአሁኑ-ጊዜ በDCPS ከሚማር ተማሪ ጋር የሚማር እና ነዋሪ ሆነው፤ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖር ተማሪ ነው። ከዚህ በታች እንደተገለጸው ሁለት ዓይነት የወንድምና እህት ምርጫ አለ።

### *የሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ (Sibling-Attending Preference)*

ምዝገባው በተካሄደበት ወቅት፣ በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በተማሪው 'My School DC' ማመልከቻ ላይ የተመዘገበ እና በአሁኑ ወቅት እየተማረ የሚገኝ ወንድምና እህት ያለውና አመልካቹ በሚያመለክትበት የትምህርት ዓመትም መማራቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ፣ የሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ (sibling-attending preference) ለተማሪው ይሰጣል። የዚህ ምርጫ ዓላማ ወንድምና እህታማቾችን አብሮ በአንድ ህንፃ ለማድረግ ነው። ስለሆነም፣ የተማሪው ማመልከቻ በሚገባበት ወቅት፣ አሁን እየተማረ ያለው ወንድም ወይም እህት በመጨረሻው መልቀቂያ ክፍል ውስጥ መሆን የለበትም። በመጪው ዓመት ተማሪውን <u>የሚያስመዘግቡ</u> ቤተሰቦች፣ ለሚያመለክቱበት ትምህርት ቤት፣ የሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ (sibling-attending preference) መጠየቅ የሚችሉበት ሁኔታ፤ የሚገባው ተማሪ <u>በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ወይም አዘዋዋሪ (feeder) መብቶች ወይም ወደትምህርት ቤቱ የመግባት መደበኛ ምደባ፤ ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ሲታይ ነው።</u>

**ምሳሌ 1:** ጆን በአሁኑ ወቅት በ3ተኛ ክፍል በፓተርሰን (Patterson ES) ተመዝግቦ የሚገኝ ተማሪ ከሆነ እና ወደዚሁ ትምህርት ቤት 4ተኛ ክፍል ተመልሶ የመግባት ዕቅድ አለው፣ በዚህም መሰረት፣ ወንድምና እህቶቹ፣ በፓተርሰን (Patterson ES) ውስጥ፣ በሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ (sibling-attending preference) ሎተሪ አማካኝነት ለሚቀጥለው ዓመት ብቁ ያደርጋቸዋል።

**ምሳሌ 2:** ጆን፣ በፓተርሰን (Patterson) በግድ መግባት ባለበት ክፍል ውስጥ፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በመኖሩ ምክንያት እና በፓተርሰን (Patterson ES) ውስጥ ገብቶ-የሚማር አዲስ ተማሪ ከሆነ፤ በPK3/PK4 የሚገቡ ወንድምና እህቶቹ፣ በፓተርሰን (Patterson ES) ውስጥ፣ በሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ (sibling-attending preference) ሎተሪ አማካኝነት ለሚቀጥለው ዓመት ብቁ ያደርጋቸዋል።

**ምሳሌ 3:** ጆን በአሁኑ ወቅት በ5ኛ ክፍል - በፓተርሰን (Patterson ES) የሚማር ከሆነ እና በሚቀጥለው ዓመት በሌላ ትምህርት ቤት ውስጥ የ6th ክፍል የሚገባ ከሆነ፣ ወንድምና እህቶቹ፣ በፓተርሰን (Patterson ES) ውስጥ፣ በሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ (sibling-attending preference) ሎተሪ አማካኝነት ለሚቀጥለው ዓመት ብቁ <u>እንዳይሆኑ</u> ያደርጋቸዋል።

***አሁን፣ በትምህርት ገበታ ላይ ያለው ተማሪ በሚቀጥለው ዓመት በድጋሚ ያልተመዘገበ ከሆነ፣ የሚማር ወንድምና እህት ምርጫን ሊያገኙ የሚችሉ፣ ወንድምና እህቶቹ፤ የተሰጣቸው ማጣመሪያ (match) ወይም የተጠባባቂነት ዝርዝርን ሊያጡ፣ ወይም ምዝገባቸው ሊሰረዝባቸው እንደሚችል እባክዎን ያስታውሱ። እነዚህ ሁኔታዎች በሚከሰቱ ጊዜ፣ አመልካቹ በትምህርት ቤቱ የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ - በሌላ የብቁነት ምርጫ ላይ መሠረት አድርጎ፤ ነገር ግን፣ ከ'ወንድምና እህት ምርጫ' ውጪ ሆኖ እንዲመደብ ይደረጋል።***

**እንዴት መጠየቅ ይቻላል (How to Claim):** በማመልከቻው ደረጃ 1 ላይ፣ በወንድምና እህት ምርጫ መረጃዎች ስር፣ "በDCPS እና/ወይም በቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ወንድምና እህት አላቸው ወይ" ለሚለው ጥያቄ፤ 'አዎ' ("Yes") መርጠው፤ የሚማረውን ወንድም ወይም እህት መረጃ ያስገቡ። በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር፣ ከአንድ በላይ ልጅ ካለዎት፣ የእያንዳንዱን ልጅ መረጃን፣ ከገጹ በታች የሚገኘውን "ወንድምና እህት መጨመሪ" ("Add Sibling") የሚለውን ሊንክ እየተጫኑ

**የተማሪ የመታወቂያ ቁጥሮች (ID)ን ማግኘት**

*Contact:* የወንድምና እህት (sibling) ትምህርት ቤቱን ማነጋገር።

የምዝገባ ቡድኑን በenroll@k12.dc.gov ወይም (202) 478-5738 ያነጋግሩ

*የ'My School DC'ን*

*በ*info.myschooldc@dc.gov ወይም በ(202)

ለሁሉም ማስገባትዎን እርግጠኛ ይሁኑ። በአሁኑ ወቅት ያሉ ተማሪዎች፣ ወንድምና እህት፤ የDCPS ተማሪ የመጣወቂያ ቁጥርም መቅረብ አለበት። ተማሪው የሚማር ከሆነ እና በወቅቱ የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር ከሌለው፤ እንደ ተማሪ መታቀቂያ ቁጥር እንዲያገለግል "0000000" (ሰባት 0'ዎች) ማስገባት – **ይህ ምርጫ ለክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ተማሪውን ለማስገባት ዕቅድ ላላቸው ወላጆች ብቻ ነው።** ከሎተሪው በፊት ይህ ምርጫ ተደርጎ እንደነበር ለማወቅ፣ በትምህርት ቤቱ የምዝገባ ክፍል (registrar) ጋር ወይም የምርጫ ሁኔታውን በሚያሳየው ገጽ ላይ መመልከቻውን ራሱን በመጠቀም ያረጋግጡ። ከሎተሪው በኋላ፣ እነዚህ ምርጫዎች ጥቅም ላይ የሚውሉት ታላቅ ወንድምና እህት በሚመዘገብበት ጊዜ ብቻ ነው።

### *ለወንድምና እህት-የቀረበ ምርጫ*

ለወንድምና እህት-የቀረበ ምርጫ (Sibling-offered preference)፣ ወንድምና እህቶቹ፣ በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ወንድምና እህት ላላቸው ተማሪዎች፣ የሚዛመዱ ናቸው።

> **ምሳሌ:** ጆን እና ወንድምና እህቶቹ በዚያው አንድ ዓይነት ትምህርት ቤቶች፣ የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻ አስገብተው ከሆነ እና ጆን በMy School DC ሎተሪ በኩል የተዛመደ ከሆነ፣ ለወንድምና እህት የተሰጠ (sibling-offered preference)፣ ለወንድምና እህቶቹ የMy School DC ሎተሪ ማመልከቻቸው እራሱ በራሱ አገልግሎት ላይ ይውላል።

**እንዴት መጠየቅ ይቻላል (How to Claim):** የወንድምና እህቱ - የ'My School DC' ማመልከቻ በአንድ የቤተሰብ የ'My School DC' አካውንት በኩል እስከገባ ድረስ፣ ምንም እርምጃ መውሰድ አያስፈልግም። ይህ ምርጫ እራሱ በራሱ በ'My School DC' ሎተሪ ማዛመጃ ሂደት መሰረት ይከናወናል። በትምህርት ቤቱ ቦታ የተሰጠው ወንድምና እህት ካልተመዘገበ፣ "ለወንድምና እህት የተሰጠ" ምርጫው፣ በዚያው ትምህርት ቤት ውስጥ ካመለከቱት ከሁሉም ወንድምና እህት ላይ ይሰረዛል። ይህም - ምናልባት የወንድምና እህትን የመዛመድ ዕድል እንዲያጡ፣ ወይም በዚያ ትምህርት ቤት ያላቸውን የተጠባባቂ ደረጃ ሊያወርደው ወይም ትምህርት ቤቱ ምዝገባውን ሊሽረው ይችላል። ወንድምና እህት በዚያው ትምህርት ቤት ተጠባባቂ ሆነው ይቆያሉ፣ ነገር ግን በዘፈቀደ (random) በሚሰጠው የሎተሪ ደረጃ ቁጥር መሰረት አዲስ የተጠባባቂ እና የሌላ ብቁ የሚሆኑባቸው ምርጫ ቦታ እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

### *በወንድምና እህት ምርጫ ላይ ልዩ የሆነ ማመልከቻ*

#### የ'Capitol Hill Cluster' ትምህርት ቤቶች (Peabody ES፣ Watkins ES፣ እና Stuart-Hobson MS)

ለዚህ ለሎተሪ አሰራር ሲባል፣ በማንኛውንም የ'Capitol Hill Cluster' ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሊገቡ ወይም የሚማሩ ወንድምና እህት ያለው ተማሪ፤ ወንድምና እህቶቹ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተመዝግበው እስከቆዩ ድረስ፣ በማንኛውም 'Cluster' ትምህርት ቤት ውስጥ፣ የወንድምና እህት ምርጫን ለመጠየቅ እና ብቁ ለመሆን ይችሉ-ይሆናሉ።

#### ሁለት ቋንቋ (Dual Language) የሚጠቀሙ/ፕሮግራሞች

ሁለት ቋንቋ (Dual language) የሚጠቀሙ/ፕሮግራሞች፣ በወንድምና እህት ምርጫው ላይ ለቋንቋ ማግኛ አገልግሎቱ እንግዳ ያልሆነ እና የታወቀ ስለሚሆን፣ ተጨማሪ ትኩረትን እንዲያገኝ ያደርጋል። ሆኖም፤ በነዚህ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች ምርጫ ወቅት፣ የወንድምና እህት ምርጫ (sibling preference)፣ ከክልል ወሰን ውስጥ ምርጫ (inboundary preference)፣ በበለጠ ሁኔታ ክብደት ይሰጠዋል።

- ሁለት ቋንቋ ያላቸው ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞችን ዝርዝር ለማግኘት ገጽ 35 ይመልከቱ።
- ሁለት ቋንቋ ያላቸው ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞችን፣ የተጠባባቂ ቅደም ተከተል ምርጫ ቻርትን ለማግኘት ገጽ 24 ይመልከቱ።

### የትምህርት ቤት በርካታ መንገዶች

በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ በሁለቱም በሁለት ቋንቋ እና ሁለት ቋና የሌላቸው ወይም በሞንተሶሪ እና ሞንተሶሪ ያልሆኑ መንገዶችን ተከትለው (Cleveland ES፣ Langdon ES፣ MacFarland MS፣ Marie Reed ES፣ Nalle ES፣ Powell ES፣ Roosevelt HS፣ ወይም Tyler ES) ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ ወንድምና እህታቸው፣ በዚያ ትምህርት ቤት የባህላዊው (traditional) ወይም በሁለት ቋንቋ/ሞንተሶሪ ፕሮግራም ውስጥ የሚማሩ ወንድምና እህት ምርጫ (sibling-attending preference)ን፣ በ'My School DC' ሎተሪ ውስጥ - ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ።

### ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች

- ወንድምና እህት ምርጫ፤ በተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (selective high schools) እና ፕሮግራሞች ውስጥ የሚሰጡ <u>አይደሉም</u>።
- ወንድምና እህት ምርጫ ባልተመረጡ ትምህርት ቤቶች እና ተባባሪ የሆኑ የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ፕሮግራሞች መካከል፤ ስማቸው: 'Columbia Heights Education Campus'፣ በ'Coolidge' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኘው፣ Early College Academy፣ 'McKinley Technology' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና 'School Without Walls' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - ውስጥ የሚሰጡ <u>አይደሉም</u>። ለምሳሌ፣ ተማሪው McKinley Technology High School ውስጥ ሲማር፣ ወንድምና እህቱ፣ በMcKinley Middle School፣ (the associated school) በሆነው ውስጥ፤ ወይም በተቃራኒው (vice versa)፤ የሎተሪ ምርጫ አይሰጣቸውም።
  - የተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች ዝርዝርን ለማግኘት ገጽ 35 ይመልከቱ።

### *የወንድምና እህት ምርጫዎች ማረጋገጫ*

የወንድምና እህት ምርጫ ማረጋገጫው፤ ከDCPS የምዝገባ ቡድን (Enrollment Team) ጋር በመተባበር - በትምህርት ቤቱ የሚረጋገጥ ይሆናል።

> **የወንድምና እህት ምርጫ ማረጋገጫ**
>
> *የምዝገባ ቡድኑን በ*enroll@k12.dc.gov *ወይም በ*(202) 478-5738 *ያነጋግሩ።*
>
> *የ'My School DC'ን በ*info.myschooldc@dc.gov *ወይም በ*(202) 888-6336 *የነጋግሩ።*

የ'My School DC' ሎተሪ ውጤቶቹ ከመገለጻቸው በፊት የወንድምና እህት ምርጫ ትክክለኛ ሆኖ <u>ካልተገኘ</u>፣ ምርጫው ከሎተሪ ምርጫው ውስጥ ይሰረዛ እና ቤተሰቦቹ በኢሜል (በMy School DC ማመልከቻቸው ውስጥ ኢሜል ካስቀመጡ) ይነገራቸዋል፤ ወይም ከትምህርት ቤቱ የሚደወል ስልክ (በ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻው ላይ ኢሜል ካልተሰጠ ብቻ) ተደውሎ ይነገራቸዋል። ተማሪው፣ የወንድምና እህት ምርጫ አግኝቶ ከነበረ እና ሕጋዊ-ሆኖ ካልተገኘ፤ ተማሪው በወንድምና እህት የመግባት ምርጫውን መልቀቅ እና፤ መዛመጃቸውን፣ የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እንዲገቡ፣ ወይም ከምዝገባው እንዲወጡ የሚያደርጋቸው እና ካለምንም ምርጫ በትምህርት ቤቱ የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እንዲመደቡ ያደርጋል። በተጨማሪም፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚማረው ተማሪ በሚቀጥለው ዓመት እንደገና ካልተመዘገበ፣ የሚያመለክተው ወንድም ወይም እህት፣ ምርጫውን እንዲቀማ የሚደረገው፤ በጊዜው የሚማር ወንድምና እህት ምርጫ ስለማያገኝ እና የማዛመጃ፣ የተጠባባቂነት ዕድል ወይም ከምዝገባው የመወገድ ሁኔታ ያጋጥመዋል። ይህ በሚሆን ጊዜ፣ አመልካቹ በሰፈቀደ በሚሰጠው የሎተሪ ቁጥሩ አማካኝነት በትምህርት ቤቱየተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እና

በሌላ ማንኛውም ከዚህ በፊት ብቁ ለሆኑበት ምርጫ ውስጥ እንዲገባ ይደርጋል፣ ነገር ግን የወንድምና እህት ምርጫውን ለማግኘት ብቁ አይሆንም።

## 3. የቅርብነት (Proximity) ምርጫ

**የቅርብነት (Proximity) ምርጫን መወሰን**
*የምዝገባ ቡድኑን በ*[enroll@k12.dc.gov](mailto:enroll@k12.dc.gov) *ወይም በ*(202) 478-5738 *ያነጋግሩ።*

ወደትምህርት ቤት የመጓጓዝን ሸክም ከወላጆች ላይ ለመቀነስ፣ DCPS በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት ለቤተሰቦች በPK3-5 ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች፣ በDCPS ትምህርት ቤቶች ዞን ውስጥ ያሉ፣ ከግማሽ ማይል በላይ ርቀት ከቤታቸው መጓዝ ላለባቸው፣ የቅርብነት ምርጫን ይሰጣል። እነዚህ ቤተሰቦች፣ በሁሉም የDCPS አጎራባች ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ከቤታቸው ከግማሽ ማይል የእግር መንገድ ርቀት በታች የሚገኙ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ በሎተሪ የቅርበት ምርጫ ያገኛሉ። የሚከተሉት የከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች የቅርበት ምርጫን አያካትቱም: የ'Capitol Hill Montessori @ Logan'፣ Dorothy Height፣ Excel Academy፣ በሚሊተሪ ሮድ (Military Road) ቅድመ መማሪያ ማዕከል፣ 'School-Within-School'፣ እና Stevens Early Learning Center።

በርካታ ካምፓሶች ላሏቸው ትምህርት ቤቶች፤ (Oyster-Adams, Peabody ES እና Watkins ES)፤ የቅርብነት (Proximity) ምርጫ የሚሰላው፣ በእያንዳንዱ ህንፃ ለየብቻ ሆኖ እንደ ተማሪው የክፍል ደረጃ እና አድራሻ ይሆናል። ለምሳሌ፤ በ'Peabody' የሚሰጥ የክፍል ደረጃን ውስጥ የቅርብነት (Proximity) ምርጫ የተመዘገበ ተማሪ፤ ውሳኔው በ'Peabody' የቦታ አቀማመጥ እንጂ በ'Watkins' የቦታ አቀመመጥ ላይ አይሆንም።

**እንዴት መጠየቅ ይቻላል (How to Claim):** ትምህርት ቤቱን በሎተሪ ማመልከቻዎ ላይ ደረጃ ከመስጠት ባሻገር ሌላ ምንም እርምጃ መውሰድ አያስፈልግም። ይህ ምርጫ፣ በMy School DC የሎተሪ ማመልከቻ ላይ፤ የቤት አድራሻ ላይ እና የክፍል ደረጃ (PK3-5) ላይ ተመርኩዞ፣ ራሱ በራሱ ይገባል። የቴክኖሎጂ ዋና ሹም ቢሮ (Office of the Chief Technology Officer (OCTO) የሚጠቀመውን፤ በማመልከቻው ከገባው አድራሻ ወደ አቅራቢያው ትምህርት ቤት በእግር የሚደረግ ጉዞን፣ በ'geographic information system (GIS)' ቴክኖሎጂ አማካኝነት በማስላት፣ ለቅርብነት ምርጫው ብቁ መሆንና አለመሆን ይወሰናል። ያስታውሱ የGIS ቴክኖሎጂ ከጉግል ማፕ (Google Maps) አንዳንድ ጊዜ ይለያል።

## ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- የተመደበላቸውን ቦታዎች ማግኘት

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ቦታዎች የሚቀመጡት፣ ስጋት ላይ ያሉ (at-risk) በሚል መስፈርት ውስጥ ተመድበው ለተለዩ የተቀመጠላቸው ይሆናል። በዚያ ምርጫ ውስጥ - ስጋት ላይ ያሉ (at-risk) የሚለው መለያ፣ የሚገረጎመው፤ አመልካቹን በ[proxy measures for at-risk status](#) ላይ፣ OSSE፤ ቢያንስ አንድ-ጊዜ መዝግቦታል ማለት ነው። እነዚህ መለኪያዎች ተማሪዎቹ፣ ቤት አልባ፣ በዲስትሪክቱ የማደጎ እንክብካቤ ዘዴ ውስጥ ያሉ፣ ወይም ለጊዜያዊ የችግረኛ ቤተሰቦች ድጋፍ (TANF) ወይም በተጨማሪ ተመጣጣኝ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (SNAP)ን የሚቀበሉ መሆኑን ያሳያል። ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- የተመደበላቸውን ቦታዎች ማግኘት፤ PK3 እና PK4 እና ከዚያ በታች ለሆኑ፤ በSY22-23 ተካፋይ የሆኑ ትምህርት ቤቶች ብቻ በስራ-ላይ ይውላል:

- አጎራባች (Neighborhood) ትምህርት ቤቶች: Barnard ES, HD Cooke ES, Garrison ES, Van Ness ES, John Lewis ES
  - ማስታወሻ: በአጎራባች (Neighborhood) ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- የተመደበላቸውን ቦታዎች ማግኘት፤ በክልል-ወሰን (in-boundary) ውስጥ ለሚኖሩ ብቁ-የሆኑ ተማሪዎች ብቻ የሚሰጥ ነው።
- ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች: Stevens ELC, Military Road ELC, Capitol Hill Montessori @ Logan, Dorothy I. Height ES

**እንዴት መጠየቅ ይቻላል (How to Claim):** ትምህርት ቤቱን በሎተሪ ማመልከቻ ላይ ደረጃ ከመስጠት እና ለ'My School DC' ብቁነታችሁን በፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- የተመደበላቸውን ቦታዎች ማግኘትን - ወደ ማመልከቻው ስትገቡ ለማረጋገጥ፣ የስምምነት መስጫውን ከማረጋገጥ ሌላ፣ መወሰድ የሚገባው ሌላ እርምጃ የለም። ቤተሰቡ፣ ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- የተመደበላቸውን ቦታዎችን ለማግኘት፤ ስምምነት መስጫውን አቅርቦ ከሆነ እና ብቁ ሆኖ ከተገኘ፤ ይህን ምርጫ የ'My School DC' ወዲያውኑ (automatically) ወደ አመልካቹ የሎተሪ ማመልከቻ እንዲገባ ያደርገዋል። ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- የተመደበላቸውን ቦታዎችን ለማግኘት - ብቁነታቸው-የሚወሰነው፣ በOSSE እና በሌላ የዲሲ መንግስት የመረጃ ስብስብ (data) ነው።

## ምርጫን መለወጥ (Preference Change)

ለምርጫው ብቁ ለመሆን አዲስ የሆኑ ቤተሰቦች ወይም ወይም የብቁነት ምርጫን በ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻቸው ላይ ያልጨመሩ፤ የሎተሪ ውጤቶቹ ከታወቁም በኋላ ቢሆን ምርጫቸው እንዲካተትላቸ የመጠየቅ መብት ሊኖራቸው ይችላል።

**እንዴት መጠየቅ ይቻላል (How to Claim):** ቤተሰቡ የምርጫ ለውጥ እንደፈለገ የሚያረጋግጥበትን መረጃ ማቀረብ ይኖርበታል። ከተረጋገጠ በኋላ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ከDCPS የምዝገባ ቡድን ( Enrollment Team) እና ከ'My School DC' ጋር በመስራት ምርጫው ወደ ሎተሪው ማመልከቻ እንዲገባ ያደርጋሉ። 'My School DC'፣ በዘፈቀደ (random) የሚሰጠውን የሎተሪ ቁጥር ላይ እና በተጨመረው ምርጫ ላይ በመመርኮዝ፣ አመልካቹን በተገቢው የተጠባባዊ ደረጃ ላይ ያስቀምጠዋል።

# የሎተሪ ውጤቶች

የ'My School DC' ሎተሪ፣ ብቸኛ፣ በዘፈቀደ (random) የሚወጣ ሎተሪ ሆኖ፤ ዓላማውም የሎተሪ ምርጫዎችን ባገናዘበ መልኩ፣ ተማሪዎችን ከመረጡት ትምህርት ቤቶች ጋር ማዛመድ ነው። ምንም እንኳን ቤተሰቦች እስከ 12 ትምህርት ቤቶችን ደረጃ መስጠትና ማመልከት ቢችሉም እንኳን፣ ሎተሪው ተማሪዎችን ከአንድ ባልበለጠ ትምህርት ቤት ውስጥ ያዛምዳል።

ለSY22-23፤ የ'My School DC' ሎተሪ ውጤቶቹ፣ ኤፕሪል (April) 1 ቀን 2022፣ መገኘት-የሚችል ይሆናል። ቤተሰቦች የ'My School C' የቤተሰብ አካውንት ውስጥ በመግባት የሎተሪ ውጤቶችን ማግኘት ይችላሉ። ቤተሰቦች፣ የሎተሪ ውጤቶቻቸውን በኢሜልም ሊያገኙ የሚችሉ፣ እና በኢሜል-ለመቀበል የተስማሙ (opt in ያደረጉ)፣ በማመልከቻው ላይ በተዘረዘረው አድራሻ አማካኝነት የውጤቶቹን ደብዳቤ - ውጤቶቹ ከተገለጹ አንድ ሣምንት በኋላ በኢሜል ይላክላቸዋል። ቤተሰቦች ላመመከቱት እያንዳንዱ ልጅ፤ ለየብቻ-የሆነ የተለያየ ደብዳቤ ያገኛሉ። ውጤቶቹን በኢሜል ያላገኙ ወይም ወደ 'My School DC' አካውንታቸው ለመግባት የተቸገሩ ቤተሰቦች፤ ስለ ውጤቶቹ ሁኔታ - ከኤፕሪል (April) 1 ቀን 2022 ጀምሮ፣ ወደ 'My School DC' አጣዳፊ-መስመር (Hotline)፣ በ (202) 888-6336፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:00am-5:00pm ባለው-ጊዜ ውስጥ - ደውለው ማግኘትም ይችላሉ።

በ'My School DC' ሎተሪ ውጤቶች ላይ ሶስት ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎች አሉት:

1. አንደኛ ደረጃ በተሰጠው ትምህርት ቤት ውስጥ መዛመድ፣ ግን በሌላ በማንኛውም ደረጃ በተሰጣቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተጠባባቂ ይሆናሉ።
2. አንደኛ ደረጃ ባልተሰጠው ትምህርት ቤት ውስጥ መዛመድ፣ ከተዛመደበት በላይ ከፍተኛ ደረጃ በተሰጣቸው ትምህርት ቤት ውስጥ ተጠባባቂ ይሆናሉ።
3. የትም ያልተዛመደ፣ በሁሉም ደረጃ ባላቸው ትምህርት ቤት ውስጥ ተጠባባቂ ይሆናል።

*ማስታወሻ፡* ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፣ ተጨማሪ ውጤቶችን ማግኘት ይችሉ ይሆናል። ገጽ 23ን ተመልከቱ።

## የመጀመሪያ ደረጃ በተሰጠው ትምህርት ቤት የተዛመዱ ተማሪዎች

አንደኛ ደረጃ በተሰጠው ትምህርት ቤት የተዛመዱ ተማሪዎች፣ በሌላ በማንኛውም ደረጃ ባላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተጠባባቂ አይሆኑም። የሎተሪ ቦታቸውን ዋስትና ለማግኘት፣ ከማለቂያው የመጨረሻ ቀን ከሆነው ከሰኞ፣ ሜይ (May) 2 ቀን 2022 በፊት፣ ቤተሰቦች - ተማሪዎቹን በተዛመዱበት ትምህርት ቤት ማስመዝገብ አለባቸው። ተማሪው ከተዛመደ በኋላ፣ በተዛመደበት ትምህርት ቤት ውስጥ ከማብቂያ የመጨረሻ ቀኑ በፊት ካልተመዘገ፣ ትምህርት ቤቱ ለተማሪው ቦታውን የመስጠት ግዴታ አይኖርበትም።

ከዚህ የሚጠበቀው፣ በማመልከቻቸው ላይ አነስተኛ ደረጃን ካስመዘገበ ትምህርት ቤት ጋር የተዛመዱ፣ ወንድምና እህት ያላቸውን አመልካቾች ብቻ ነው። ከተዛመዱ በኋላ፣ አመልካቹ በማንኛውም ወንድምና እህታቸው በተዛመዱበት ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ምንም ትምህርት ቤቱ እነሱ ከተዛምዱበት ያነሰ ደረጃ ቢኖረውም እንኳን፤ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እንዲቀመቱ ይደረጋል። በተባለው ማዛመቻን ለመቀበል ተማሪው ካልፈለገ፣ በወንድምና እህት ማዛመቻ ከሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ - በተጠባባቂነት ቦታ ውስጥ ይቆያል።

### *ከሎተራ-በኋላ (Post-Lottery) ማመልከቻዎች*

ተማሪው የመጀመሪያ ደረጃ ባለው ትምህርት ቤት በሎተሪ የተዛመደበትን ቦታ ካልወሰደ፣ በDCPS የክልል ወሰን ውስጥ (inboundary) ከ(K-12) አስገዳጅ ክፍሎች ትምህርት ቤቶች ውስጥ መመዝገብ ይችሉ ይሆናል። የሎተሪ ማመልከቻ ማስገቢያው የማብቂያ-ጊዜውን ካመለጣቸው ወይም ወደ ተጨማሪ ትምህርት ቤቶች ማመልከት ከፈለጉ፤ ቤተሰቦች፣ ከሎተሪ-በኋላ (Post-Lottery) ማመልከቻን በMySchoolDC.org ላይ ማስገባትም ይችላሉ።

## የመጀመሪያ ደረጃ ባልተሰጠው ትምህርት ቤት ውስጥ የተዛመዱ ተማሪዎች

በሎተሪ ማመልከቻቸው ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ከሌለው ትምህርት ቤት ጋር የተዛመዱ ተማሪዎች፣ ከተዛመዱበት የበለጠ ከፍተኛ ደረጃ የተሰጣቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሙሉ ተጠባባቂ ይሆናሉ። ተማሪዎቹ ከተዛመዱበት ትምህርት ቤት ያነሰ ደረጃ ካለው ማንኛውም ትምህርት ቤት ጋር ተጠባባቂ አይደረጉም።

ከዚህ የሚጠበቀው፣ በማመልከቻቸው ላይ አነስተኛ ደረጃን ካስመዘገበ ትምህርት ቤት ጋር የተዛመዱ፣ ወንድምና እህት ያላቸውን አመልካቾች ብቻ ነው። ከተዛመዱ በኋላ፣ አመልካቹ በማንኛውም ወንድምና እህታቸው በተዛመዱበት ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ምንም ትምህርት ቤቱ እነሱ ከተዛምዱበት ያነሰ ደረጃ ቢኖረውም እንኳን፤ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እንዲቀመቱ ይደረጋል።

*ማስታወሻ፡* ይህ ለተመረጡ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች ላይ አይሰራም። በገጽ 23 የሚገኘውን፣ በተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች የሎተሪ ውጤቶች የሚለውን ይመልከቱ።

በምዝገባ ማብቂያ የመጨረሻ ቀን፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያ ምርጫቸው ባይሆንም፣ ቦታውን ላለማጣት ሲባል፣ የተዛመዱ ቤተሰቦች፤ በተዛመዱበት ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲመዘገቡ ይበረታታሉ። በተዛመዱበት ትምህርት ቤት መመዝገብ፣ በሌላ ትምህርት ቤት ያላቸው የተጠባባቂነት ቦታ አደጋ ላይ አይጥለውም። ቤተሰቦች በተዛመዱበት ትምህርት ቤት ከተመዘገቡ በኋላ፣ ቆይቶ፣ ከተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ በሌላ ትምህርት ቤት ቢጠሩና ቢመዘገቡ፣ አሁን ከተመዘገቡበት ትምህርት ቤት እንዲሰረዙ ያደርጋቸዋል።

## ያልተዛመዱ ተማሪዎች

ከማንኛውም ትምህርት ቤት ጋር ያልተዛመዱ ተማሪዎች፣ አሁን ባሉበት ትምህርት ቤት የመቆየት መብት አላቸው፤ ወይም ደግሞ የመግባት መብት (right-to-attend) ባላቸው ትምህርት ቤት ውስጥ ከ(K-12) መመዝገብ

ይችላሉ። ያልተዛመዱ ተማሪዎች፣ በሎተሪ ማመልከቻቸው ላይ ደረጃ በሰጧቸው ትምህርት ቤቶች በሙሉ ተጠባባቂ ይሆናሉ። ወደ ተጨማሪ ትምህርት ቤቶችም፣ በ'My School DC' ከሎተሪ-በኋላ (Post-Lottery) ማመልከቻ አማካኝነት በwww.myschooldc.org/postlotto የማመልከትም አማራጭ አላቸው።

ሆኖም፣ ተማሪው፤ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች ውስጥ አመልክተው እና ተመራጭ (selective) ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራሙ(ሞቹ)፣ ተማሪው ብቁ ካላደረጉት፤ እነርሱ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ አይቀመጡም። በተጨማሪም፣ የሎተሪ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ፣ በ'My School DC' ከሎተሪ-በኋላ (Post-Lottery) በwww.myschooldc.org/postlotto ማመልከቻዎ በኩል፣ ተጨማሪ ለሆኑ ትምህርት ቤቶች የማመልከት ምርጫዎች ይሰጣቸዋል።

- ሊሆኑ የሚችሉ ሙሉ የሎተሪ ውጤቶች ዝርዝሮችን እና የሁኔታዎች መግለጫዎችን፣ በ myschooldc.org/faq/lottery-results-and-status-definitions ላይ ተመልከቱ።

## በተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች የሎተሪ ውጤቶች

በተመረጭ (selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም ለመመዝገብ ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ፣ የ'My School Dc'ሎተሪ ማመልከቻዎች መግባት አለባቸው፣ ሆኖም ግን፣ መግባት የሚቻለው በተወሰነ የመግቢያ ሂደቶ እና በተመረጡ መስፈርቶች አማካኝነት ይሆናል። ተማሪው በተመረጭ (selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን እና ፕሮግራምን ብቁ የመሆን መስፈርቶችን የማያሟላ ከሆነ፣ ተማሪው - ብቁ-ያልሆነ ተብሎ ምልክት ይደረግበታል። ብቁ-ያልሆኑ ተማሪዎች፣ ለዚያ ትምህርት ቤት ሊዛመዱ (matched) ወይም በተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ ሊገቡ አይችሉም።

- ተጨማሪ መረጃዎች በገጽ 35 ይመልከቱ።

# **ተጠባባቂ (Waitlist)**

የተጠባባቂ ዝርዝሮች ላይ፣ ቦታ እንደተገኘ ተማሪዎች የሚመዘገቡበትን ቅደም ተከተልን ያሳያል። በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ የተጠባባቂ ቅደም ተከተሎች፣ በሎተሪ ምርጫዎች እና የማመልከቻ ጊዜ (ሎተሪ እና ከሎተሪ-በኋላ)ን ተከትሎ ይከናወናል። የሎተሪ ማመልከቻዎች፣ የዘፈቀደ (random) የሎተሪ ቁጥራቸውን በመጠቀም እና ከሎተሪ-በኋላ (post-lottery) ደግሞ ማመልከቻውን ባስገቡበት ቀን መሠረት፣ የተጠባባቂ ቦታዎቻቸው ላይ በደረጃ የተጠባባቂ-ቦታቸው መሠረት እንዲቀመጡ ያደርጋል።

በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ተጠባባቂ ተማሪዎች፣ በምርጫቸው መሠረት ቡድን ይሰጣቸዋል:

- በአንድ ዓይነት የምርጫ ቡድን ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ባመለከቱበት ጊዜ-መሠረት፣ ደረጃ ይሰጣቸዋል (ይህም ማለት፤ ሎተሪ ወይም ከሎተሪ-በኋላ)።
- በአንድ አይነት የምርጫ ቡድን ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ሎተሪውን ባመለከቱበት ወቅት በዘፈቀደ (random) በተሰጣቸው የሎተሪ ቁጥር መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።
    - ስለምርጫዎች የአቀማመጥ ደረጃ (hierarchy) በገጽ 24 ይመልከቱ።
- ከሎተሪ-በኋላ (post-lottery)ን፣ (ከ9-12 ለሆኑ ክፍሎች፤ ከማክሰኞ ፌብሩዋሪ (February) 1, 2022 እና ከPK3-8 ለሆኑ ክፍሎች፤ እና ከማክሰኞ ማርች (March) 1 ቀን 2022 በኋላ) ያመለከቱ ተማሪዎች፣ ማመልከቻው በገባበት ጊዜና ቀን - ቅደም-ተከተል መሠረት፣ ተገቢው በሆነው የምርጫ ቡድን የመጨረሻ ክፍል ውስጥ ይጨመራል።

*ማስታወሻ:* በማመልከቻው ሁኔታ፣ ሌሎች አመልካቾች ለከፍተኛ ተመራጭ ክፍሎች ብቁ የሚያደርጋቸው ሁኔታ ሲፈጠር፣ የተማሪዎችን የተጠባባቂ ዝርዝርን ወደታች የማያወርዱ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በmyschooldc.org/faq/faqs#lottery፣ ላይ የበለጠ እወቁ።

**እንዴት መጠየቅ ይቻላል (How to Claim):** ቦታዎች በሚገኙ ጊዜ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኛው፣ በተጠባባቂነት እና በተጠባባቂ ቅደም ተከተሉ መሰረት፣ ቤተሰቦችን በኢሜል እና በስልክ ያነጋግራል። 'My School DC'ም እራሱ በራሱ የሚልክ የማስታወቂያ ኢሜል አማካኝነት፣ በማመልከቻው ላይ በተሞላው ማንኛውም ኢሜል ይልካል። የሎተሪ ቦታቸውን ለማረጋገጥ መመዝገብ ያለባቸው ከየትኛው የመጨረሻ ማብቂያ ገደብ ጊዜ በፊት እንደሆነ፣ ቤተሰቦች ይገለጽላቸዋል። ቤተሰቡ ምላሽ ካልሰጠ ወይም የምዝገባ ሂደቱን በተባለው የመጨረሻ ማብቂያ ጊዜ ካላደረገ፣ የተሰጠው ቦታ ይወጣና፣ ትምህርት ቤቱ በተጠባባቂነት በሚቀጥለው ደረጃ ላይ ለሚገኘው ተማሪ ቦታውን ይሰጣል። ከተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ የመጠራት ተስፋ ያላቸው ወላጆች፣ ትምህርት ቤቱ የሚጠቀመው የመገናኛ አድራሻ፣ በ'My School DC' ማመልከቻው ላይ የተሞላውን አድራሻ ስለሆነ፣ ወላጆች፣ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጣቸው ይጠቅማል። በማንኛውም ጊዜ አድራሻቸው ከተቀየረ፣ ቤተሰቦች የ'My School DC' አካውንታቸውን ወዲያው (immediately) ማስተካከል (update) ወይም 'My School DC'ን ማነጋገር ያስፈልጋቸዋል።

የሎተሪ-ቦታን ለማግኘት ሲባል፣ ቤተሰቦች የምዝገባ ወረቀቶችን፤ የዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫን ጨምሮ፣ በትምህርት ቤቱ በግንባር ቀርበው ማስገባት አለባቸው። ስለ ሎተሪ ምዝገባ መረጃ ለማግኘት ገጽ 29 ይመልከቱ።

በተጠባባቂነት የተሰጠ ቦታን ለመቀበል፣ የተለመደው የመጨረሻ ማብቂያ ቀን የጊዜ ገደብ፣ ማስታወቂያ ከደረሰበት፣ በአምስት (5) የስራ-ቀናት ውስጥ፣ የቀረበው-ቦታ ይሰጣል። ትምህርት ቤቶች ይህን የጊዜ ገደብ መጨመርም ሆነ መቀነስ የሚያስችላቸው ሙብት ሲኖራቸው፣ የትምህርት ክፍለጊዜ ከተጀመረ በኋላ እና ወደ-መጀመሪያ ጊዜ የማቅረብና ማሳጠርም ይችላሉ። ቤተሰቦች ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለጋቸው፣ በቀጥታ ከትምህርት ቤቱ ጋር መስራት አለባቸው። ብዙም ባልተለመደ ሁኔታ፣ የተጠባባቂ ቦታን ለማግኘት፣ የ24-ሰዓት ማስታወቂያ ከደረሳቸው በኋላ፣ ቤተሰቦች ኢሜል እና የስልክ ጥሪ ከትምህርት ቤቱ ይደርሳቸዋል።

## የተጠባባቂ ቅደም ተከተል በተመረጠ ትምህርት ቤቶች የተሰጠ ምርጫ/ፕሮግራሞች

ከዚህ በታች የሚታየው፣ የተጠባባቂነት ቅደም ተከተል፣ በተለምዶ እና ሁለት ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች ምርጫ ላይ የሚያሳይ ነው። ለሁለት ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች፣ በPK3 እና PK4 ምርጫዎች ላይ፣ በአንድ አኳያ፣ ከተለምዶ ትምህርት ቤቶች (traditional schools)/ፕሮግራሞች በተለየ ሁኔታ ቅደም ተከተል ተሰቶታል። ሁለት ቋንቋ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራም፣ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ወንድምና እህት አመልካቾች፤ ወንድምና እህት ከሌላቸው በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሚገኙ አመልካቾች ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል።

| **የተለምዶ (Traditional) ሎተሪ እና ከሎተሪ-በኋላ (Post-Lottery)** | **ሁለት ቋንቋ ሎተሪ እና ከሎተሪ-በኋላ (Post-Lottery)** |
|---|---|
| 1. የሚማር ወንድምና እህት ያላቸው በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) አመልካች (ለPK ብቻ) | 1. የሚማር ወንድምና እህት ያላቸው በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) አመልካች (ለPK ብቻ) |
| 2. ለወንድምና እህት የተሰጠው፣ በክልል ወሰን ውስጥ (inboundary) አመልካች (ለPK ብቻ) | 2. ለወንድምና እህት የተሰጠው፣ በክልል ወሰን ውስጥ (inboundary) አመልካች (ለPK ብቻ) |
| 3. በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) አመልካች (ወንድምና እህት የሌለው)፤ (ለPK ብቻ) | 3. የሚማር ወንድምና እህት ያላቸው፣ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አመልካች |

| | |
|---|---|
| 4. የሚማር ወንድምና እህት ያላቸው፣ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አመልካች | 4. ለወንድምና እህት የተሰጠው፣ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አመልካች |
| 5. ለወንድምና እህት የተሰጠው፣ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አመልካች | 5. በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) አመልካች (ወንድምና እህት የሌለው) |
| 6. የቅርብነት (Proximity) ምርጫ | 6. የቅርብነት (Proximity) ምርጫ |
| 7. ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አመልካች (ሌላ ምንም ምርጫ የሌለው) | 7. ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) አመልካች (ሌላ ምንም ምርጫ የሌለው) |

| **ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- ምደባ የተደረገላቸው ቦታዎች - በአጎራባች ትምህርት ቤቶች (በPK3 እና በPK4 ብቻ)** | **ፍትሃዊ-እኩልነት ባለው ሁኔታ- ምደባ የተደረገላቸው ቦታዎች - በከተማ-አቀፍ ትምህርት ቤቶች (በPK3 እና በPK4 ብቻ)** |
|---|---|
| 1. የሚማር ወንድምና እህት ያላቸው፣ በክልል ወሰን-ውስጥ (in-boundary) በአደጋ-ላይ (at-risk) ያሉ | 1. የሚማር ወንድምና እህት ያላቸው፣ በአደጋ-ላይ (at-risk) ያሉ |
| 2. ለወንድምና እህት የተሰጠው፣ በክልል-ወሰን ውስጥ (inboundary) በአደጋ-ላይ ያሉ | 2. የሚማር ወንድምና እህት ዕድል የሚሰጣቸው፣ በአደጋ-ላይ (at-risk) ያሉ |
| 3. በክልል-ወሰን ውስጥ በአደጋ-ላይ ያሉ (In-boundary at-risk) | 3. በአደጋ-ላይ (at-risk) ያሉ |

# መደበኛ በሆነ ምደባ መግባት

## ስለመደበኛ ምደባዎች

በDCPS ማዕከላዊ ቢሮ (Central Office) ለተማሪዎች በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች በመደበኛ ምደባ እንዲገቡ ብቁነትን የሚሰጣቸው፣ አራት ተርሞች (teams) አሉ: የልዩ-ትምህርት አሰጣጥ ክፍል (Division of Specialized Instruction (DSI)፣ ቅድመ-እርምጃዎች (Early Stages)፣ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division (LAD)፣ እና የተማሪ እርዳታ ቡድን (the Students Support Team (SST)፣ ናቸው። መደበኛ የሆነ ምደባን፣ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአደኛው-ውስጥ የሚያገኙ ተማሪዎች፤ የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻዎችን ለማስገባት አያስፈልጋቸውም።

## የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ምደባዎች ክፍል

DCPS የልዩ ትምህርት (special education) ሞዴል፣ ዲስትሪክት ለመሆን ይመኛል። ጉዳተኛ ልጅ፣ ዕድሜው ሃያ ሁለት (22) እስከሚሞላው እና እስከ ሴሚስተሩ መጨረሻ በልዩ ትምህርት ውስጥ እና ተመሳሳይ አገልግሎቶች ለመካፈል ብቁ ያደርገዋል። ከፍተኛ ጥራት ያለው ሁሉን ያቀፈ እና ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች ለመስጠት፣ እና የአካል ጉዳት ያላቸውን ልጆች የቀለም ትምህርት ውጤታማነትን ድንቅ በሆነ ሁኔታ ማሻሻል፣ የDCPS ዓላማ ነው።

ስለልጁ ጉዳተኝነት የሚገልጽ ማንኛውም መረጃ፣ ልጁ IEP ኖሮት ሆነም- አልሆነ፣ ይህን ጨምሮ፣ በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ለመመዝገብ ስለመቻሉ የሚወስን ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም። ስለመግቢያ ዘዴዎች መረጃዎችን በገጽ 8 ላይ እንባከዎን ይመልከቱ።

ከአጠቃላይ የትምህርት ስርዓቱ ውጪ፣ ከ20 ሰዓት ያነሰ ልዩ የትምህርት አሰጣጥ IEP የሚያስፈልገው ልጅ፣ አብዛኛዎቹ የDCPS ትምህርት ቤቶች፤ ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ፕሮግራሞችን

**የልዩ ትምህርት (Special Education) ጥያቄዎች**
የክፍሉን የልዩ ትምህርት አሰጣጥን ያነጋግሩ በ dcps.specialed@k12.dc.gov ያነጋግሩ።

በመስጠት፣ ልጁ የሚያስፈልገውን የIEP ግቦች ላይ እንዲደርስ እና ሁሉንም የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች እና እንክብካቤዎችን ይሰጣሉ። ልጁ እንደ ለልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ፕሮግራም በሚያስፈልገው ጊዜ፣ ለልጁ የልዩ ትምህርት የተዘጋጀ ክፍሎች (self-contained) ውስጥ ለመማር ቦታ አግኝቶ እድል እንደተሰጠው፤ የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ክፍሉ ያረጋግጣል።

## በአዲስ መልክ የተገኘ የልዩ ትምህርት-ብቁነት ለPK3 እና PK4 ተማሪዎች (የቅድሚያ ደረጃዎች ምደባዎች)

***የቅድሚያ ደረጃዎች* (Early Stages) *ጥያቄዎች***
በ(202) 698-8037 ወይም referrals@earlystagesdc.org ያነጋግሩ

የቅድሚያ ደረጃዎች (Early Stages)፣ ከ2 ዓመት-ከ8 ወራት እና በ5 ዓመት-ከ10 ወራት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ልጆችን የሚገመግም የDCPS ማዕከል ነው። የቅድሚያ ደረጃዎች (Early Stages)፣ ትምህርት ቤት ያልገቡ ልጆችን፣ የእድገት መፈተኛ እና የግምገማ ሂደቶችን በማካሄድ፣ ለልዩ ትምህርት እና ለሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ብቁ መሆን አለመሆናቸውን ይመለከታል።

የPK3/PK4 ልጆች በአዲስ ሁኔታ ለልዩ ትምህርት ብቁ ሆነው የተገኙ ልጆች፣ ወይም በአሁኑ ወቅት፣ ከዚህ በፊት የተከናወነ IEP ያላቸው እና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ እና፤ (1) እስከአሁን ተመዝግበው ካልሆነ፣ ወይም (2) አሁን ያሉበት የDCPS ትምህርት ቤት IEPን ማካሄድ ካልቻለ፤ በቅድሚያ ደረጃዎች (Early Stages) አማካኝነት፣ በትምህርት ቤቱ ቦታ እንዲያገኙ ይደረጋል። ይህ ሂደት ከ’My School DC’ ሎተሪ ውጪ ይሆናል። በማንኛውም ጊዜ፣ የሚሰጠው ቦታ በልጁ የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በሚገኝ ትምህርት ቤት ይሆናል። በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ውስጥ ቦታ ካልተገኘ፣ የሚሰጠው ቦታ ቤተሰቡ ከሚኖርበት ቅርብ የሆነ ትምህርት ቤት በሚገኝ ክፍት ቦታ ሆኖ፣ የIEP ሂደቱም የሚከናወንበት ቦታም ይሆናል። የቅድመ-እርምጃዎች (Early Stages) ምደባን፣ በተሰጠው-ትምህርት ቤት ውስጥ በመመዝገብ፣ ቤተሰቡ መቀበሉትን ያሳያል። ልጁ፣ በዚያ ትምህርት ቤት የ‘My School DC’ ሎተሪ ተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ ከነበረ፣ ከዚያ-ውስጥ እንዲወጡ ይደረጋል። የቅድመ-እርምጃዎች (Early Stages)ን ቦታ ተቀብሎ-መውሰድ፣ በሌላ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ልጁ ያለበትን የተጠባባቂ-ዝርዝር ቦታን፣ አያውከውም። በአንዳንድ-ሁኔታዎች፤ በPK3 የቅድሚያ-ቦታ የተሰጣቸው ልጆች፤ ምናልባት 3 ዓመት በሴፕቴምበር (September) 30 - የመጨረሻ-ቀን ሆኖ በተቀመጠው ጊዜ ላይሆናቸው ይችላል፤ ሆኖም ግን፣ የ‘IEP’ አገልግሎቶችን ማግኘት ስለሚችሉ፣ ለመመዝገብ መብት ይኖራቸዋል። እነዚህ ዓይነት ልጆች፤ በPK3 ውስጥ ለሚቀጥለው ዓመት እንደገና-የተመዘገቡ ናቸው።

## ከእንግሊዘኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ተማሪዎች (በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል ምደባዎች - Language Acquisition Division Placements)

በDCPS ምዝገባ ወቅት እና የቤት ውስጥ ቋንቋ የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎችን ካጠናቀቁ በኋላ፣ ከእንግሊዘኛ ሌላ እንደሚናገሩ ያሳወቁ ተማሪዎች፣ ወይም በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ከእንግሊዘኛ ሌላ ቋንቋን እንዲያውቁ የተደረጉ ልጆች፤ ወደ ‘በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (LAD) – ‘የእንኳን ደህና መጣችሁ ማዕከል’ መጥተው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታቸው እንዲፈተን ተመርተዋል። ከዚህ በፊት ከአሜሪካ ውጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች እና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ዓይነቶችን ያጠናቀቁ፣ የDCPS የምረቃ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ወደ ‘LAD – ‘የእንኳን ደህና መጣችሁ ማዕከል’ እንዲመሩና እንዲገመገሙ ይደረጋል። የLAD – ‘የእንኳን ደህና መጣችሁ ማዕከል - ሊካፈሉ የሚችሉ የ‘EL’ ተማሪዎችን በመፈተን፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ (English as Second

Language (ESL) ብቁነታቸውን ለመወሰን፣ ለESL አስተማሪዎች ምክሮችን ለመስጠት እና የክፍል ደረጃን ለመመደብ፣ የቋንቋ እና የባህል ስብጥር ያላቸው ቤተሰቦችን ለማስተማር፣ ወደ ማህበረሰብን ማዕከል ያደረጉ ድርጅቶች በመምራትና ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት እንዲያገኙ፣ የውጪ ሃገር የትምህርት መረጃዎቻቸው እንዲመዘኑ ሃሳብ-ያቀርባል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ ድህረ-ገጾችንን መጎብኘት እና/ወይም፤ ራኬል ኦርቲዝ (Raquel Ortiz) በraquel.ortiz@k12.dc.gov አነጋግሩ።

## የተማሪ ምደባ ቢሮ ዝውውሮች

የDCPS የተማሪ እርዳታ ሰጪ ቡድን፣ መደበኛ በሆነው የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) እና የሎተሪ የምዝገባ ሂደቶች ውጪ፣ ልዩ ሁኔታዎች በሚከሰቱ ጊዜ፣ ለተማሪዎች የትምህርት ቤት ምደባዎችን በማፈላለግ ከተማሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር ይሰራል። በተማሪ እርዳታ ሰጪ ቡድን የሚታገዙ ሁሉንም ተማሪዎች፣ ሕጋዊ የሆነ የምደባ ማስታወቂያ በአባሪነት ይሰጣቸዋል። የተማሪ እርዳታ ሰጪ ቡድን፣ ለተማሪዎች የምዝገባ እርዳታ እና ምደባ በሚካሄድበት ጊዜ፣ የሚከተሉት ኢጋጣሚዎች፣ ተፅዕኖ ከፈጠሩባቸው በሚል እና ተጨማሪ መረጃዎችን ስለ ምደባዎች ያቀርባል። ስለማንኛውም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ምደባዎች ጥያቄዎች ካለዎት፣ የተማሪ እርዳታ ሰጪ ቡድንን ያነጋግሩ።

**የተማሪ ምደባ ቢሮ**
3535 V Street, NE
Washington, DC 20018
በ(202) 939-2004 ወይም
Student.Placement@k12.dc.gov
ያነጋግሩ

1. በ'Supervision of the Family Court Social Services Division (FCSSD)' ስር የሚገኘው፣ ለDepartment of Youth Rehabilitation Services (DYRS) የወጣት ትጉህነት
2. በ'Child & Family Services Administration (CFSA)' ቁጥጥር ስር የሚገኙ ልጆች
3. በፍላጎት የሚደረግ ከክልል ወሰን ውጪ (Out-of-Boundary) ዝውውር
4. በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የተፈናቀሉ ቤተሰቦች
5. የወታደራዊ ቤተሰብ ልጆች
6. የጉዳት ሰለባዎች (Victim)፣ ካለፈቃደኝነት (Involuntary)፣ እና ወዲያውኑ መዛወሮችን (ለደህንነት)
7. የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎች (የዲሲ ሴፍ የተጎጂ ምርመራ ፕሮጀክት - DC SAFE Lethality Assessment Project)
8. የኮሎምብያ ዲስትሪክት የከንቲባ ቢሮ፣ ለሰለባዎች (Victim) አገልግሎት ሰጪ
9. ወጣት እና ዕድል አካዳሚ መምሪያ ሂደት ዘርግቷል።
10. ሁለት ቋንቋ ያልሆነ (Non-Dual Language) አማራጭ ትምህርት ቤት ምደባ (እህት ትምህርት ቤት/Sister School)
11. ቤት አልባ የሆኑ ልጆች እና ወጣቶች ድጋፎች መስጫ ፕሮግራም

### *በራስ ውሣኔ የሚደረግ፣ ከክልል ወሰን ውጪ ዝውውሮች*

የDCPS ቻንስለር በፍላጎት የሚደረግ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ዝውውርን፣ እጅግ በጣም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ ለተማሪው/ዋ የመፍቀድ ስልጣኑን መጠቀም ይችላል። ስለዚህ ሂደት እና ሊታዩ የሚችሉ መስፈርቶች እና በፍላጎት የሚደረግ ከክልል ወሰን ውጪ (Out-of-Boundary) ዝውውር፣ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ ሙሉ የፖሊሲ ምርመራውን dcps.dc.gov/node/1253426ይመልከቱ።

### *የማደጎ እንክብካቤ ውስጥ/Foster Care ያሉ ልጆች (የዲሲ የልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎቶች አስተዳደር/DC Child & Family Services Administration)*

በዲሲ የልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎቶች አስተዳደር (e DC Child & Family Services Administration (CFSA) ውስጥ፣ በማደጎ-እንክብካቤ እና ጥበቃ ውስጥ ያሉ ልጆች እና ወጣቶች፤ ከዲሲ፣ ሜሪላንድ ወይም ቨርጅኒያ ውጪ-የሆነ አቀማመጥ ባለው የማደጎ-እንክብካቤ ውስጥ በጊዜያዊነት የመመደብ ሁኔታዎች በሚገጥሟቸው ጊዜ ጨምሮ፤

የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች የሆኑ እና በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመመዝገብ እና ለመማር መብት አላቸው። ስለ ማደጎ-እንክብካቤ ውስጥ ላሉ ወጣቶች፣ እና ስለ 'My School DC' ሎተሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁን፣ በ[www.myschooldc.org/faq/faqs](http://www.myschooldc.org/faq/faqs) ላይ ጎብኙ።

- በማደጎ-እንክብካቤ ውስጥ ያለ ልጅ፤ መጀመሪያ በነበረበት ትምህርት ቤት ውስጥ - ይህ መጀመሪያ የነበረበት (origin) ትምህርት ቤት ውስጥ መቆየታቸው-ለእነሱ በሚፈልጉት ሁኔታ ተመራጭ እንዳልሆነ ካልተወሰነ በስተቀር፤ የመቆየት መብትም አላቸው። እነዚህ ተማሪዎች፤ ለእነሱ ተመራጭ ሆኖ የሚፈልጉት (best interest) መሆኑን የሚወስኑበትን እና ምዝገባዎች[7] ላይ እርዳታን ለማግኘት፣ ወደ የተማሪ ምደባ ቢሮ (Student Placement Office) ይመራሉ። አሳዳጊ ቤተሰቦች (Foster families) ወይም የማህበረሰ ሠራተኞች (social workers)፤ የተማሪ እርዳታ ቡድኑን በ (202) 939-2004 ወይም በ[student.placement@k12.dc.gov](mailto:student.placement@k12.dc.gov) እርዳታ ለማግኘት ማነጋገር ይችላሉ።

## *የወታደር ቤተሰቦች (Military Families)*

ለትምህርት ዕሜያቸው የደረሰ የወታደራዊ ቤተሰቦች ልጆች፣ በትምህርታቸው ስኬት ለማምጣት፣ በተደጋጋሚ ከቦታ-ወደ ቦታ መዘዋወራቸው እና አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቤተሰብ አባላቶቻቸው ለወታደራዊ አገልግሎት በመሰማራታቸው ምክንያት ችግሮች ይገጥማቸዋል። ከK-12 ክፍሎች ለመመዝገብ ብቁ የሆኑ እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ - እንደ 'Joint Base Anacostia-Bolling'፣ 'Fort McNair'፣ እና 'Marine Barracks Washington DC'፣ ተብለው በሚጠሩ በወታደራዊ ተቋማት ውስጥ የሚኖሩ፣ የወታደራዊ ቤተሰብ ልጆች፤ በሚመርጡት የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በማንኛውም የትምህርት ዓመት ወቅት፣ ክፍለጊዜው/ፕሮግራሙ የሚገኝበት-ሁኔታ እስካለ-ድረስ፣ እና ማንኛውንም የመግቢያ መስፈርትን ተከትለው፣ መመዝገብ ይችላሉ።

- ➢ በወታደራዊ ቤተሰቦች ምዝገባ እና ምደባን በተመለከተ፣ የቻንስለር መመሪያን (Chancellor's Directive) በ: [dcps.dc.gov/page/enrollment-students-military-families](https://dcps.dc.gov/page/enrollment-students-military-families) ያንብቡ።

ከዚህ በላይ በተጠቆሙት ወታደራዊ ተቋማት ውስጥ ከሚኖሩ ተማሪዎች በተጨማሪ፣ DCPS ሁሉንም የወታደራዊ ቤተሰቦች ተማሪዎችን፣ በምዝገባ እና በትምህርት ቤት አድራሻ ውሳኔዎች ይረዳል። በDCPS ውስጥ ለመመዝገብ እርዳታን የሚፈልጉ ወታደራዊ ቤተሰቦች፣ እባክዎን የተማሪ እርዳታ ሰጪ ቡድኑን በ(202) 939-2004 ወይም በ [student.placement@k12.dc.gov](mailto:student.placement@k12.dc.gov) ያነጋግሩ።

## *ቤት አልባነት (Homelessness)*

በ'McKinney-Vento' የቤት አልባነት ትምህርት እገዛ ድንጋጌ፣ ("McKinney-Vento")፤ የተሻሻለው የ2015ቱ፣ የሁሉም ተማሪ ስኬት ድንጋጌ ("ESSA")፣ ትምህርት የማግኘት መብቶችን ዋስትና መስጠት እና ቤት አልባነት ለገጠባቸው[8] ተማሪዎች እርዳታዎችን ይሰጣል። McKinney-Vento፤ "ቤት አልባ ልጆች እና ወጣት" የሚለውን ትርጓሜ ሲያብራራ፣ ልጆች እና ወጣቶችን ጨምሮ፣ ቋሚ፣ መደበኛ፣ እና በቂ የሆነ የሌሊት ማደሪያ፣ የሌላቸው ግለሰቦች ሆነው፣ በሚከተሉት ሁኔታ ያሉ፡

- **መዳበል (Doubled Up) –** መኖሪያውን በማጣት፣ በኢኮኖሚ ክብደት የተነሳ፣ ወይም ተመሳሳይ ምክንያት፤ የሌላ ሰውን መኖሪያ ቤት በመጋራት የሚኖር፣
- **በሆቴሎች/ሞቴሎች የሚኖሩ –** በቂ የሆነ የመጠለያ አማራጭን በማጣት ምክንያት፣ በሞቴሎች፣ ሆቴሎች፣ ተሳቢ ማቆሚያዎች፣ ወይም በድንኳን መጠለያ ስፍራዎች የሚኖር፣
- **በመጠለያ (Sheltered) ውስጥ –** በድንገተኛ ወይም በሽግግር መጠለያዎች፣ ወይም ማንም የማይገለገልበት የተለቀቀ ሆስፒታሎች ውስጥ የሚኖር፣

---

[7] For more information about education stability for children in foster care, please see OSSE and CFSA's joint guidance available at [https://osse.dc.gov/publication/osse-and-cfsa-issue-joint-essa-foster-care-guidance-leas](https://osse.dc.gov/publication/osse-and-cfsa-issue-joint-essa-foster-care-guidance-leas).
[8] 42 U.S.C. 11431 et seq.

- **መጠለያ የሌለው (Unsheltered) –** *ተቀዳሚ የሆነ የግል ወይም የሕዝብ የሌሊት ጊዜ ማደሪያ/መኖሪያ ቦታ እንዲያገኝ ሆኖ፣ ለሰው ልጅ የመደበኛ የእንቅልፍ ጊዜ መቆያነት ሆኖ ያልተቀረፀ፣ ወይም በመኪናዎች ውስጥ፣ በፓርኮች፣ በሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ ማንም የማይኖርበት የተለቀቀ ህንፃዎች፣ ደረጃውን ያልጠበቁ መኖሪያዎች፣ አውቶቡስ ወይም ባቡር ጣቢያዎች፣ ወይም ተመሳሳይ አቀማመጥ ያላቸው ቦታዎች ውስጥ መኖር፣*

- **ከማንም ጋር የማይኖር ወጣት (Unaccompanied Youth) –** በወላጅ/አሳዳጊ የአካል ሞግዚትነት የማይኖር ወጣት፣ እና ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች በማንኛቸውም አኳሃን በመኖራቸው ምክንያት፣ ቤት አልባ ተብሎ ሊመደብ የሚችል፣ እና

- **ፍልሰት (Migratory) –** በፍልሰት ላይ ያሉ ልጆች፣ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች በማንኛቸውም አኳሃን በመኖራቸው ምክንያት፣ ቤት አልባ ተብሎው ሊመደቡ የሚችሉ፤

'McKinney-Vento' *መሠረት፣ ቤት አልባነት የገጠባቸው ተማሪዎች፣* የሚከተሉት የምዝገባ መብቶች አሏቸው:

1. ***<u>መጀመሪያ በነበሩበት ትምህርት ቤታቸው (school of origin)</u> የመቆየት መብት።***

   *መጀመሪያ የነበሩበት ትምህርት ቤት* (school of origin) *ማለት፣ "ልጁ ወይም ወጣቱ ቋሚ የሆነ መኖሪያ በነበረው ጊዜ የነበረበት ትምህርት ቤት ወይም በመጨረሻ ይማርበት የነበረው ትምህርት ቤት፣ ቅድመ-ትምህርት ቤትን ጨምሮ ማለት ነው"። ተማሪው ለመማር መብት ባለው ትምህርት ቤት ውስጥ በአጠቃላይ የቤት አልባ ሆኖ በቆየበት ጊዜ ውስጥ የመማር መብት አለው።*

2. **<u>በክልል ወሰን ውስጥ ባለ ትምህርት ቤት</u> ውስጥ *<u>ወዲያውኑ የመመዝገብ</u> መብት።***

   *ወላጅ/አሳዳጊ/ከማንም ጋር የማይኖር* (unaccompanied) *ወጣት፣* ከጊዜያዊ *መኖሪያ/ምደባ ቦታቸው* በቅርበት በሚገኝ የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ የሕዝብ ትምህርት *ለመመዝገብ መጠየቅ ይችላል። ወዲያውኑ የመመዝገብ መብት* እስከ በክልል ውስጥ (in-boundary) የሚገኙ *አጎራቦች ትምህርት ቤቶች ብቻ ሊሰፋ ይችላል፤ ሆኖም ግን ወደ* ከተማአቀፍ እና የተመረጡ ትምህርት ቤቶች፣ *መራዘም አይችልም።*

*በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ የቤት አልባነት ያጋጠመው ተማሪ፣ መጀመሪያ* በነበረበት ትምህርት ቤት (school of origin) ወይም በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ሳይሆን፣ በሌላ ትምህርት ቤት እንዲገባ ሊደረግ ይችል ይሆናል። ይህን መሰል ምደባ፣ በመልካም ፍላጎት ላይ የተመሰረተ (best interest) ምደባ ተብሎ ሊቆጠር የሚችል እና በDCPS የቤት አልባነት ግንኙነት (Liaison) እና የሚመለከታቸው የትምህርት አሰጣጥ የበላይ ተቆጣጣሪዎች የሚወሰን ይሆናል። በመልካም ፍላጎት ላይ የተመሰረተ (best interest) ምደባ፣ በልጁ ወይም ወጣቱ የደህንነት ጥበቃ በሚያስፈልገው የልዩ ትምህርት ሁኔታዎች፣ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት/አለመገኘት ላይ ባለ ስጋቶች የተነሳ፣ እና በትምህርት ቤቱ የወንድምና እህት ምደባ ሁኔታ ይወሰናል።

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የተመደበ የቤት አልባነት ግንኙነት (Liaison (SBHL)፣ በተማሪዎች ላይ የቤት አልባነት በሚያጋጥም ጊዜ እርዳታ ያደርጋሉ። የግንኙነት ክፍሉ (liaison) በሚከተሉት ሊረዳ ይችላል:

- *ወዲያውኑ መመዝገብ፣*
- *የምዝገባ አለመግባባቶችን መፍታት፣*
- *የወላጅ የተሳትፎ ዕድሎች እና ከማህበረሰብ የመረጃ ምንጮች ጋር ግንኙነት መፍጠር፣*
- ቤት-አልባ ተማሪዎችን እና ወላጆች ከትምህርት አገልግሎቶች እና ሌሎች የመረጃ ምንጮች ጋር ማገናኘት (ለምሳሌ፤ የመጓጓዣ እና የትምህርት ቤት ልብስ (uniform) እገዛዎች)፣ እና
- በቅድሚያ የተሰጠ (Head Start)፣ በቅድሚያ ለማስተካከል የተጀመረ (IDEA Part C) እና ሌሎች የቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞችን ጨምሮ፣ - ልጆችን፣ ከማንም ጋር የማይኖር ወጣት፣ እና ቤተሰቦች፤ ብቁ ከሆኑበት የትምህርት አገልግሎት መስጫ ሄደው፣ እንዲገለገሉ የሚያስችል፤

መጀመሪያ የነበሩበት ትምህርት ቤት (school of origin) እና/ወይም በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤቶች፤ የቤት አልባነት ተሞክሮ የገጠማቸውን ልጆችን እና ወጣቶችን ወዲያውኑ መመዝገብ እና በተለምዶ መቅረብ የሚገባቸው የምዝገባ መረጃዎች (የልደት ሰተፊኬቶች፣ የክትባት መዝገቦችን፣ ወዘተ) ማቅረብ ባይችሉም እንኳን፣ ብቁ ለሆኑበት የትምህርት እና ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ሊቀርቡ-የሚችሉ ሰነዶች (Documents)፤ ነገር ግን መስፈርቶች ያልሆኑ - የሚያካትተው:

- የምደባ ደብዳቤ ከVirginia Williams Family Resource Center ወይም ቤተሰቦች በጊዜአዊነት ከሚኖሩበት መጠለያ፣ ወይም
- የተፈረመ ደብዳቤ፣ ቤተሰቡ በጊዜአዊነት አብረውት ከሚኖሩት ግለሰብ፤ ወላጅ/አሳዳጊ እና ልጆቻቸው በእነርሱ አድራሻ በጊዜአዊነት እንደሚኖሩ የሚጠቅስ ደብዳቤ። ይህ ከማንም ጋር የማይኖር (unaccompanied) ወጣትም፣ ይህን እንደ አማራጭ ሊያቀርቡት ይችላሉ።

የቤት አልባነት ተሞክሮ የገጠማቸው ተማሪዎች፣ የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫን ማቅረብ ካልቻሉ፣ ምዝገባ እና በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በሚገኝ ትምህርት ቤታቸው ውስጥ መግባት ሊከለከሉ አይችሉም። ማንኛውም የጎደሉ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ትምህርት ቤቱ ከተማሪ እና ቤተሰብ ጋር አብሮ ሊሠራ ይችላል። በዚያ ወቅት ውስጥ፣ ተማሪው ትምህርት ቤት መግባት ይችላል። መረጃዎቹ ከታረሙ በኋላ፣ ምናልባት በአሁኑ ወቅት፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary ) በሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዳይማር ሊወሰን ስለሚችል፣ ይህ በሚሆን ጊዜ ተማሪው ወደ ክልል ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤታቸው ወይም ወደ መጀመሪያ የነበረበት ትምህርት ቤታቸው (school of origin)፣ ወይም ወደ ሌላ ትምህርት ቤቶች፤ በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት እንዲመዘገቡ ይመራሉ።

ቤተሰቡ፣ ተማሪው መጀመሪያ የነበረበት ትምህርት ቤት (school of origin) ወይም በክልል ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ነው ብለው ባመኑበት ትምህርት ቤት ውስጥ እንዳይመዘገብ ከተከለከለ፣ ትምህርት ቤቱ የOSSEን የ'McKinney-Vento' ድንጋጌ - የአለመግባባት መፍቻ ፖሊሲና መመሪያዎችን (OSSE's McKinney-Vento Act Dispute Resolution Policy and GuidelinesDispute Resolution Policy and Guidelines)፣ ለቤተሰቦቹ መስጠት አለበት። በትምህርት ቤቱ ተቀማጭ የሆነው የቤት አልባነት ግንኙነት (Liaison)፣ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ወጣት፤ በውሳኔው ላይ አቤቱታ ማቅረቢያ መብትን ጨምሮ፣ ስለትምህርት ቤት ምርጫ እና ምዝገባ፣ ትምህርት ቤቱ የወሰነውን የጽሁፍ-ማብራሪያ መስጠት አለበት። የአለመግባባት መፍትሄ መመሪያዎች በ: OSSE Dispute Resolution Guidelines ላይ ለማግኘት፣ ወይም የ'DCPS Homeless Children Youth Services' ድህረ-ገጽን፣ በdcps.dc.gov/service/homeless-children-and-youth-services-dcps ላይ መገኘት ይችላል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ እባክዎን በ'DCPS Homeless Children and Youth Program'ን በdcps.hcyp@k12.dc.gov ላይ፣ ወይም በ(202) 576-9502 ያነጋግሩ።

ከዚህ በላይ ከተገለጹት ምደባዎች ጋር የተያያዙ ማንኛውም ጥያቄዎች ካለዎት፣ የDCPS የተማሪ እርዳታ ቡድን ዳይሬክተር የሆኑትን - ሚሎ ኤ. ሆዋርድ (Milo A. Howard)ን በ202) 270.6182 ወይም (በኢሜል: milo.howard@k12.dc.gov) እባክዎን ያነጋግሩ።

## ምዝገባ (Enrollment)

በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ምዝገባን ለማጠናቀቅ፣ ቤተሰቦች ተሞልቶ የተጠናቀቀ የምዝገባ ጥራዝ (packet) በግንባር በመቅረብ ለትምህርት ቤቱ ማስገባት እና ሁሉንም የብቁነት ቅድመ-ሁኔታዎችን፤ እንደ - በOSSE ቅድመ-ሁኔታዎችን[9] መሠረት ያደረገ፣ የዲሲ ነዋሪ መሆንን የሚያረጋግጥ፣ በቂ የሆነ መረጃን ጨምሮ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። DCPS ሁሉም ቤተሰቦች፣ **በተመዘገቡ በ10 የቀን መቁጠሪያ (ካላንደር) ቀን ውስጥ** የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫቸውን እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። በዚህ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የዲስትሪክቱ ነዋሪ መሆናቸውን ማረጋገጫ ማቅረብ ካልቻሉ፣ በቂ የሆነ

[9] 5-E DCMR § 2000.1

መረጃዎች እስከሚያቀርቡ ድረስ፣ DCPS እንዳይገቡ ይታገዳሉ። ተመድቦ-በተቀመጠው ‘CBO’ ውስጥ የግል-ምዝገባን ሳይጨምር፤ በሁለት ትምህርት ቤቶች በአንድ-ጊዜ (simultaneously) ተማሪው መመዝገብ የማይችል-ሊሆን ይችላል። አንድ-ጊዜ አንድ-ተማሪ በአዲስ ትምህርት ቤት ውስጥ ከተመዘገበ በኋላ፤ ከቀድሞ-ትምህርት ቤታቸው ጋር የነበረውን አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፈውን (feeder pattern) የማግኘት ዕድሉን ሊያጣ ይችላል። ይህ የሚሆነው፣ ተማሪው በ‘My School DC’ ሎተሪ አማካኝነት - ወደ ቀድሞው ትምህርት ቤት በሚገባበት-ጊዜ ብቻ ነው። በማንኛውም-ጊዜ፤ ተማሪዎች በክልል-ወሰን (in-boundary) ትምህርት ቤታቸው ውስጥ ሊመዘገቡ ይችላሉ።

- የDCPS የምዝገባ ጥራዝ (packet) እዚህ ዳውንሎድ (download) በማድረግ አጠናቀው ያስገቡ: EnrollDCPS.dc.gov

## የሎተሪ ምዝገባ

ተማሪው በክልል ወሰናቸው ውስጥ (in-boundary) እና/ወይም አዘዋዋሪ (K-12) ትምህርት ቤት፣ ውስጥ ካልተመዘገበ፣ እና አሁን በሚማርበት ትምህርት ቤት በድጋሚ መመዝገብ፣ በ‘Opportunity Academy’ ምደባዎች ተጨማሪ መረጃዎችን በገጽ 32 ‘Opportunity Academy’ ውስጥ፣ ወይም በመደበኛ ምደባ አማካኝነት የተመዘገቡ ካልሆነ፣ (ስለመደበኛ የተማሪ ምደባዎች ተጨማሪ መረጃዎችን በገጽ 24 ይመልከቱ) በ’My School DC’ ሎተሪ በኩል ተዛማጅነትን ማግኘት አለባቸው። በሎተሪ-በተዛመደ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመመዝገብ፣ ቤተሰቦች የሚፈለገውን የምዝገባ ቅጾች ወደ ትምህርት ቤቱ በማቅረብ እና የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫን፤ ከሎተሪ የምዝገባው ቀን-ማብቂያ ከሆነው - (ሰኞ፣ ሜይ/May 2 ቀን 2022) በፊት ማስገባት አለባቸው። ከሎተሪው ማብቂያ የመጨረሻ ቀን በኋላ፣ ትምህርት ቤቶች በሎተሪ የተዛመዱ ተማሪዎችን መመዝገብ ግዴታ የለባቸው፤ በመሆኑም፣ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ቀሪውን ቦታ እንዲያገኙ መስጠት ይጀምሩ ይሆናል።

ከምዝግባ ሰነዶቹ በተጨማሪ፣ በሎተሪ ቦታ ያገኘው ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ፣ በማመልከቻ ጥራዙ (enrollment packet) ውስጥ የሚገኘውን - የ’My School DC’ ቦታው መቀበያ ማስታወቂያውን ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ማቅረብ ይኖርበታል። በዚህ መረጃ ላይ ስምምነትን በመግለጽ፣ እና ወደ ሎተሪ ማዛመጃው ትምህርት ቤት በመመዝገብ፤ የተማሪው በወቅቱ ያለው በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ውስጥ ካልሆነና፣ ለመጪው የትምህርት ዓመት፣ ተማሪው/ዋ አሁኑ ወቅት ያለውን/ላትን ትምህርት ቤት፣ እና በአሁኑ ወቅት ያለውን/ላትን አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላፍን (feeder pattern) እንደተወ/ች፤ ወላጆች የሚያረጋግጡበት ነው። እንደ ማስታወሻነት፤ በሌላ የLEA ትምህርት ቤት ውስጥ በአንድ-ላይ የተደረገ (simultaneously) ምዝገባ ካለ፣ ወይም ተማሪዎች በአንድ-ላይ (simultaneously) ከአንድ-በላይ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ መመዝገብ የማችሉ ሲሆን፤ ተማሪዎች በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ መመዝገብ የማይችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በተጨማሪም፣ አንድ ጊዜ ተማሪው ከክልል ወሰን ውጪ ትምህርት ቤት ለቅቆ ወደሌላ በሎተሪ የተዛመደበት ትምህርት ቤት በDCPS ወይም በቻርተር፣ ወይም የግል (private)፣ በመኖሪያ ቤት ትምህርት ቤት (homeschool)፣ ወይም ማንኛውም ሌላ ትምህርት ቤት ውስጥ ከተገባ፤ ወደቀድሞው የክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ትምህርት ቤታቸው ለመመለስ ከፈለጉ፣ በ‘My School DC’ ሎተሪ አማካኝነት እንደገና ማመልከት ያስፈልጋቸዋል። ሆኖም ግን፣ ተማሪው በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከK-12 ክፍሎች ገብቶ የመማር መብቱ ምንግዜም ቢሆን የተጠበቀ ነው።

## የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎች

በDCPS ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ቤተሰብ፣ እንደምዝገባ ሂደት አንዱ አካል በመሆን፣ የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫን በየዓመቱ ማቅረብ አለበት።[10] በሎተሪው ቦታ ያገኙ ቤተሰቦች፣ ለተሰጣቸው ቦታ የይገባኛል መብት እንዲኖራቸው፣ የዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫ ሂደትን ጨምሮ፣ የምዝገባ ሂደቱን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ አለባቸው።

- ለSY22-23፣ የዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫ መመሪያዎችን፣ በ osse.dc.gov/publication/office-and-enrollment-and-residency-handbook ተመልከቱ።

[10] D.C. Official Code § 38-306.

ከተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ቦታ እንዲያገኙ የተጠሩ ቤተሰቦች፣ የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ በተጠቀሰው የመጨረሻ ቀን ገድብ ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። የዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫን በምዝገባ የማብቂያ የመጨረሻ ቀን ማቅረብ ያልቻሉ፣ አዲስ ወይም ቦታ የቀየሩ ቤተሰቦች፣ የተዛመዱበትን ትምህርት ቤት ወይም የምዝገባ ቡድኑን በ(***202) 478-5738 ወይም በ*** enroll@k12.dc.gov ማነጋገር አለባቸው።

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚገኙ ቤት አልባዎች ወይም ተፈናቃይ ቤተሰቦች፣ በMcKinney-Vento የ2001 ድንጋጌ[11] በተሰጠው መሰረት የተወሰኑ መስፈርቶችን ማሟላት አይጠበቅባቸውም። በዲስትሪክቱ ዋርዶች (Wards of the District) እና በማደጎ እንክብካቤ ወይም ሌላ በዲስትሪክቱ የተመደበ ማቆያ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ ለትምህርት ቤት የዲስትሪክቱ ዋርድ ደብዳቤን እንደ ዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው።

- ቤት አልባነት የደረሰባቸውን ተማሪዎች ምዝገባን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን በገጽ 27 ይመልከቱ።

የተለየ ከሚያደርገው፣ የ2001 የMcKinney-Vento ድንጋጌ በስተቀር፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪነትን ማረጋገጥ፣ በDCPS፣ ከትምህርት ቤት ክፍያ ነፃ (tuition-free) በሆነ መንገድ ለመማር መስመር የሚያስይዝ ነው። ተማሪው የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫን በበቂ ሁኔታ ማቅረብ አለማቅረቡን፣ DCPS የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል። ተማሪው በቂ የሆነ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ካልቻለ፣ በDCPS ውስጥ፣ ከትምህርት ቤት ክፍያ ነፃ (tuition-free) በሆነ ሁኔታ ተማሪው እንዳይማር DCPS ያግደዋል።

የነዋሪነት ማረጋገጫው ተቀባይነት እንዳላገኘ ከተወሰነ በኋላ፣ ተማሪው ነዋሪነቱን ለማረጋገጥ፣ ሌላ ዕድል እንዲሰጠው ከፈለገ፣ የመጀመሪያው ውሳኔ እንደገና እንዲታይ መጠየቅ ይችላሉ፤ ነገር ግን እስከተከታዩ ሴሚስተር ድረስ ምዝገባው አይፈቀድም። ስለሆነም፣ DCPS እንደ የጉዳዩ ሁኔታ፣ የተማሪውን ልዩ ሁኔታዎችን (ለምሳሌ፣ DCPS ለተማሪው፣ ልዩ የትምህርት አገልግሎት ማቅረብ ግዴታ ካለበት ወይም ከሌለበት) በማገናዘብ፣ ምዝገባው በአሁኑ ሴሚስተር እንዲፈቀድ የሚያደርግበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በቂ ባልሆነ የዲስትሪክት ነዋሪነት ማረጋገጫ ምክንያት ተማሪው ከDCPS ከተወገደ፣ ለወደፊት ተማሪው በDCPS እንዲመዘገብ ከመፈቀዱ በፊት፣ የዲስትሪክት ነዋሪነቱን ለማረጋገጥ የቤት ውስጥ ጉብኝት መካሄድ ይኖርበታል። በተጨማሪም፣ በአሁኑ ወቅት በDCPS ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎችን የዲሲ ነዋሪነትን በተመለከተ፣ ማንኛውም አጠራጣሪ ነገርን ካገኘ፣ ወደ OSSE ነዋሪ ያልሆኑ መርማሪ ክፍል (Non-Residency investigation unit) ይመራል።

- የዲሲ ነዋሪ ያልሆነ በDCPS ውስጥ ገብቶ ለመማር፣ ተጨማሪ ለማወቅ ገጽ 34 ይመልከቱ።

## ምርመራ እና የዲሲ ነዋሪ ያለመሆን አጠራጣሪነት

ሁሉም በDCPS የተመዘገቡ፣ የዲሲ ነዋሪ ያለመሆን ጥርጣሬ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚደረጉ ምርመራዎች በሙሉ በOSSE የሚካሄድ ሲሆን፣ የዲሲ ነዋሪ ያለመሆን ጥርጣሬን በተመለከተ፣ ጥቆማዎች እና መረጃዎችን የሚቀበልበትን አጣዳፊ መስመር አዘጋጅቷል።

የዲሲ ነዋሪ ያለመሆን ጥርጣሬን፣ DCPS ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ይመለከተዋል። በዲሲ ትምህርት ቤት ሠራተኛ እና አስተዳዳሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሌሎች ጉዳዩ የሚያሳስባቸው ዜጎች፤ አግባብ ያለውን ጥርጣሬአቸውን ለOSSE ማመልከት አለባቸው። የዲሲ ነዋሪ ያለመሆንን የጥርጣሬ ውንጀላ ለOSSE ሪፖርት ለማድረግ እና የነዋሪነት ምርመራ እንዲካሄድ ለመጠየቅ፣ OSSEን በsubmitting tips online ወይም በ(202) 719-6500 በመደወል ያሳውቁ።

---

[11] 42 U.S.C. 11431 et seq.

## የትምህርት ቤት ጤና መስፈርቶች

**የትምህርት ቤት ጤና ጥያቄዎች**
የDCPS የጤና አገልግሎቶችን በ(202) 664-2002 ወይም በhealthservices.dcps@k12.dc.gov ያነጋግሩ።

በሁሉም የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች፣ አለማቀፋዊ የጤና ሰርተፊኬት (Universal Health Certificate) እና የአፍ ጤና (Oral Health) ዓመታዊ ምርመራ ማቅረብ አለባቸው። አለማቀፋዊ የጤና ሰተፊኬቱ፣ በተማሪው ሐኪም ወይም ነርስ ባለሙያ የተሞላ፣ ሁሉንም ክትባቶች፣ አስፈላጊ የሆኑ ምርመራዎችንና፣ ከትምህርት መጀመሪያው አንስቶ በ365 ቀናት ውስጥ የተከናወነ አካላዊ ምርመራን ማጠናቀቅ አለባቸው። የአፍ ጤና (Oral Health) ምርመራው፣ በተማሪውን ጥርስ ሐኪም የተከናወነ እና በቅርብ-ጊዜ የተደረገ ዓመታዊ የጥርስ ሐኪም ጉብኝትና ተማሪው በተጨማሪ ያስፈለገው ሌላ የአፍ ጤና አገልግሎቶችን ያጠናቀቀበት መሆን አለበት። እነዚህ ቅጾች፣ ምዝገባው በሚከናወንበት ጊዜ እና ትምህርት ቤት ከተጀመረበት አንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፤ አሁን ያለው ሕጋዊ ቅጽ፣ (ማለትም፣ ባለፉት 365 ቀናት ውስጥ የሚተካሄደ ጉብኝቶችን የሚያሳይ ማስረጃዎችን) ተማሪው በሚገኝበት ትምህርት ቤት ውስጥ በፋይል ውስጥ ተቀምጦ የሚገኝ ካልሆነ በስተቀር፤ ማስገባት አለባቸው። አለማቀፋዊ የጤና ሰርተፊኬት (Universal Health Certificate) እና የአፍ ጤና (Oral Health) ምርመራ ቅጾቹ፣ በDCPS የምዝገባ ጥራዝ (packet) ውስጥ በEnrollDCPS.dc.gov ላይ የሚገኘውን፤ ወይም ከትምህርት ቤቱ ነርስ መውሰድ ይቻላል።

### *ክትባቶች (Immunizations)*

የዲሲ ሕግ በሚጠይቀው መሰረት፣ እያንዳንዱ በDCPS የሚማር ተማሪ፣ የጤና መምሪያ (Department of Health) የክትባት መስፈርቶች መሠረት፣ የወቅቱን ክትባቶችን በተሳካ ሁኔታ መውሰዳቸውን የሚያሳይ መረጃ፤ የእርሱ/እርሷ ትምህርት ቤት የትምህርት መጀመሪያ ቀን በፊት፣ ሕጋዊ የሆነ የክትባት ሰርተፊኬት ማቅረብ አለባቸው። በክትባት ተገቢነት የሚመዘገበው፣ የተሟላ አለም አቀፋዊ የጤና ሰርተፊኬት (Universal Health Certificate)ን ወደ ትምህርት ቤቱ በማቅረብ ነው። በሕክምና ምክንያት ወይም በሃይማኖች የተከለከለ መሆኑን ከዲሲ ጤና፣ ካላረጋገጠ በስተቀር፤ ልጅዎ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር፤ ክትባቶችን መከተቡ፣ የዲሲ ሕግ የሚጠይቀው ነው።

በትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ቀን፣ ሰነዶቹን ያላስገቡ ተማሪዎች፤ በህጉ-ያለመገዛት (non-compliance) ማስታወቂያ የሚያገኙ ይሆናል። ለSY 22-23፤ በህጉ-ያለመገዛት (non-compliance) ማስታወቂያው ከደረሳቸው ጊዜ አንስቶ፣ ሰነዶቹን ለማስገባት 20 የትምህርት ቀናቶች ይኖራቸዋል።

ስለ ዲስትሪክቱ የክትባት ማስፈጸሚያ ፖሊሲ (District Immunization Enforcement Policy) ተጨማሪ መረጃ በOSSE ድህረ-ገጽ ላይ፡ osse.dc.gov/node/1460386#families ይገኛል።

በዲስትሪክቱ ስለሚፈለገው የክትባት መስፈርቶች ወይም የአካባቢ የወረርሽኝ ክትባት ክሊንክን ለማግኘት፤ በዲሲ ጤና (DC Health): dchealth.dc.gov/service/immunization አማካኝነት ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ይችላል።

## በትምህርት ቀኑ ውስጥ፣ መድኃኒት መውሰድ/የሕክምና እንክብካቤ ማስፈለግ

ምንም እንኳን ለምዝገባ አስፈላጊ ባይሆንም፣ ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ ስለሚያስፈልጋቸው፤ መድሃኒቶች፣ ሕክምናዎች፣ ወይም ተጨማሪ እንክብካቤዎች፤ በሕክምና ሰጪ ተሞልቶ የተዘጋጀ ተጨማሪ ወረቀቶችን ቤተሰቦች ማስገባት አለባቸው። ተጨማሪ መረጃዎችን በ dcps.dc.gov/node/1003562 ወይም ከትምህርት ቤቱ ነርስ ማግኘት ይቻላል።

ስለ ትምህርት ቤት ጤና መስፈርቶች ወይም የተማሪውን የጤና ፍላጎቶቹን በትምህርት ቤት ለማሟላት ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎን በ(202) 664-2002 ወይም healthservices.dcps@k12.dc.gov፣ ይጠይቁ ወይም ከትምህርት ቤቱ ነርስ ጋር ይነጋገሩ።

## የአትሌቲክ (Athletic) ተማሪ ምዝገባ

**የDCPS የአትሌቲክስ ቡድን ጥያቄዎች**

athletics.dcps@k12.dc.gov

በDCPS የተማሪ አትሌትነት ለመሳተፍ፣ በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ በተሳካ ሁኔታ በመመዝገብ ላይ የተመረኮዘ ነው። የዲሲ ነዋሪ መሆንን በሚገባ ማረጋገጥን፣ እና ተፈላጊ የሆኑ የክትባት መስፈርቶችን ማጠናቀቅን የሚጨምረውን፣ የትምህርት ቤት ምዝገባን ተማሪው እስኪያጠናቅቅ ድረስ፣ ተማሪው በትምህርት ቤቱ የአትሌትነት ፕሮግራም መሳተፍ አይችልም። የDCPS የምዝገባ ፖሊሲዎችን ለመከተል አለመቻል፣ ተማሪው በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እንዳይሳተፍ ብቁ ያለመሆኑን መግለጫ እና ተማሪው ብቁ በማይሆንባቸው የተማሪ ተሳትፎዎች ውስጥ፣ ትምህርት ቤቱ ሁሉንም ስምምነቶች እንዳይቀበል ሊያደርገው ይችላል። የDCPS የአትሌቲክስ መመሪያ መጽሐፍን፣ በ www.thedciaa.com ለተጨማሪ መረጃዎች መመልከት ይቻላል።

## መውጣት/መልቀቅ

**የመልቀቂያ (Withdrawal) ጥያቄዎች**

*የመልቀቂያ ቡድኑን በDcps.withdraw@k12.dc.gov ያነጋግሩ።*

በአስገዳጅ-የትምህርት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ከDCPS መልቀቅ/መውጣት (withdraw ማድረግ) የሚችሉት ብቸኛው ሁኔታ - በአስመዘገባቸው ወላጅ/አሳዳጊ/ሞግዚት ጥያቄ ብቻ ሲሆን፤ ይህ የተማሪው - ወላጅ/አሳዳጊ/ሞግዚት፣ ከትምህርታዊ ሙብቶቻቸው ብቃት ባለው የፍርድ-ቤት ስልጣን፤ ካልተነሳባቸው በስተቀር ይሆናል። ተማሪው የተመዘገበው በሌላ ዋና እንክብካቤ ሰጪ ከሆነ፣ ማንኛውም ወላጅ/አሳዳጊ/ሞግዚት ተማሪው እንዲለቅ ማድረግ ይችላል። የተማሪውን መልቀቂያ (withdrawal) ለማጠናቀቅ፤ ተማሪው በሌላ ትምህርት ቤት ውስጥ መመዝገቡን የሚያሳይ ሕጋዊ ማረጋገጫ ወይም ሌላ በአስገዳጅ-የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ደንብን በተለየ ሁኔታ ተቀባይ የሚያደርገው፤ - ለምሳሌ ተማሪው ቋሚ የሆነ ጉዳት የደረሰበት ስለሆነ ወይም ከ18 ዓመት በታች ሆኖ፣ ነገር ግን ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊ የሆነውን የዲፕሎማ ፕሮግራም ያጠናቀቀ መሆኑን ማረጋገጫ ያስፈልገዋል። ሕጋዊ ማረጋገጫዎቹ የሚያካትቱት፤ በተቀባዩ ትምህርት ቤት የተሞላ የDCPS የመልቀቂያ ቅጽ፣ ከተቀባዩ ትምህርት ቤት ተማሪው እንደተመዘገበ የሚገልጽ ሕጋዊ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣ ወይም ከተቀባዩ ትምህርት ቤት መዝገቦቹን መጠየቂያ ናቸው። በተጨማሪም፣ የተማሪው መረጃዎች፣ ለመልቀቂያው የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ተሟልተው እስኪጠናቀቁ ድረስ፣ ለተቀባዩ ትምህርት ቤት አይሰጥም። በአስገዳጅ-የትምህርት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ በሌላ ትምህርት ቤት መግባታቸውን

ማረጋገጫ ሳያመጡ ወይም በሌላ በአስገዳጅ-የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ደንብን በተለየ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ማረጋገጫን ሳያቀርቡ፣ ለቀው ወይም ወደትምህርት ቤት መምጣት ሲያቆሙ፤ ካለበቂ ምክንያት ከትምህርት ገበታ መቅረት ፕሮቶኮል (truancy protocols) ተጠያቂ የሚያደርጋቸው እና ማረጋገጫው እስከሚቀርብ ድረስ ሂደቱ ይቀጥላል። አዋቂ የሆኑ ተማሪዎች ከDCPS በማንኛውም ጊዜ በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቅ የሚችሉ እና እነዚህ ተማሪዎች ካለበቂ ምክንያት ከትምህርት ገበታ በመቅረት እና ከዚህ በላይ በተገለጸው በአስገዳጅ-የትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን ተከትሎ ተጠያቂ አያደርጋቸውም።

## ልዩ የምዝገባ ሁኔታ ያላቸው ተማሪዎች

### የተመረጠ 504 ፕሮግራም

**ክፍል (Section) 504 ጥያቄዎች**

*ክፍል (Section) 504 እና የተማሪ እንክብካቤዎች ቡድን (Student Accommodations Team)ን በ*

በ(202) 442-5471 ወይም 504@k12.dc.gov ያነጋግሩ

*በ* https://dcps.dc.gov/page/section-504

ክፍል (Section) 504፤ የ1973፣ የፌደራል ተሃድሶ ድንጋጌ አካል ሲሆን፤ የአካል ጉዳተኞች በሆኑ ግለሰቦች ላይ፣ በፌደራል የገንዘብ እርዳታ የሚሰጡ አገልግሎቶችን፣ ፕሮግራሞችን እና እንቅስቃሴዎችን በሚያገኙ ጊዜ የሚደርስ አድልዎን ለመከላከል የተቀረፀ ነው። የ504 እቅዶች፣ እንክብካቤዎችን እና ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶችን ብቁ ለሆኑ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በመስጠት፣ አጠቃላይ የሆነውን ስርዓተ ትምህርት፣ የመማር ዕድሎችን፣ እና የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ጓደኞቻቸው እኩል በሆነ መልኩ እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

እያንዳንዱ የDCPS ትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር (principal) የተመደበ የ504 አስተናባሪ አለው። የ504 አስተናባሪው፣ በክፍል (Section) 504 ስር ስለሚሰጡ፣ ልዩ እንክብካቤዎችን እና አገልግሎቶችን፣ ከተማሪዎች፣ ወላጆች፣ እና ትምህርት ቤት ሰራተኞች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እንደትምህርት ቤቱ ዋናው የመገናኛ ነጥብ በሆን ያገለግላል። የDCPS ምዝገባ ሲካሄድ፣ ተማሪው ልዩ እንክብካቤዎችን ወይም አገልግሎቶችን በ504 እቅድ በኩል ማግኘት ያስፈልገዋል ብለው ካመኑ፣ ቤተሰቦቹ የትምህርት ቤቱን 504 አስተናባሪ የሆነውን ግለሰብ ማነጋገር ይገባቸዋል።

### ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies)

**የ'Opportunity Academy' ጥያቄዎች ወይም *መመሪያዎች***

የተማሪ እርዳታዎች ቡድኑን በStudent.Placement@k12.dc.gov ወይም በ(202) 939-2004 ያነጋግሩ

በSY22-23 ውስጥ፣ DCPS ሦስት የኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies)ን በ(Ballou STAY, Luke C. Moore, እና Roosevelt STAY) ውስጥ የሚኖረው ሲሆን፤ በግል ተወዳዳሪነት ላይ መሠረት ያደረገ የመማር ፕሮግራምን የሚሰጥ እና ሁሉም በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ወደ ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ (post-secondary) በሚያደርጉት ጉዞ ላይ ስኬታማ እንዲሁኑ አዎንታዊ ጉዞ እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ ይሰጣል። ከተለመደው ውጪ (non-traditional) አቀማመጥ በተለየ አሰራር ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ የተባሉ ተማሪዎች፣ ለዝውውር ሊመሩ ወይም በኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academy) ገብተው እንዲቀጥቅሉ ሊመረጡ ይችሉ ይሆናል። ለዝውውሩ ቅድሚያ የሚሰጠው፣ ተማሪው ከመጀመሪያ ዘጠኝ የክፍል ዓመታት ውስጥ ባገኘው የክሬዲቶች (credits) ብዛት ላይ፣ አሁን ባለበት ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተደረገ ጠንካራ የጣልቃገብነት ሙከራዎች እና በተማሪው እና በወላጅ/አሳዳጊው ለዝውውር ባላቸው ምርጫ ላይ መሠረት በማድረግ ይወሰናል። ከዚህ በታች በምዝገባ መመሪያዎቹ ላይ ተጨማሪ መረጃን ይገኛል፡

- ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies)፣ በምርጫ የሚካሄድ ነው (optional ነው)፤ በኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academy) ገብቶ የመማር ግዴታ የለባቸውም።
- ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies)፣ በ'My School DC' የሎተሪ ሂደት ውስጥ አይካፈሉም።
- ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies) ተማሪዎች፣ የሙሉ ሰዓት (full-time) የልዩ ትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራምን ከBallou STAY እና Luke C. Moore ሊያገኙ ይችላሉ።
- ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies) ተማሪዎች፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ (English Learner) አገልግሎቶች/ፕሮግራም አሰጣጥን ከRoosevelt STAY ሊያገኙ ይችላሉ።

- በአሁኑ ጊዜ በሌላ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች፣ የኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies) ሂደንት ለማከናወን በመመራት ሂደት ውስጥ ማለፍ አለባቸው።
- በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የማይማሩ እና 17 ዓመት እና ከዚያ በታች የሆኑ ተማሪዎች፣ የኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies) ምዝገባ ሂደትን በተማሪ ምደባ ቢሮ በኩል ሊያከናውኑ ይችላሉ።
- በDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የማይማሩ እና 18 ዓመት እድሜ እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎች፣ በዓመቱ በማንኛውም ጊዜ ላይ በኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies) ማከናውን የሚችሉ እና ቦታ እንደተገኘ መግባት ይችላሉ።
- ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies)፣ አማራጭ የምዝገባ ንድፍ (enrollment pattern)ን ስራ ላይ አውሏል።

ስለእያንዳንዱ ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (Opportunity Academies) ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ እባክዎን የDCPS School Profiles Website ማጣቀሻ ያድርጉ።

## የኤምባሲ ቤተሰቦች

በዲሲ ውስጥ በኤምባሲ-የተደገፈ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች፣ የዲሲ ነዋሪነትን የሚገልጽ፤ በአሁኒ-ጊዜ በኤምባሲው የተጻፈ ደብዳቤ፣ የኤምባሲውን ማህተም የያዘ መቅረብ አለበት። በኤምባሲ-የተደገፈ የመኖሪያ አድራሻ፣ የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ይወስነዋል። በዲሲ የኤምባሲ መኖሪያ ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች፣ በኤምባሲው ንብረት አድራሻ የዞን ክልል መሰረት፣ ከክልል ወሰን ውስጥ (inboundary) የሆነ ትምህርት ቤት ውጪ በሆነ በሌላ ትምህርት ቤት ውስጥ ማስገባት ከፈለጉ፣ ማመልከቻውን በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት ማስገባት አለባቸው።

> **የተማሪውን በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ለማግኘት፣**
> *በ* በHttp://enrolldcps.dc.gov/node/41 ይመልከቱ።
>
> የምዝገባ ቡድኑን*በ* enroll@k12.dc.gov ወይም (202) 478-5738 ያነጋግሩ

## ቪዛ የሚጠይቁ የውጪ ሃገር የስኮላርሽፕ (Scholarship) የልውውጥ ተማሪዎች

DCPS፣ በዲስትሪክቱ ሕጋዊነት ያለው ትምህርት ቤት ሆኖ፣ የጉብኝት ተማሪዎች የልውውጥ ፕሮግራም (Student Visitor Exchange Program (SEVP)፣ ፕሮግራሞችን አያካሂድም። በዚህም ምክንያት፣ የDCPS ትምህርት ቤቶች፣ የF-1 ወይም M-1 ቪዛ ስፖንሰር ለሚፈልጉ የውጪ ሃገር የልውውጥ ተማሪዎች፣ የI-20 ቅጾችን አይፈርምም። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ እባክዎችን የሚከተለውን ሊንክ በመጫን ከ'Department of Homeland Security's' ድህረ-ገጽ: studyinthestates.dhs.gov/school-search. ስለ ቪዛ ድጋፍ ሰጪነት (sponsor)፣ ተጨማሪ ጥያቄዎች ያሏቸው ቤተሰቦች፣ የኢሚግሬሽን ጠበቃን እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ።

## የኢሚግሬሽን ሁኔታ (Immigration Status)

እያንዳንዱ ተማሪ ምንም ዓይነት የኢሚግሬሽን ሁኔታ ወይም የዜንነት ማንነት ቢኖረው፤ በሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ የመማር መብቱን፣ DCPS ለመጠበቅ በቁርጠኝነት ይሰራል። በመሆኑም፣ DCPS በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የመኖር ብቃት ያላቸውን ሁሉንም ነዋሪዎች፣ ስለቤተሰቡ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ሳይጠይቅ ትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ገብተው እንዲማሩ ይፈቅዳል። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ dcps.dc.gov/publication/immigration-guidance ይጎብኙ።

## በዓመቱ-አጋማሽ ላይ (Mid-Year) የማመልከቻ ሂደት

የመካከለኛ ዓመት ማመልከቻ ሂደት ከPK3 እስከ 12 ክፍሎች ላሉ ተማሪዎች ወደ ዲስትሪክቱ የመጡ ወይም አሁን ካሉበት ትምህርት ቤት ወደ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት (DCPS ወይም ቻርተር) በሆነ የትምህርት ዓመት ውስጥ ለመዛወር የሚፈልጉ ተማሪዎች ናቸው። ለሁሉም ተሳታፊ የ'My School DC' ትምህርት ቤቶች ለማመልከት፣ ማመልከቻይ ያገለግላል። ወደክልል ወሰን ውስጥ ትምህርት ቤታቸው መዛወር የሚፈልጉ ከK-12 ክፍል ተማሪዎች፣ ምንም ዓይነት ማመልከቻ አያስፈልጋቸውም። የዓመቱ-አጋማሽ የማመልከቻ ጊዜ - ከኦክቶበር (October) እስከ ማርች (March) ድረስ ተራሽሞ የሚሸፍን ሆኖ፤ በማንኛውም የትምህርት ዓመት ውስጥ፣ አዲሱ የሎተሪ ውጤቶች ከመገለፃቸው በፊት ይካሄዳል። የሎተሪ ውጤቶች ከተገለጹ በኋላ፤ ቤተሰቦች - አሁንም-ቢሆን በ'My School DC' አማካኝነት ማመልከት ያስፈልጋቸዋል። የተጠባባቂ ዝርዝሮች (Waitlists)፤ እስከ ትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ፣ በDCPS የምዝገባ ቡድን (DCPS Enrollment Team) ተጠብቆ ይቆያል። አዲስ ተማሪዎች ወይም ዝውውርን የሚጠይቁ ተማሪዎች፣ የዓመቱ-አጋማሽ ማመልከቻን፤ የ'My School DC' የአፋጣን ጊዜ መስመር (Hotline)ን በ(202) 888-6336 በመደወል ማጠናቀቅ አለባቸው። ሁሉም የዓመቱ-አጋማሽ (mid-year) ማመልከቻዎች፤ ከመግባታቸው በፊት የተጠባባቂ-ዝርዝሩን ማግኘት አለባቸው።

## የዲሲ ነዋሪዎች ያልሆኑ (Non-DC Residents)

**የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑ (Non-DC Resident) ጥያቄዎች**

*የምዝገባ ቡድኑ (Enrollment Team)ን* ***በ(202) 478-5738*** *ወይም* enroll@k12.dc.gov *ያነጋግሩ*

DCPS፣ ቦታ ካለ እና ማንም ብቁ የሆነ የዲስትሪክቱ ነዋሪ ለመግባት የማይጠይቅበት ቦታ ከተገኘ ብቻ፣ ነዋሪ ያልሆነ ተማሪ በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመመዝገብ ይችል ይሆናል። የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑ (Non-DC resident) ቤተሰቦች፣ ለDCPS ትምህርት ቤት፣ የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻን ማስገባት እና ማንም የዲሲ ነዋሪ በትምህርት ቤቱ ተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ካልኖረ ብቻ ቦታ ይሰጠዋል። የዲሲ ነዋሪነት-የሚያረጋግጠው ቤተሰብ - የዲሲ ነዋሪነቱን ማረጋገጫ በምዝገባው ጊዜ ማቅረብ ካልቻለ፣ ተማሪው በተጠባባቂነት ከሁሉም መጨረሻ በሆነው ስፍራ፣ ከዲሲ ነዋሪዎች ዝርዝር በኋላ እና ሌላ የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑ በተጠባባቂነት ከተቀመጡበት ሁሉ መጨረሻ ላይ ይቀመጣል። የDCPS የምዝገባ ቡድን፣ ትምህርት ቤቱ ወይም ወላጅ፤ የ'My School DC' በማነጋገር የተጠባባቂነት ደረጃቸውን ሊስተካከሉ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ነዋሪ ያልሆኑ ቤተሰቦች ለመማር የትምህርት ቤት ክፍያ መክፈል አለባቸው።[12] OSSE የዲሲ ነዋሪ ያልሆኑን፣ የትምህርት ክፍያን ያስፈጽማል። ቤተሰቦች በቀጥታ OSSE ጋር በመስራት የትምህርት ቤት ክፍያ ስምምነትን ይፈጥርና የትምህርት ቤት ክፍያውን ይከፍላሉ። የዲሲ ነዋሪ ያልሆነ ተማሪን የማስመዝገብ አላማ ካለዎ፣ OSSEን በ osse.residency@dc.gov በማነጋገር ስለተማሪው ያሳውቋቸው። **OSSE የትምህርት ቤት ክፍያ ስምምነታቸው መፈረሙን እና የመጀመሪያ ክፍያቸው መከፈሉን እስከሚያረጋግጥ ድረስ፣ ነዋሪ ያልሆኑ (Non-resident) ተማሪዎች፣ ክፍል ውስጥ ገብተው ለመማር ብቁ አይሆኑም።**

- ስለ OSSE የመማሪያ ክፍያ ስብሰባ (tuition collection) መረጃዎችን ለማግኘት፣ በosse.dc.gov/publication/tuition-collection. ላይ ጎብኙ።

ከዲሲ ነዋሪነት ወደ ነዋሪ-አለመሆን የሚሸጋገሩ ተማሪዎች፣ በDCPS ትምህርት ቤታቸው ውስጥ እንደገና ሳያመለክቱ በቆየት ብቁ ሆነው እንዲቆዩ የሚያስችላቸው በሚከተሉት ውሱን-የሆኑ ሁኔታዎች ብቻ ነው:

- የDCPS ተማሪ፣ በትምህርት ቤቱ የመጨረሻ መልቀቂያ ክፍል የተመዘገበ እና የመጨረሻ ዓመት የክፍል ደረጃው ውስጥ የሚማር ተማሪ፣ በትምህርት ዓመቱ ነዋሪነት የሌለው ከሆነ፣ ክፍያ-ከፋይ ተማሪ በመሆን፣ የመጨረሻ ዓመት ትምህርቱን እንዲጨርስ ሊፈቀድለት ይችል ይሆናል። ቀጣይነት ያለው ምዝገባም የሚካሄደው የትምህርት ቤት ክፍያ እና ነዋሪ ያልሆነ ተማሪ ክፍያን ለማድረግ ስምምነት ከተፈረመ ነው። ለጥያቄዎችዎ፣ OSSEን በosse.residency@dc.gov ያነጋግሩ።

[12] 5-A DCMR § 5007.1

- የDCPS ተማሪ፣ በትምህርት ቤቱ የመጨረሻ መልቀቂያ ክፍል እንደገና በSeptember ወር የተመዘገበ ሆኖ፣ ነገር ግን በትምህርት ዓመቱ ወይም በበጋ ወራት፣ ከመጨረሻ ዓመት ክፍሉ በፊት መኖሪያውን የቀየረ ተማሪ፣ ክፍያውን ከፋይ ተማሪ በመሆን፣ የመጨረሻ ዓመት ትምህርቱን እንዲጨርስ ሊፈቀድለት ይችል ይሆናል። ቀጣይነት ያለው ምዝገባም የሚካሄደው የትምህርት ቤት ክፍያ እና ነዋሪ ያልሆነ ተማሪ ክፍያን ለማድረግ ስምምነት ከተፈረመ ነው። ለጥያቄዎችዎ፣ OSSEን በosse.residency@dc.gov ያነጋግሩ።

- የኮሎምብያ ዲስትሪክት ዋርድ (ward of the District of Columbia) ከእንግዲህ ዋርድ ያልሆነበት ምክንያት - እነርሱ፣ በቋሚ እንክብካቤ ቦታ ውስጥ የተቀመጡበት ቦታ - ከኮሎምብያ ዲስትሪክት ውጪ ከሚኖሩ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ጥበቃ-አድራጊ ከሆነ ሰው ጋር ሆኖ ከተገኘ፣ በዚያ ትምህርት ቤት የመጨረሻ-ለቅቆ መውጫ በሆነው የክፍል ደረጃ እስከሚደርሱ ድረስ፤ የዋርድ (ward) ሁኔታቸውን ባጡበት ጊዜ ይማሩበት በነበረው የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ መማራቸው ለመቀጠል ፍቃድ ሊያገኙ የሚገባቸው ይሆናል። ከዚህ-ቀደም የነበረው ዋርድ (ward)፣ በDCPS ውስጥ የተመዘገበ ሆኖ ከነበረ፤ ነገር ግን - የዋርድ ሁኔታቸውን (ward status) ባጡበት-ጊዜ፣ የሕዝብ ትምህርት ቤት ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በልዩ ትምህርት (special education) ምደባ ውስጥ ይማሩ ከነበረ፤ ዋርድ ሁኔታቸውን (ward status)[13] ያጡበትን ዓመት ተከትሎ እስከአለው የትምህርት ዓመት መጨረሻ ድረስ፤ በDCPS በኩል በሕዝብ ትምህርት ቤት ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ መማራቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ ያሉ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ክፍያ እንዲከፍሉ አይጠየቁም።

## የDCPS ተመራጭ (Selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ፕሮግራም መግቢያ መስፈርቶች እና ሂደቶች

አንድ እና ከዚያ በላይ በሆኑ የDCPS ተመራጭ (selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች የሚያመለክቱ ተማሪዎች፣ የ'My School DC' ማመልከቻን ተጨማሪ የሆነውን ክፍል፣ አጠናቀው መሙላት አለባቸው። ተጨማሪው ክፍሉም፣ እንደየትምህርት ቤቱ ወይም ፕሮግራሙ ይለያያል፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም የራሱ የሆኑ መስፈርቶች[14] ስለሚኖራቸው ነው። ለጥያቄዎችዎ፣ የምዝገባ ቡድኑ (Enrollment Team)ን በ enroll@k12.dc.gov ወይም በ(202) 478-5738 አነጋግሩ።

1. ቤንጃሚን ባነከር አካዳሚ (Benjamin Banneker Academic) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: http://www.benjaminbanneker.org/
2. ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ (Bard High School Early College) ዲሲ (Bard DC): bhsec.bard.edu/dc
3. ኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓስ (Columbia Heights Education Campus (CHEC): checdc.org
4. ዱክ ኤሊንግተን (Duke Ellington) የስነጥበባት (Arts) ትምህርት ቤት: ellingtonschool.org
5. የቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ (Early College Academy) በኩሌጅ (Coolidge) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: coolidgeshs.org
6. መኪንሊ ቴክኖሎጂ (McKinley Technology) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: mckinleytech.org

[13] DC Code 38-302(e)

[14] ትምህርት ቤቱ በቅርብ ጊዜ በመዘጋቱ ምክንያት፣ የቀድሞ ዓመት የመጨረሻው ሪፖርት ካርዳቸው ስላልተዘጋጀና የሌላቸው ተማሪዎች፣ በዚህ ዓመት የተሰጣቸውን የመጀመሪያው የማማከሪያ ሪፖርት ካርዳቸውን (advisory report card) እንደ ብቁነት መወሰኛ ሊጠቀሙበት ይችሉ ይሆናል። ይህ ሁኔታ የገጠማቸው ቤተሰቦች ትምህርት ቤታቸውን በቀጥታ ማነጋገር ይገባቸዋል።

7. የ'Phelps የምህንድስና (Architecture)፣ የግንባታ እና የኢንጂነሪንግ (Construction, and Engineering) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: phelpshsdc.org
8. 'School Without Walls' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: swwhs.org

ከትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽ በተጨማሪ፣ የSY22-23 የDCPS የተመራጭ (selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ፕሮግራም ማመልከቻ መስፈርቶች እና መግቢያ ሂደቶችን እዚህ በenrolldcps.dc.gov/node/46. መመልከት ይቻላል።

# ከተማአቀፍ፣ ሁለት ቋንቋ፣ እና ሞንተሶሪ (Montessori) ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች

## ከተማአቀፍ ትምህርት ቤቶች

1. Capitol Hill Montessori @ Logan (ከPK3-8)
2. Dorothy I. Height Elementary School (ከPK3-5)
3. Excel Academy (ከPK3-8)
4. Leckie Education Campus – መካከለኛ ክፍሎች ብቻ (ከ6-8)
5. Military Road Early Learning Center (ከPK3-PK4)
6. Ron Brown College Preparatory High School (ከ9-12)
7. School-Within-School (ከPK3-5)
8. Stevens Early Learning Center (ከPK3-PK4)

## ሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች

*ሙሉ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች (Whole School Programs) – ሁሉም የተመዘገቡ ተማሪዎች በሁለት ቋንቋ ፕሮግራሙ ውስጥ ይካፈላሉ። እንግሊዘኛ ቋንቋን-ብቻ (English-only)፣ የመጠቀም አማራጭ በትምህርት ቤቱ የለም።*

1. Bancroft Elementary School (ከPK3-5)
2. Bruce-Monroe Elementary School (ከPK3-5)
3. Columbia Heights Education Campus (ከ6-8)
4. Houston Elementary School (ከPK3-4)
5. Oyster-Adams Bilingual School (ከPK4-8)
6. Powell Elementary School (ከPK3-5)

*የመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጡ ፕሮግራሞች (Strand Programs) – የሚሰጠውን የሁለት ቋንቋ ፕሮግራምን እና ሁለት ቋንቋ ፕሮግራም ያልሆነውን ጨምሮ፤ የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች።*

1. Cleveland Elementary School (ከPK3-5)
2. Marie Reed Elementary School (ከPK3-5)
3. Tyler Elementary School (ከPK3-5)

## የሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች – ከ6-12ኛ ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች - የባለሁለት ቋንቋ (Dual Language) ፕሮግራሞች

ከመጀመሪያ ደረጃ የባለ ሁለት ቋንቋ (dual language) ፕሮግራሞቻችን በተጨማሪ፤ ተማሪዎች አንዳንድ ዋና ኮርሶቻቸውን (core courses) በስፓኒሽ ቋንቋ እንዲወስዱ የሚያደርጋቸውን - DCPS በርካታ ቁጥር ያላቸው የሁለተኛ

ደረጃ የባለ ሁለት ቋንቋ (dual language) ፕሮግራሞችን ይሠጣል። በሁለት ቋንቋ (dual language) አዘዋዋሪ ሆኖ የሚያስተላልፍ (feeder pattern) በኩል የሚማሩ-ተማሪዎች፤ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በሁለት ቋንቋ (dual language) ፕሮግራሞች ውስጥ የመመዝገብ መብት አላቸው። በኮሎምቢያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓስ (Columbia Heights Education Campus) (ከ9-12) እና በማክፋርላንድ (MacFarland) መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በሎተሪ ለሚገቡ ተማሪዎች፤ በ'My School DC' ሎተሪ ውስጥ ሌላ የባለ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) ፕሮግራም አማራጭ፣ ለብቻው-ተለይቶ አይኖርም። በቋንቋ የብቃት-ችሎታ፣ የተማሪ ፍላጎት፣ እና የጊዜ-ሰሌዳው እንደተገኘበት ሁኔታ ላይ መሠረት በማድረግ፤ የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ በሁለት ቋንቋ (Dual Language) ክፍሎች ውስጥ ገብተው እንዲማሩ ይመደባሉ። በሩዘቬልት (Roosevelt) HS ውስጥ፣ በሎተሪ ወደ ትምህርት ቤቱ ገብቶ-የሚማሩ ተማሪዎች፤ በሁለት ቋንቋ (Dual Language) ፕሮግራም ወይም በሁለት ቋንቋ (non-Dual Language) ባልሆነ ፕሮግራም ውስጥ፤ ወይም በሁለቱም ለመግባት ማመልከት ይችላሉ።

## የሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራሞች

### በሙሉ (Whole) የትምህርት ቤት ፕሮግራም– ሁሉም የተመዘገቡ ተማሪዎች በሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራም ይሳተፋሉ።

1. Capitol Hill Montessori @ Logan (ከPK3-8)

### መደበኛ ፕሮግራሞች (Strand Programs) – መደበኛ የሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራምን እና ሞንተሶሪ ያልሆነ (non- Montessori) ፕሮግራምን የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች

1. Langdon Elementary School (ከPK3-5)
2. Nalle Elementary School (ከPK3-5)

## ሁለት ቋንቋ ፕሮግራም የምዝገባ ፖሊሲዎች

### *የቋንቋ የበላይነት: ከPK3-1 ክፍሎች የምዝገባ ፖሊሲ*

ተማሪዎች ከK - 12 ክፍሎች ገብቶ የመማር መብት ባላቸው ትምህርት ቤት(ቶች) ውስጥ፣ የ'My School DC' ሎተሪን ሳያመለክቱ መግባት ይችላሉ። ሁለት ቋንቋ መማርን ለመደገፍና እንግሊዘኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ የሁለት ቋንቋ (bilingual) አገልግሎቶችን እንደሚያገኙ ለማረጋገጥ፣ ከPK3-1 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የDCPS የሁለት ቋንቋ ፕሮግራም፣ ከክልል ወሰን ውጪ (out-of- boundary) የሆኑ የሎተሪ አመልካቾች፣ "እንግሊዘኛ ቋንቋ የበላይነት (English-dominant)" ወይም "የስፓኒሽ ቋንቋ የበላይነት (Spanish-dominant)" ብለው እየለዩ እንዲገልጹ ይጠይቃል። 'የቋንቋ-የበላይነት (Languagedominance)' የሚለው ቃል፣ ለአመልካቹ ተማሪ የመጀመሪያ የመግባቢያ ቋንቋ የሆነው ተብሎ ይተረጎማል። የሎተሪ ውጤቶቹ ከተገለጹ በኋላ፣ እና ከምዝገባው በፊት፣ ሁሉም "የስፓኒሽ ቋንቋ የበላይነት (Spanish-dominant)" ብለው የተዛመዱ ተማሪዎች፣ የቋንቋ ችሎታ ግምገማ ሊደረግላቸው ይችል ይሆናል። የቋንቋ ችሎታ መስፈርትን የማያሟሉ ተማሪዎች፣ በሎተሪው አማካኝነት በዘፈቀደ (random) በተሰጠ ቁጥራቸው እና ሌላ ከዚህ ቀደም ብቁነታቸውን ላረጋገጡባቸው ምርጫዎችን በተከተለ ሁኔታ፣ በትምህርት ቤቱ የእንግሊዘኛ የበላይነት (English-dominant) ትምህርት ቤቶች የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይቀመጣሉ። በቋንቋ የበላይነት (language dominance) ላይ የበለጠ መረጃን ለማግኘት፣ እባካችሁ እዚህ፣ [dcps.dc.gov/DL](dcps.dc.gov/DL) ተመልከቱ።

### *የስፓኒሽ ቋንቋ ችሎታ ብቃትን መፈተኛ: ከ2-12 ክፍሎች የምዝገባ ፖሊሲ*

ተማሪዎች ከK - 12 ክፍሎች ገብቶ የመማር መብት ባላቸው ትምህርት ቤት(ቶች) ውስጥ፣ የ'My School DC' ሎተሪን ሳያመለክቱ መግባት ይችላሉ። ከዚህ በፊት በDCPS ወይም በዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የስፓኒሽ ሁለት ቋንቋ ፕሮግራም ውስጥ ያልተካፈሉ፣ እና የስፓኒሽ ቋንቋ የሚናገሩና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ያልሆኑ፣ ከክልል ወሰን ውጪ (Out-of-boundary) የሎተሪ አመልካቾች፤ በኮሎምቢያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓስ (Columbia Heights

Education Campus (CHEC) ውስጥ - ዘግይቶ በመግቢያ (late entry) ፕሮግራም ውስጥ - ከ6-8 ክፍሎች ውስጥ የተመዘገቡ ካልሆኑ በስተቀር፣ የስፓኒሽ ችሎታን መፈተኛ መውሰድ ያስፈልጋቸው ይሆናል። ፈተናው የሚካሄደው በሎተሪ የተዛመዱት ዝርዝር ከተገለጸ በኋላ ነው። ግምገማውን ተማሪው ካላለፈ፣ በሁለት ቋንቋ ፕሮግራም ትምህርት ቤት ውስጥ ያገኙትን መዛመድ መልቀቅ ይኖርባቸዋል። ይህ ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ፣ በወላጆቹ ጥያቄ፣ በፊት አመልካቹ "በተጠባባቂነት ውስጥ ባልነበረበት" በሁሉም ትምህርት ቤቶች የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ተመልሶ እንዲገባ ይደረጋል። ይህ ጥያቄ በወላጅ እና ተማሪው ለ'My School DC' የሚቀርበው፥ የስፓኒሽ ችሎታ ፈተናውን መውደቁ ከታወቀ በኋላ ብቻ ነው።

ማስታወሻ፡ ተማሪው የቋንቋ መስፈርቶቹን የማያሟላ ከሆነ፣ የስፓኒሽ ችሎታ ግምገማ ፈተናን ለመግቢያነት የማይጠየቀው - እነርሱ፣ በCHEC ውስጥ ከ6-8 ክፍሎች ውስጥ፣ ዘግይቶ የመግቢያ ፕሮግራም ውስጥ ካልሆነ በስተቀር፣ በሁሉም የDCPS የሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች ክፍል ውስጥ ብቁ ይሆናሉ።

### *ሁለት ቋንቋ (Dual Language) ለሚጠቀሙ (ከPK3-5) ምዝገባ*

ሁለቱንም - የባለ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) የሚጠቀሙ እና የእንግሊዘኛ-ብቻ (ወይም ባለ ሁለት ቋንቋ ያልሆኑ/non-Dual Dual Language ለሚጠቀሙ) **በመጀመሪያ ደረጃ (elementary) ትምህርት ቤት ክፍሎች ውስጥ -** በመስጠት የሚያገለግሉ ትምህርት ቤቶች፤ ሁሉም በሁለት ቋንቋ (Dual Language) መስጫ ውስጥ፣ መማር ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች - በ'My School DC' አማካኝነት የሎተሪ ማመልከቻቸውን፣ ማስገባት አለባቸው። ባለ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) በሚጠቀም ትምህርት ቤት - በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሚኖሩ ተማሪዎች፤ በሎተሪ ወደ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) ሰጪ- ውስጥ የመግቢያ ምርጫቸውን የሚያገኙ እና ወደ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) ሰጪ - ወዲያውኑ እንዲመደቡ ከሚያደርገው - በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤት ውስጥ የመመዝገብ መብታቸውን፣ በማንኛውም ጊዜ ይጠበቅላቸዋል። በአሁኑ-ጊዜ በእንግሊዘኛ-ብቻ (ወይም ባለ ሁለት ቋንቋ ያልሆኑ/non-Dual Dual Language ለሚጠቀሙ) ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች፤ በአሁኑ-ትምህርት ቤታቸው ውስጥ በሚገኝ የባለ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) የሚጠቀም ፕሮግራም ውስጥ ለመግባት ማመልከት ይችላሉ፤ ነገር ግን - በወንድምና እህት (sibling) ውእይም በክልል ወሰን ውስጥ (In-Boundary) ምርጫቸው ምክንያት ብቁነትን ካላገኙ በስተቀር፤ አሁን-ባለው ምዝገባቸው መሠረት ምርጫቸውን ሊያገኙ አይችሉም። ለቋንቋ-የበላይነት (Language Dominance) - (ከPK3-1) የምዝገባ ፖሊሲዎች፣ እና ለስፓኒሽ ቋንቋ ችሎታ ብቃትን መፈተኛ (ከ2-5 ክፍሎች)፤ ወደ ባለ ሁለት ቋንቋ (Dual Language) የሚጠቀሙ ፕሮግራሞች ለሚያመለክቱ አመልካቾች በሙሉ በስራ-ላይ ውሎ ያገለግላል።

### *ሁለት ቋንቋ ያልሆነ (Non-Dual Language) አማራጭ ትምህርት ቤት ምደባ (እህት ትምህርት ቤት) (ከK-8 ክፍሎች)*

በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ውስጥ እንግሊዘኛ ብቻ (English-only) አማራጭ የሌለው፣ የሁለት ቋንቋ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩና ቤተሰቦቻቸው በሁለት ቋንቋ ፕሮግራሙ ውስጥ እንዲሳተፉ የማይፈልጉ፣ በአስገዳጅ-የትምህርት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቤተሰቦች ለሆኑት፣ የምዝገባ ተለዋጭ አማራጭን DCPS ይሰጣቸዋል። ሁለት ቋንቋ ያልሆኑ ተለዋጭ ትምህርት

ቤቶች ለPK3፣ PK4 ወይም ከክልል ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ተማሪዎች አያገለግልም።

| የሁለት ቋንቋ ፕሮግራም (እንግሊዘኛ ብቻ/English-Only ያልሆኑ ክፍሎች አማራጭ) | ሁለት ቋንቋ ያልሆነ አማራጭ (በትምህርት ቤት የሚሰጡ ክፍሎች) |
|---|---|
| Bancroft Elementary School (ከPK3-5) | Tubman Elementary School (ከPK3-5) |
| Bruce-Monroe Elementary School (ከPK3-5) | Raymond Elementary School (ከPK3-5) |
| Columbia Heights Education Campus (ከ6-8) | Cardozo Education Campus (ከ6-8) |
| Houston Elementary School (ከPK3-4 ከክፍል ወደ ክፍል እያደገ የሚሄድ የሁለት ቋንቋ ፕሮግራም) | Burrville Elementary School (ከPK3-5) |

| | |
|---|---|
| Oyster-Adams Bilingual School (ከPK4-8)፣ | School Without Walls at Francis-Stevens (ከPK3-8) |
| Powell Elementary School (ከPK3-5) | Dorothy I. Height Elementary School (ከPK3-5) |

- የሁለት ቋንቋ ትምህርት ቤት/ፕሮግራሞች ሙሉ ዝርዝርን ለማግኘት በገጽ 35 ይመልከቱ።

ከ2-8ተኛ ክፍሎች ውስጥ የሚገኝ በክልል ወሰን ውስጥ (inboundary) የሚገኝ ተማሪ፣ የስፓኒሽ ቋንቋ ብቃት ሳይኖረው፣ ቤተሰቦቹ በሁለት ቋንቋ (dual language) ፕሮግራም ውስጥ ለማስመዝገብ ቢመርጡ እና ሁለት ቋንቋ ያልሆነ (non-dual language) አማራጭ ትምህርት ቤትን ባይሞሉ፣ ትምህርት ቤቱ የስፓኒሽ ቋንቋን የማወቅ ብቃትን ታሳቢ በማያደግ፣ ባለሁለት ቋንቋ (dual language) ትምህርት ቤት ማስመዝገባቸውን እና ልጃቸው በሁለት ቋንቋ ፕሮግራሙ ውስጥ ሊያጋጥመው ስለሚችለው ማንኛውም የቀለም ትምህርት ችግር ተገንዝበው እንዳደረጉት የሚያረጋግጥ የመልቀቂያ (waiver) ስምምነት እንዲፈርሙ ቤተሰቦች ይጠየቃሉ።

**የተማሪ ምደባ (Placement) ቢሮ**
3535 V Street, NE
Washington, DC 20018
በ(202) 939-2004 ወይም
student.placement@k12.dc.gov ያነጋግሩ

### *ሁለት ቋንቋ ያልሆነ አማራጮች ለPK3 እና PK4*

አስገዳጅ ባልሆኑ (non-compulsory) ክፍሎች በ(PK3 and PK4) ለሚመዘገቡ ተማሪዎች ካልሆነ በስተቀር፣ DCPS ሁለት ቋንቋ ያልሆኑ አማራጮችን በመጠቀም መግባትን ዋስትና አይሰጥም። የክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ትምህርት ቤታቸው፣ እንግሊዘኛ ብቻ - ያልሆነ ባለሁለት ቋንቋ ትምህርት ቤት ምርጫ ውስጥ ለሆኑ የPK3 እና PK4 ተማሪዎች ቤተሰቦች የሆኑ፤ ነገር ግን በሁለት ቋንቋ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ መካፈል የማይፈልጉ ቤተሰቦች፣ በ'My School DC' ሎተሪ አማካኝነት ሁለት ቋንቋ ያልሆነ አማራጭ ትምህርት ቤቶች ቦታ ለማግኘት ማመልከት አለባቸው። በምዝገባው ወቅት፣ ሁለት ቋንቋ ያልሆነ አማራጭ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ወንድምና እህት ካላቸው፤ ተማሪ የወንድምና እህት ምርጫ የማግኘት ጥያቄውን ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ለሆነ ትምህርት ቤት የሚያመለክቱ ተማሪዎች፣ በዚያ ትምህርት ቤት፣ በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) ምርጫ ማግኘት አይችሉም።

በሁለት ቋንቋ፣ በስፓኒሽ ቋንቋ ችሎታ፣ እና በሎተሪ ላይ የተለየ ጥያቄዎች ላይ፣ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፤ dcps.dc.gov/DL ይጎብኙ።

## ሞንተሶሪ (Montessori) ትምህርት ቤት ምዝገባ ፖሊሲዎች

ከሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራሞች ጋር ያሉ ትምህርት ቤቶች ጋር በክልል ወሰን ውስጥ (in-boundary) የሆኑና በDCPS የሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራሞች ላይ ፍላጎት ያላቸው ቤተሰቦች፤ ከዚህ-ቀደም የሞንተሶሪ (Montessori) ተሞክሮ ያላቸው መሆን አያስፈልጋቸውም - ነገር ግን የምናበረታታቸው ናቸው። ከክልል ወሰን-ውጪ (out-of-boundary) ያሉ ወይም፣ አዲስ የPK ተማሪዎችን የሚያስመዘግቡ ቤተሰቦች፤ አሁንም-ቢሆን በ'My School DC' አማካኝነት ማመልከት እና የመዛመቻ ወይም የተጠባባቂነት ዕድልን ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። በDCPS የሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራሞች ያመለከቱ ቤተሰቦች፣ ግን ከዚህ ቀደም የሞንተሶሪ (Montessori) ልምድ የሌላቸው፣ የትምህርት ቤቱ የሞንተሶሪ (Montessori) ፕሮግራም በሚወስነው መሠረት፣ በትምህርት ቤት ጉብኝት እና/ወይም ቃለ-መጠይቅ እንዲካፈሉ ይጠበቅባቸው ይሆናል።